# የእውነት ምስክር

ኅዳር 2012 ዓ.ም

## ቃለ ምልልስ

"ነፍሳትን ወደ እግዚአብሔር መንግስት መመለስ የሚል አንድና ብቸኛ ራዕይ ነበር የነበረው"

**ቢሾፕ ደጉ ከበደ**
የኢትዮጵያ ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን ዋና አስተዳዳሪ

## በውስጥ ገጾች

ቀጣይ የእግዚአብሔር ሥራ
**በቀጣይ ትውልድ**

**መንፈሳዊ ህይወት**
ለመንፈሳዊ አገልግሎት

**መዝሙርን ከምንጩ**

**ደቀመዝሙር**

**ታላቁ ስደትና ፍሬው**

**ትሕትና** እና **ትዕቢት**

**የመረዳት** ባለጠግነት

**አገልግሎት** እና **ቤተሰብ**

"ለቀባሁትም ሰው መብራትን አዘጋጃለሁ።"

መዝ. 132፥17

# ማውጫ


**ርዕሰ አንቀጽ**
1 **ትምህርትና ሥልጠና ለምንና እንዴት?**
ዝግጅት ክፍሉ

**ትኩረት**
2 **ቀጣይ የእግዚአብሔር ሥራ**
ዝግጅት ክፍሉ

**አባቶችህን ጠይቅ**
3 **ቃለ ምልልስ ከቢሾፕ ደጉ ከበደ ጋር**
እህት ኢየሩሳሌም መዝገቡ

**መንፈሳዊ ህይወት**
11 **መንፈሳዊ ህይወት ለመንፈሳዊ አገልግሎት**
ቄስ ካሳሁን አባይ

**ደቀመዝሙር**
14 **ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው!**
ወንድም ኃይለየሱስ ወሰን

**አምልኮ**
17 **መዝሙርን ከምንጩ**
ወንድም ዮሐንስ ኃይሉ

**ዶክትሪን**
20 **የመረዳት ባለጠግነት**
ቢሾፕ አዲሱ በሪሶ

**ያዳናቸው ይናገሩ**
22 **ታላቁ ስደትና ፍሬው**
ወንድም ደሜ አበራ

**ቅድስና**
25 **ትሕትና እና ትዕቢት**
ቄስ ኤልያስ ሽባባው

**ቤተሰብ**
29 **አገልግሎትና ቤተሰብ**
ወንድም ወሰነ ኃይሉ



የኢትዮጵያ ሐዋርያዊት
ቤተክርስቲያን

የእውነት ምስክር መጽሔት
በ 1981 ዓ.ም መታተም
የጀመረች ሲሆን በተለያዩ
ምክንያቶች ህትመቶቹ
በተከታታይነት ለመታተም
አልቻሉም። እግዚአብሔር
ቢፈቅድ ብንኖርም ከዚህ ዓመት
ጀምሮ በዓመት አራት ጊዜ ያህል
ይታተማል ብለን እናምናለን።

1ኛ ዓመት ቁጥር 2

ኅዳር 2012

<u>አሳታሚ</u>

የኢትዮጵያ ሐዋርያዊት
ቤተክርስቲያን

<u>አዘጋጆች</u>

ቢሾፕ ኢሳያስ አሻ

ቢሾፕ አንዱአለም ብርሃኑ

ወ/ም ብርሃኑ በቀለ

<u>የገጽ ቅንብር</u>

ወ/ም ወሰነ ኃይሉ

<u>ፊደል ለቀማ</u>

ወ/ም ብርሃኑ በቀለ

<u>ህትመት ክትትል</u>

ወ/ም ብርሃኑ በቀለ

<u>የኮምፒውተር ጽሑፍ</u>

እህት አስቴር አበበ

እህት አማረች ከበደ

## ርዕሰ አንቀጽ

# ለእግዚአብሔር ሕዝብ ትምህርትና ሥልጠና ለምንና እንዴት?

✍ ቢሾፕ ኢሳያስ አሻ

የእግዚአብሔር ሕዝብ (ልጆችም አዋቂዎችም፣ ተከታዮችም መሪዎችም፣ በአጠቃላይ ሁሉም) እንደ ምዕመናን ወደ ክርስትና ሕይወት ሙላት እንዲደርሱ፤ በልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሳተፉት ደግሞ በየአገልግሎታቸው ብቁና ውጤታማ እንዲሆኑ መደበኛ ባልሆኑ የትምህርት አሰጣጥ መንገዶችና በመደበኛ የትምህርት ሥልጠና ፕሮግራሞች የማያቋርጥ ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኙ አስፈላጊ ይሆናል።

## ትምህርትና ሥልጠና ለምን?

የእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔርን ቃል መማር ያለበት የተሟላ እውቀት እንዲኖረው (2ጢሞ. 3÷14-17)፣ እግዚአብሔርን እንዲፈራ (ዘዳ. 4÷9፤ 10)፣ ደቀመዝሙር እንዲሆን (ማቴ. 28÷20)፣ ለልዩ ልዩ አገልግሎትና ለጽድቅ ሥራ የተዘጋጀና ብቃት ያለው እንዲሆን (ኤፌ. 4÷11-13)፣ ለክርስቶስ ፍጹም ሆኖ እንዲቀርብ (ቆላ. 1÷28)፣ ወዘተ ነው።

## ትምህርትና ሥልጠና እንዴት?

- ትምህርትና ሥልጠና ሊሰጥ የሚችለው መደበኛ ባልሆኑ ልዩ ልዩ መንገዶችና መደበኛ በሆኑ ልዩ ልዩ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ነው። ከእነዚህ መካከል ለምሳሌ ያህል ጥቂቶቹን እጠቅሳለሁ።
- በየቤተሰቡ ልጆች ከወላጆቻቸው ሊማሩና ሊሠለጥኑ እንደሚገባ ከቃሉ መረዳት ይቻላል። በዘዳ. 6÷7 ላይ፥- *"... ለልጆችህም አስተምረው"* ይላል። በምሳሌ 22÷6 ላይ *"ልጅህን በሚሄድበት መንገድ ምራው÷በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።"* ይላል። ወላጆቻቸው ስለ ክርስትና ሕይወት ያስተማሩአቸውና የሕይወት ተሞክሮአቸውን እያሳዩአቸው ያሠለጠኑአቸው ልጆች ከእግዚአብሔር መንገድ ፈቀቅ አይሉም።
- አዋቂዎች መደበኛ ባልሆነ መንገድም በመደበኛ ፕሮግራሞችም ሊማሩ ይችላሉ። ከመደበኛ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ውጭ በግል ጥረትና ከእግዚአብሔር ሊማሩ ይችላሉ። ኢሳ. 50÷4-5 ላይ፥- *"የደከመውን በቃል እንዴት እንደምደግፍ አውቅ ዘንድ ጌታ እግዚአብሔር የተማሩትን ምላስ ሰጥቶኛል፤ ማለዳ ማለዳ ያነቃኛል÷እንደ ተማሪዎችም ትሰማ ዘንድ ጆሮዬን ያነቃቃል።..."* ይላል። ኢሳ. 54÷13 ላይ ደግሞ፥- *"ልጆችሽ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ÷የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።"* ይላል።

ስለዚህ ከእግዚአብሔር ለመማር የሚፈቅዱ ሁሉ ከእርሱ ሊማሩ ይችላሉ። ከእግዚአብሔር በምንማርበት ጊዜ በስሜታችን የተሰማንን ሁሉ የእግዚአብሔር ትምህርት ነው ብለን እንዳንደመድም ጥንቃቄ ያስፈልጋል። በስሜታችን የሚሰማን የግል መረዳት የእግዚአብሔር ትምህርት መሆን አለመሆኑን የምናረጋግጠው በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚስማማ የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው። በመሆኑም ከእግዚአብሔር ለመማር ስንፈቅድ በግላችን መጽሐፍ ቅዱስን እያጠናን እና ቤተክርሰቲያን በልዩ ልዩ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞቿ የምትሰጠውን ትምህርትና ሥልጠና እየተከተልን ሊሆን ይገባል። በምሳሌ 22÷20፤21 ላይ እንደተጻፈው የእውነትን ቃል እርግጥነት እንድናውቅና ለሚጠይቀን የእውነት ቃል መመለስ እንድንችል ከተጻፉልን ቅዱሳት መጻሕፍት እያነበብን ልንማር ይገባል። (1ጴጥ. 3÷15)

ምዕመናን ከመጋቢዎቻቸው አገልጋዮች ደግሞ ከመሪዎቻቸውና ቤተክርስቲያን ካዘጋጀቻቸው የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች እየተማሩ መልካም ምሳሌ የሆኑ የእግዚአብሔር ሰዎችን ትምህርት፣ አካሄድ፣ አሳብ፣ እምነት፣ ትዕግሥት፣ ፍቅር፣ መጽናት፣ ስደትና መከራ ተከታዮች ሊሆኑ ይገባቸዋል።

አገልጋዮች በግል በሚያደርጉት የመማር ጥረት ቅዱሳት መጻሕፍትን ሳይታክቱ በማንበብና በትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ቸል ሳይሉ በመሳተፍ በቃል፣ በኑሮ፣ በፍቅር፣ በእምነት በንጽሕና ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሆነው ለመምከርና ለማስተማር ሊጠነቀቁ ይገባል። በማንም የማይናቁ፣ በነገር ሁሉ ያደጉ አገልጋዮች ሆነው ራሳቸውንም የሚሰሙአቸውንም ለማዳን ሊተጉ ይገባቸዋል።

መማርና መሰልጠን ሊቆም አይገባም። የቤተክርስቲያን የበላይ አስተዳደር የሚያዘጋጀው የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ብቻውን በቂ ሊሆን ስለማይችል ምዕመናንን ወደ ክርስትና ሕይወት ሙላት ለማድረስና አገልጋዮችን ለተሰማሩለት አገልግሎት ብቁ ለማድረግ በየአጥቢያውም፣ በየንዑስ ሰበካውም፣ በየቅርንጫፍ ሰበካውም ትምህርትና ሥልጠናዎች ሊኖሩ የሚያስፈልግ ሲሆን ማንኛውም በመደበኛ መልክ የሚሰጥ ትምህርትና ሥልጠና በየደረጃው ካለው የቤተክርስቲያን የበላይ ኃላፊዎች እውቅናና ፈቃድ የተሰጠው ቢሆን የቤተክርስቲያንን የትምህርትና የመንፈስ አንድነት ለመጠበቅ የሚጠቅም ይሆናል።

ትምህርትና ሥልጠና ጤናማና የክርስቶስን አካል (ቤተክርስቲያንን) የሚያንጽ የሚሆነው ምዕመናንም ሆኑ አገልጋዮች የቤተክርስቲያን ትምህርት ደቀመዛሙርት ሲሆኑና የቤተክርስቲያንን ትምህርት ፈጽመው የተማሩ ሲሆኑ ነው።

ጌታ ኢየሱስ፥- *"ደቀመዝሙር ከመምህሩ አይበልጥም፤ ፈጽሞ የተማረ ሁሉ ግን እንደ መምህሩ ይሆናል።"* ብሏል። (ሉቃስ 6÷40) ስለዚህ ትምህርትና ሥልጠና ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን እና እርሱን የሚመስሉትን ለመከተል ይሁን። ■

ትኩረት

# ቀጣይ የእግዚአብሔር ሥራ በቀጣይ ትውልድ

ከዝግጅት ክፍሉ

የእግዚአብሔር ቃል  የወራሽ ጉዳይ ምን ያህል አንገብጋቢ እንደሆነ በኤርምያስ 49፥1 ላይ *“ለእስራኤል ልጆች የሉትምን? ወይስ ወራሽ የለውምን?”* ሲል ይናገራል። አብርሃም በዘመኑ ሁሉ ለ “ወራሽ ልጅ” ወደ እግዚአብሔር ሲጮኽ እንደኖረና በመጨረሻ ዕድሜው ላይ እግዚአብሔር ይስሐቅን እንደሰጠው መጽሐፍ ቅዱሳችን ይነግረናል።

ከክርስቶስ ትንሳኤ በኋላ ሃምሳ ቀናት ቆይቶ በበዓለ ሃምሣ የአዲስ ኪዳን የገሃነም ደጆች የማይችሉአት ቤተክርስቲያን ስትወለድ የአንድ አምላክ በሥጋ የመገለጥ፣ የሞቱና የትንሳኤው፣ የዳግም ልደት የወንጌል አዋጅ ሲታወጅ መጽሐፍ ቅዱሳችን ላይ በስፋት እናያለን።

የወንጌል እሳት በየቦታው ሲቀጣጠል፣ ሐዋርያትና ተከታዮቻቸው ስደትንና ሞትን ሳይፈሩ ብዙ ሄደዋል። ሆኖም ይህ የእውነት ወንጌል እሳት ከ70 ዓመታት በላይ አልዘለቀም። ያንኑ መንፈስ ይዞ ወይም ከዚያም ባለፈ የሚያስቀጥል ትውልድ ወራሽ ሆኖ አልተነሳም። የተነሳው ትውልድ እውነትን በራዥ፣ ስደትን ወደ ድሎት የቀየረ፣ ከዘመኑ ነገሥታትና ታዋቂ ሰዎች ጋር መዳራትን የመረጠ፣ በየዋህነትና በእምነት ሰው ሊቀበለው ከሚገባው የእግዚአብሔር ቃል ይልቅ የፈላስፋዎችን አባባል የመረጠ በመሆኑ ቤተክርስቲያን የጨለማው ዘመን ውስጥ እንድትገባ ሆነ።

እግዚአብሔር እንደ ቃል ኪዳኑ የቀድሞውን መልሶ የሚሠራ (Restorer) በመሆኑ ያንኑ የቀድሞውን ወንጌል በመጨረሻው ዘመን እንደገና አበራው፤ እኛም ጋ ደረሰ። ዛሬ ወደ ሽምግልና አንድ አንድ እያሉ በመሄድ ላይ ያሉትን አባቶች ራስን አስክዶ ወንጌሉን አሳወጀ።

ያንን የሚያስቀጥል ትውልድ፣ ወራሽ ትውልድ፣ የቤተክርስቲያንና የእውነተኛውን ወንጌል አደራ እንካ ተብሎ እንደ ኢያሱ፣ እንደ ኤልሳዕ የሚረከብ ከአባቶቹ በበረታ ሁለት እጥፍ መንፈስ የተጀመረውን ሩጫ በድል የሚያስደመድም ወጣት ቤተክርስቲያን ፈለገች፣ ተጠማች፣ የወራሽ ያለህ! አለች።

ከዚህም በተጨማሪ እግዚአብሔርን ለማገልገል ቅንአት ያላቸው ወጣቶች አገልግሎታቸው በኃላፊነትና በመሰጠት (Responsibility & Commitment) በሌላ አባባል አደራን በመቀበል እንዲሆን ትልቅ የቤተክርስቲያን ሸክም ሆኗል።

ቤተክርስቲያን ይህንን ሸክም በመያዝ ከመላው ኢትዮጵያ ከሚገኙ አጥቢያዎች የተውጣጡ ወደ እግዚአብሔር እየተጠጉ ያሉ 4,800 የሚሆኑ ወጣቶችን በማሰባሰብ በ17 ማዕከላት ሕይወታቸው እግዚአብሔር በሚፈልገው አቅጣጫ እንዲሆን በመስከረም ወር 2012 ዓ.ም የመጀመሪያ ሴሚናር ተሰጥቷል።

በመጀመሪያው ዙር በተሰጠው ሴሚናር ታላቅ የሆነ የእግዚአብሔር ጉብኝት እና የበረከት ጊዜ እንደነበር ስልጠናውን ከሰጡ አገልጋዮችና ከተሳታፊ ወጣቶች መረዳት ተችሏል። የሴሚናሩም ዓላማዎች፦

- ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክት (2ጢሞ. 2፥21-22) እንደተገለጠው ለጽድቅ የቆሙ፣ ራሳቸውን ከክፉ ምኞት ለይተው ለበጎ ሥራ የተዘጋጁና ለእውነት የሚቀኑ ወጣቶችን ለማፍራት ነው።
- በኢየሱስ፣ በቤተክርስቲያንና በወንጌል ፍቅር ልባቸው የተያዘ፣ የቤተክርስቲያንን ሥርዓት አክብረው በመታዘዝ እንደ ኤልሳዕ ነገ ላይ በሁለት እጥፍ መንፈስ ሊያገለግሉ የሚችሉ ወጣቶች እንዲፈጠሩ ለማድረግ ነው።
- ምንም እንኳን ለወንጌል ሰውን ለይቶ የመጥራት ሥራ የጌታ ኢየሱስ ቢሆንም ወደ ወንጌል የሚጠሩ ወጣቶች ምን ዓይነት ሕይወት፣ እምነትና አካሄድ መከተል እንዳለባቸውም ለማስጨበጥ ነው።
- ወደ ሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይነት መጠራት የማይደርሱም ቢሆን እግዚአብሔር በእውነት ቃል አስቦ እንደወለዳቸው የእግዚአብሔር ልጆች በየተሰማሩበት በየትኛውም አገልግሎት ለክርስቶስ ኢየሱስና ለቤተክርስቲያን ክብር የሚሆኑ ትውልድ የሚታነጽባቸው የተባረኩ ወጣቶችን በጠማማ ትውልድ መካከል ለማፍራት ነው።
- የዚህ ሴሚናር ዓላማ በምንም መልኩ የሚታዘዙ ወጣቶችን ለመቅረጽ እንጂ በመጋቢ ላይ የሚነሱ አመጸኞችን ለማንቀሳቀስ ወይም መጋቢዎችን ከቦታቸው አውርዶ እነርሱን በቦታቸው ለመተካትም ታስቦ አይደለም። ሆኖም መጋቢዎች በዕድሜም ሆነ በተለያየ ሁኔታ ሲደክሙ ወይም በሞት ሲለዩ እንደ እግዚአብሔር ጥሪና እርሱ በፈቀደው መንገድ ሊተኩ የሚችሉ ወጣቶች ከነዚህ መካከል ሊገኙ እንደሚችሉ ቤተክርስቲያን ተስፋ ታደርጋለች።
- እነዚህን ወጣቶች ወደዚህ ደረጃ የማድረስ (የማብቃት ሥራ ለመሥራት) የየመጋቢዎቻቸው ኃላፊነት መሆኑ ቢታወቅም ይህ ትልቅ ኃላፊነት በመጋቢዎች ላይ ብቻ የሚተው አለመሆኑን በመረዳት ሃገረስብከቱ ይህንን ሴሚናር ለማዘጋጀት ተገዶአል። ■

# አባቶችህን ጠይቅ

# ቃለ ምልልስ ከቢሾፕ ደጉ ከበደ ጋር

✍ እህት ኢየሩሳሌም መዝገቡ

**ለውድ አንባብያን፡-**

የዛሬው እንግዳችን የኢትዮጵያ ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን ዋና አስተዳዳሪ ቢሾፕ ደጉ ከበደ ሲሆኑ በወንጌል አገልግሎት ለ44 ዓመታት የቆዩ የእግዚአብሔር ሰው ናቸው። ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ቃለ ምልልስ ለማድረግ ፈቃደኛ በመሆናቸው በክፍሉ ስም ከልብ እንባርካቸዋለን። ቃለ ምልልሱን አንዳች ሳናንድል እንዳለ ያቀረብንላችሁ ሲሆን በእርጋታና በማስተዋል አንብባችሁ ትምህርት ትወስዱበት ዘንድ በአክብሮት እንጋብዛለን።

**የእውነት ምስክር፡-** በቅድሚያ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ሆነው ስለተገኙ በእውነት ምስክር መጽሄት አዘጋጆች ስም ከልብ አመሰግናለሁ። ተኩረታችን አገልግሎት ላይ ያደረገ ነው። የወንጌል ጥሪ ወደ ህይወትዎ እንዴት መጣ?

**ቢሾፕ ደጉ፡-** የእግዚአብሔር ጥሪ ወደ ህይወቴ የመጣው እኔ በቀጥታ ባላሰብኩበት ሁኔታ ላይ ነው ማለት እችላለሁ። የእግዚአብሔር ጥሪ ወደ ሕይወቴ በመጣበት ጊዜ እኔ ገና ወደ ዩኒቨርስቲ ገብቼ፣ ከዚያ በኋላ ጥሩ ነገር አገኛለሁ፣ ጥሩ ደረጃ እደርሳለሁ ብዬ ለአዕምሮዬ፣ ለስጋዬ መልካምን ነገር፣ ጥሩውን ነገር አልፎም ደግሞ ያ ነገር ለቤተክርስቲያን ይጠቅማል ቢያንስ የተማሩ ሰዎች ገንዘባቸውን ይሰጣሉ የሚል እንዲሁ ቀና አመለካከትም በመያዝ ከዚያም ውጭ ሀገርም በመሄድ እና የመሳሰሉትን በማሰብ ብቻ ጥሩ ደረጃ በመድረስ እራስንም ማሳደግ የቤተ ክርስቲያንም ኩራት መሆን ይቻላል የሚል ነበር የኔ ግምት።

ከዚያም ባሻገር ደግሞ እኔ በተፈጥሮዬም በወቅቱ ተናጋሪ ሰው አልነበርኩም። ስለዚህም እኔን ለሰባኪነት ማጨት/ማሰብ አልችልም፣ ሌላውም እኔን ሊያስበኝ አይችልም። ሆኖም በመጀመሪያ የሆንኩት ነገር ቢኖር እግዚአብሔር ምንም በማላውቀው ሁኔታ ዝም ብሎ ወደ ጸሎት ሕይወት እየገፋኝ መሄዱ ነው። በወቅቱ ዘማች መምህር ስለነበርኩ ሰፊ ጊዜ ነበረኝ። እኔ በጣም ሰብሰብ ያለ የራሴ ጸሎት ከነበረኝ ክልል የጸሎት አርእስቱንም አወጣው። አውጥቶ ስለ ነፍሳት፣ ስለ ቤተክርስቲያን ማደግ፣ ስለ ወንጌል በቃ እያስነባ፣ እንባ እያስፈሰሰ፣ ረጅም ሰዓታት ማጸለይ፣ መጽሐፍ ቅዱስንም ድሮ መዝሙረ ዳዊት ላይ የሚበዛውን ከራስ ጋር እግዚአብሔር ሆይ ጠብቀኝ፣ እርዳኝ፣ መከታ ሁነኝ ከሚለውም አልፎ እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን የሰጠውን ቃል ኪዳኖች ማለትም የማብዛት፣ የማስፋት እና የማሳደግ ቃል ኪዳኖችን ያመጣ ጀመር። ከዚያም ያው ያጸልየኝ ጀመር። ብዙ እንዳነብብ ያስደርገኝ ጀመር። በቃ እያለ እየቀጠለ ሲሄድ መልኩን እየቀየረ ሄደ።

ቀደም ሲል የነበረኝ ውጪ ሃገር ሄዶ የመማር የትምህርት ዕድሎች ስለነበሩ እነዚያን ሁሉ የመጥላት፣ ነገሮች ሁሉ እጅ እጅ የማለት፣ ተመልሶም ዩንቨርስቲ ገብቶ የመማር ነገር ጭልም ማለት፣ የውስጥ ማቅለሽለሽ አይነት እየበዛ ሄደ። እንዴ ምንድነው ይሄ ነገር? እና ቀን በቀን ነገሮቹ እየተለወጡ የማደንቃቸው ነገሮች የማይደነቁ ወደ መሆን እየሄዱ፣ የማላደንቃቸው ነገሮች ደግሞ የማደንቃቸው እየሆኑ፣ እያለ እንዲህ ከመስከረም ወር ጀምሮ እስከ ጥር 20 አካባቢ ድረስ በዚህ ሁኔታ ላይ ተይዤ እግዚአብሔር እንዲህ አያደረገ ከእጄ ሁሉን ነገር ተረከበኝ። ምን ቀረኝ? በቃ የቀረኝ ነገር ቢኖር የተሰፋው ቃል ብቻ ሆነ። መጸለይ፣ ማንባት፣ በቃ ሌላው እንዳለ በሙሉ ከላዬ ላይ ብፈልገው አጣሁት። በዚያ ሰዓት ት/ቤት ገብተህ ተማር ብባል እኔ እንጃ ሁለትና ሁለት አራት ነው ለማለት እስከማልችል ድረስ እስኪመስለኝ ጭንቅላቴ ለሌላው ነገር ባዶ ቅል ሆኗል። ለእግዚአብሔር ነገር ግን አዕምሮዬ እየተከፈተ እዛ ማስተማሩን የገባሁበት ግን በጭንቅ የሚከናወን ሆነ። እግዚአብሔርም በውስጤ እየተናገረኝ እፈልግሃለሁ እያለኝ ወደጭንቀት ሲመጣ ነገሩን ስወስን ጭንቀቱ ለቀቀኝ። ሰላሜ ተመለሰ። ከዚያ በኋላ ለቤተክስቲያን አስታወቅሁ። እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያንም መሰከረላት። በወ/ም ተክሌም በኩል መጣ፤ ሌሎቸም እንዲሁ እግዚአብሔር የጠራቸው ጓደኞቼ ነበሩ። ከእነርሱም ጋራ ደብዳቤ ስንጻጻፍ የእኔን ነገር ለእነርሱ የነሱን ነገር ለእኔ እግዚአብሔር እያሳወቀ እነዚህን ሁሉ ማረጋገጫ እግዚአብሔር አምጥቶ ያው ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ እንግዲህ ላለፉት 44 አመታት አካባቢ ይኸው በእግዚአብሔር እርሻ ላይ እገኛለሁ።

**የእውነት ምስክር፡-** አገልግሎትን በጀመሩ ወቅት ምን አይነት ራዕይ ነበርዎት? ዛሬ ያሉበትን ስፍራ ያስቡት ነበር?

**ቢሾፕ ደጉ፡-** አገልግሎት በጀመርኩበት ጊዜ የነበረው ራዕይ፣ ከእኔም ጋራ አብረው ከነበሩት ሰዎች ጋራ ማለትም በአንድ ወቅት ወይንም በአንድ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጥሪ ከመጣን አገልጋዮች ጋር አንድ አይነት ራዕይ ነበረን ማለት ይቻላል። ከዚያም ቀደም ብሎ ደግሞ በወንጌሉ ስራ ወንድም ተክሌ የነበረው «ነፍሳትን ወደ እግዚአብሔር መንግስት መመለስ» የሚል አንድና ብቸኛ ራዕይ የሁላችንም ራዕይ ነበር። ነፍሳትን ወደ እግዚአብሔር መንግስት የመመለስ፣ ይህንን የሐዋርያትን ወንጌል የማብራት እና ምድረበዳዎች ላይ፣ ወንጌል ያልገባባቸው ቦታዎች ላይ የሚያስከፍለው ሁሉ ተፍሎ አብያተክርስቲያናት እንዲመሰረቱ፣ እንዲተከሉ በዚያ ውስጥ የሚከፈለው

ዋጋ ቢከፈልም ምንም እንደማይቆጭ፤ ያ ነው የነበረው ራዕይ። ይሄ ራዕይ ሁሉንም ማለት ይቻላል ከ ወ/ም ተክሌ ጀምሮ ሁላችንንም የያዘን ራዕይ ነበር። ገና ጅምር ላይ ስለነበርን ጸሎት ቤት የመስራት ራዕይ አልነበረንም፣ ጊዜውም፣ ዘመኑም የጸሎት ቤት ለመስራት የሚያበረታታም አልነበረም። ለማንስ ጸሎት ቤት ይሰራል? ገና ሰው አልዳነምና ከዚህ የተነሳ በቃ መዝሙሮቹ ጭምር ከራእያችን ጋር የተያያዙ ነበር:-

«ኢያለሁ አየዋለሁ፣
በአጭሯ የሕይወት ዘመኔ፣
ጌታ ሆይ ለምኜሃለሁ፣
ሌላው ሁሉ ይቅርብኝና፣
በዝተን አይቼ ልሙት»

የሚልና የመሳሰሉ። መብዛት፣ መስፋት፣ በኢየሱስ ስም ማጥመቅ፣ ወንጌል እዚያም እዚያም ገባ የሚል ነበር፤ በእርግጥ ይህ የእኔ ብቻም አልነበረም። የእኔም፣ የወ/ም ተክሌም ራዕይ ነበር፤ ራእያችን አንድ ነው ማለት ይቻላል።

በዚያ በተጠራንበት ወቅት የሚያስከፍለውን ማንኛውም ነገር ተከፍሎ በቃ ነፍሳት ይዳኑ የሚል ብቻ ነበር የዘወትሩ አሳብ። እኔ እራሴ የወንጌል ጥሪ ተቀብዬ አንድ ተራራ ላይ ሆኜ በእድገት በህብረት ዘመቻ ወቅት አንድ መዝሙር እዘምር ነበር። እንደሁ ጌታ የሱስ «አንድ ይስሃቅ ቢሰጠኝ፣ ዘር የሚያስጠራ ለብዙዎች በረከት መሆን የሚችል አንድ ይስሃቅ!» ለራሱ ብቻ የሚድን አንድ ነፍስ ሳይሆን ሊበዛና ሊሰፋ፣ ሊያድግ የሚችል ነፍስ ቢሰጠኝ በሚል ምኞትና ጸሎት "አሁን ጌታ የሱስ ሆይ እባክህ አንድ ይስሃቅ ስጠኝ" የሚል መዝሙር እዘምር ነበር። ይሄ ነው የነበረው ራዕይ ማለት እችላለሁ። መብዛት...መብዛት...መብዛት!

**የእውነት ምስክር:-** ወደፊት የሚያዩት ነገር ነበር?

**ቢሾፕ ደጉ:-** በእውነት እውነተኛ ሆኖ ለመናገር እንደው በዚያን ወቅት የነበረው ስሜት በጣም ሃይለኛ ጸሎትም ናፍቆትም ቅድም እንዳልኩት ወንጌል ሰፍቶ፣ ቤተክርስቲያን በየቦታው ተተክላ፣ ብዙ ነፍሳት ወደ እግዚአብሔር መንግስት ተጨምረው፣ አልፎ ተርፎ ወንጌል ወደ ሌሎችም ሃገሮች ወጥቶ የሐዋርያት ወንጌል አሸንፎ፣ በርትቶ፣ አይሎ፣ ከማየት ውጪ ሌላ ቅንጣት የሚታይ ነገር አልነበረም። ጸሎት ቤት ሰርተን፣ ይሄ ንብረታዊ የሆኑ ቁሳቁሳዊ የሆኑ ነገሮች የሚል እንኳን ምንም አሳብ አልነበረም። እግዚአብሔር ያንን ነገር ሁሉ ዝግትግት አድርጎት አእምሮንም ለስኖ ልብንም ለስኖ ሙሉ ትኩረትን በዚህ በነፍሳት መዳን፣ መብዛት፣ ማደግ፣ መስፋት፣ የወንጌሉ ማሸነፍ ላይ ነበረ ማለት ይቻላል እይታው። እና በዚህ መካከል ጌታ ኢየሱስ መጥቶ እንነጠቃለን የሚል አይነት እንጂ እንዲህ ተቋማዊ አደረጃጀት ላይ ያተኮረ ነገር አልነበረም።

**የእውነት ምስክር:-** አገልግሎት በጀመሩበት ወቅት ሊሆን ይችላል ወይም በጥልቀት ከገቡበት በኋላ ያጋጠሞት ተግዳሮቶች ምን ነበሩ? እንዴትስ አለፉ?

**ቢሾፕ ደጉ:-** እንግዲህ በአገልግሎት ጅማሬ አካባቢ ላይ አንደኛ ወጣትነት አለ። እድሜም ገና በሃያዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ላይ ነበር። የነበረው ሸክም ነፍሳትን የማግኘት፣ ሰዎችን የማጥመቅ፣ መንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ የማሰብ፣ እነዚህ እነዚህ ነገሮች አሉ። እና መጀመሪያ ላይ የነበረው ተግዳሮት ጥሪው በውስጥ እየተቀጣጠለ የአገልግሎት በሮች አለመኖራቸው ነበር። እሳት ልብ ውስጥ ይነዳል፤ ግን የተከፈተ በር አልነበረም። ወቅቱ ደግሞ የኮሚኒስት መንግሥት ጅማሬ ጊዜ በመሆኑና እኔም ገና ወጣት ስለነበርሁ በአይን ውስጥ የምገባ ነበርሁና ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስም እራሱ ከባድ ነበር። የተደበቀ መሳሪያ ፍለጋ በየቤቱ አሰሳ እየተደረገ ቤቶች ይፈተሹ ነበር። እዛ መገኘቱ እራሱ ሁል ጊዜ ከባድ ነበር። ብቻ ሁሉ ነገር በጣም በጣም የታነቀ እና አስቸጋሪ ጊዜ ነበር።

ግን በዚ በታነቀና ሞት ሞት በሚሸትበት ሁኔታ ውስጥ ጥሪ አለኝ ብዬ ወጥቼ፣ ትምህርትም ተትቶ፣ ለአገልግሎት ደግሞ በር ሳይከፈት ሲቀር ሊኖር የሚችለውን ስሜት መረዳት ይቻላል። ከባድ ነበር። እግዚአብሔር ግን በዚያ የስሜት መጎዳት መካከል የበለጠ የከፋ ጉዳት እንዳይፈጠር ቶሎ ብሎ እኔ ባላሰብኩት ሰዓት እና ጊዜ ወደ ኬንያ ሄጄ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት እንድማር እድል አመቻቸልኝ። ያንን ለወንጌል በር የመዘጋት ጊዜ እግዚአብሔር የትምህርት የማግኘት ጊዜ አደረገው።

ትምህርቱን ጨርሼ ከኬንያ ስመለስ እዚህ ወጣቱ ላይ አትኩሮ ሲካሄድ የነበረው ከባባድ መከራ እና ሞት ጋብ ብሎ፣ እዚህ ጎፋ ላይ ያለውን ግቢ ወንድም ተክሌ ከመንግሥት አግኝቶ፣ በቆርቆሮ አጥር ታጥሮ፣ የቆርቆሮ ሰርቪስ ቤትም ተሰርቶ ነበር። ያን ጊዜ .ወንድም ተክሌ ግንባታው ላይ ሲያተኩር እኔ አዲስ አበባ ላይ ያለውን የወንጌል ማስፋፋት ስራ ጀመርኩ። አሁን የምብሰክበት ቦታ ኖረኝ፤ ህጋዊ ቤትና ግቢም አለ። ቢያንስ ለወ/ም ተክሌ በተሰራው ቤት ላይ ስብሰባ ማድረግ፣ መጸለይ፣ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ፣ የሰዎች መጠመቅ እንደዛ መሆን ጀመረ። በዚያ በኩል የምተጋበትን ዕድል እግዚአብሔር ሰጠኝ ማለት ነው።

እየተቆየ ሲኬድ ወደ ወንጌል ውስጥ የመግባቱ ነገር በእንደዚያ አይነት መፋጠን ስለሆነ የተጀመረው በነበረው መፋጠን እና መጠባበቅ መጠን ውጤት/ፍሬ ስላላገኘሁ በሰይጣን ክስ ጥሪዬን አንዳንድ ጊዜ መጠራጠር እና የውስጥ ውጪ የመሆን ነገር መፈጠር ጀመረ። የውስጥ መታወክ ነገሮችም ነበሩ። እንግዲህ በወቅቱ ሌሎች ሌሎች ጫናዎች፣ የኑሮ ጫና፣ የገንዘብ እጥረት፣ ሌላም ሌላም ነገሮች ከስጋዊ ኑሮ ጋር በተያያዘ ቢኖሩም እነዚያን እኔ ተግዳሮቶች አልላቸውም። ምክንያቱም ገና ጥሪው ሲመጣ አምኜባቸው የገባሁባቸው ስለሆኑ እንደ መደበኛ ኑሮዬ አድርጌ ስለምወስዳቸው ያንን ተግዳሮት ብዬ እኔ አሁን አላስቀምጠውም። ተግዳሮት ብዬ የማስቀምጠው ያለሁት ከስራው ጋራ በተያያዘ ያሉትን ብቻ ነው። ስለዚህ አፋጣኝ የሆነ አንድ Explosion (ፍንዳታ) ተፈጥሮ ሀይለኛ Revival (መንፈሳዊ እንቅስቃሴ) ውስጥ የመግባት ነገር ቶሎ ስላላገኘሁት ክሱ፣ ምኑ፣ የውስጥ ትግሉ እየበዛብኝ ሄደ ማለት ነው። ግን ለዚያም ለውስጥ ትግሉ ለነበረው ጥያቄ ቁጭ አድርጎ ደግሞ የሚያስተምር ሰው አልነበረም። ሁሉም ጀማሪ ነው። ሁለተኛ ደግሞ ሁላችንም የተያዝንበት መንፈስ አንድ ውጤት፣ አንድ Revival/መንፈሳዊ እንቅስቃሴ መምጣት ስለሆነ እንጂ መጠበቅ መቆየትና በእግዚአብሔር ፊት በእምነት መኖር የሚል ማንም የሚያስተምረን አልነበረም። በቃ ሁሉም የኔው ብጤ ስለሆነ ያንን የሚያስተምር ስለሌለ በመላላጥና በመጋጋጥም ቢሆን እግዚአብሔር ይመስገን ጸሎት፣ በጣም ሃይለኛ ጸሎት ስለነበረ ተግዳሮቶቹ ታለፉ።

በምን ታለፉ ቢባል አስተማሪ ባልነበረበት በዚያ ጊዜ ውስጥ እነዚያ ተግዳሮቶች በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ሲቀረብ የሰጣቸው መልሶች ናቸው ያቆሙን። እንደ ምሳሌ አንዱን ብጠቅስ ደስ ይለኛል። አንድ ጊዜ እንደዚሁ በአንድ ከባድ ሁኔታ ውስጥ በጣም ተወጥሬ በጾምና በጸሎት ውስጥ እያለሁኝ ከአስራ አምስት ቀን ጾም ጸሎት በኋላ አንድ ራዕይ አየሁ። ራዕዩን ያየሁት ልክ የጾም ጸሎቱ መጨረሻ ቀን ላይ ነበር። ራዕዩም እንዲህ ነበር። ወደ አንድ ከፍ ወዳለ ጠፈር እሄዳለሁ። ከመሬት ርቄ በጣም ርቄ ... ርቄ...። እና መሬት እንደ ሉል (Globe) እስክትታይ ድረስ። በሰው እጅ የምትያዝ እስክትመስል ድረስ ቁልቁል አያለሁ። ጥልቅ ጨለማ እና አየር ላይ የተንጠለጠልኩበት ከሰማይ አንድ ካቦ ወፍራም ገመድ ይወርዳል። ይወርድና እንደ ሸምቀቆ ሆኖ አንገቴ ውስጥ ይገባል። አንገቴ ውስጥ ገብቶ ልክ አንገቴ ሲገባበት ሰው ገመድ ሲገባበት ሸምቀቆ ከሆነ ሄዶ እስር እንደሚያደርገው እንቅ አድርጎ ያስረኛል። ግን ሲያንቀኝ የመጨረሻ የሚመች ማነቆ ያንቀኛል። እጅግ የሚለሰልስ እና የሚመች ሆኖ ያንቀኛል። ሰው አየር ላይ ተንጠልጥሎ ሲገኝ እጅግ ከባድ ሊሆንበት ሲገባው

ለእኔ ግን የመጨረሻ ልዩ ሆኖ በቃ ምቾት ውስጥ ተንጠልጥያለሁ ማለት ነው። ታቹን ሳየው እጅግ ድቅድቅ ጨለማ ነው። ተንጠልጥዬ ግን እጅግ በጥሩ ምቾት ውስጥ ራሴን አገኘሁት። በዚያ ምቾት ውስጥ እያለሁ ቀና ብዬ ገመዱን ከየት እንደመጣ ለማየት ሞከርኩ። ገመዱ ከየት እንደመጣ አይታወቅም። መጨረሻው ላይ ግን ሁለት ፊደሎችን ሰርቶአል - «ጸጋ» የሚል። ሁለት ፊደሎችን ሰርቶ «ጸጋ» የሚለውን ሳነብብ ገመዱ ተጠማዝዞ የፈጠራቸው ፊደሎች ናቸው። በኋላ "ጸጋዬ ይበቃሃል" የሚል ድምጽ ሰማሁ።

ከዚያ ወደ አዕምሮዬ ተመለስኩኝ። ከተመለስኩኝ በኋላ ለብዙ አመታት ማለት ይቻላል በሚከብደኝ ነገር ውስጥ በሚወጥረኝ ነገር ውስጥ ምቾቴ ሆኖ የኖረው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። በቃ በእግዚአብሔር ጸጋ ተማምኜ በክሱም፣ በምኑም፣ ባለመቻሉም፣ በዚያም ውጊያ ውስጥ የእግዚአብሔር ጸጋ ተሸክሞኛል። እዚያ ላይ ተንጠልጥያለሁኝ። በነበሩ ልዩ ልዩ ተግዳሮቶች ውስጥ ሁሉ ጭራሽ ይህን ጸጋ አልጥልም ብዬ ጸጋው አሻግሮኛል፣ አሳልፎኛል ብዬ አምናለሁ።

ከዚያ ደግሞ ወደ አገልግሎት ሲኬድ ቀጥሎ መቼም ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ ይኬዳል። እየቀጠለ ሲሄድ አገልግሎቱ ሰፋ። አሁን ምን አገለግላለሁ? ከሚለው ጥያቄ ወጥተን ደግሞ በምንና እንዴት አገለግላለሁ? ወደሚለው ተገባ ማለት ነው። ይህን ሁሉ እንዴት አገለግላለሁ? ይህን የሚያስብለው እግዚአብሔርና ቤተክርስቲያን በተለያዩ የአገልግሎት መስመሮች እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ልበለው እና «በፈረሰው በኩል» ሁሉ በየአቅጣጫው መግባት ስለነበረ ነው። በሰበካ ክፍል ሃላፊነትም፣ አንዳንድ ጊዜ በጊዜያዊ መጋቢነትም፣ አንዳንድ ጊዜም በተለያዩ አገልግሎቶች ለምሳሌ በወጣቶች አለ፣ በስነ-ጽሁፉ አለ፣ በመዝሙር ውስጥም አለ፣ በቦርድ ስራ ውስጥ አለ ብቻ በእያንዳንዱ ስራ ውስጥ የምገባበት ነገር መጣ።

በእኔ በኩል ደግሞ እንደ አዲስ የነበረው ነገር በቃ አንድ ወጥ የሆነ አገልግሎት (Ministry) ኖሮኝ ያንን አገልግሎት እየኮተኮትኩ (Cultivate አድርጌ) በጣም ሰርቼበት ለእግዚአብሔርም ለቤተክርስቲያንም ይኸው ብዬ የማስረክበው ወይንም የማሳየው ነገር መሻት በውስጤ አጥብቆ ተፈጠረብኝ። ሆኖም ይህ ነው የምለው ነገር እኔ አልነበረኝም። እኔ በየቦታው፣ በየተቀደደበት፣ በየተከፈተበት ሁሉ በማስተማሩም፣ በመስበኩም፣ በየሁሉም፣ በዚያም በዚህም የምንቀሳቀስበት እንቅስቃሴ እና የኔ ፍላጎት ብዙ ጊዜ በቃ ውስጤ እንዳይመቸኝ አደረገኝ። ይህም ሲባል እኔ በመታዘዝ አምናለሁ።

> ”
>
> **አንድ ሰው በእግዚአብሔር ሲፈተን የሚያልፍበት ወይም ያን ፈተና የሚሻገርበት መንገድ ይለያል...**

እግዚአብሔርንም ቤተክርስቲያንንም በመታዘዝ በጣም ነው የማምነው። ይህ ልክ የመዳን ዶክትሪንን እንደማምነው ያህል ነው የማምነው ማለት እችላለሁ። ነገር ግን ሰው ስለሆንኩኝ በአእምሮዬና በስጋዬ በኩል መቼ ነው እያልኩ ውስጤ የነበረውን ሸክም እና ትንቅንቅ ልበለው ትልቅ ተግዳሮት ነው ያሳለፍኩት።

እንግዲህ አሁንም ተግዳሮቶች ሲባሉ ለኔ ስራው ላይ ካለው ጋር እንጂ ከሌላ ጋር አላገናኘውም። እንዲሁ ለማሳየት ያክል በዚህ በኩል ልጆች አሉ፣ ቤተሰብ አለ፣ ትዳር አለ፣ መብላት አለ፣ መጠጣት አለ፣ ቤት አለ፣ የመሳሰሉት ነገሮች፤ ጤና አለ፣ ድካም አለ። እነዚህ ነገሮችን ሁሉ እንደ ተግዳሮት ሳልቆጥራቸው ከስራው ጋር በተገናኘ ያለውን ብቻ ለማስቀመጥ እሞክራለሁ ማለት ነው። ለማንኛውም እንግዲህ የሰከነ አገልግሎት ፈልጌ ብዙ ለመግፋት ሞክሬያለሁ። ነገር ግን እንደዚህ በብዙ ነገር እንድያዝ የሆንኩባቸውን እግዚአብሔር አልፈቀደም ብዬ መጨረሻ ላይ ሃይለኛ ጉልበት ልጠቀም ወስኜ ፆም ጸሎት ፕሮግራም ይዤ በነገሩ ላይ እየጸለይሁ ሳለሁ፣ የጤናም ነገር እንዲሁ ተያይዞ ያስቸግር ስለነበር አንዳንዶቹን ማስረከብ የምችላቸውን አገልግሎቶች አስረክቤ እራሴን ወደማሰባሰብ ለመምጣት እየተዘጋጀሁ ነበር። እንደዚያ ባለሁበት ወቅት ነበር እንግዲህ አሁን ወዳለሁበት ወደዚህ አገልግሎት መጥቼ እንደገና ወደመበተን እንደገና ወደተለያዩ አቅጣጫዎች ከንፌን እንድዘረጋ አእምሮዬን እንድዘረጋ የሆንኩት። ስለዚህ በየዘመናቱ የነበረው እንግዲህ የአገልግሎቶች ሁኔታ ይህን ነው የሚመስለው። ተግዳሮቶቹም ይህን ይመስላሉ። የታለፈባቸውም ሁሉን እግዚአብሔር በጸጋው አቅም በፈቀደ መልኩ ውስጤ ከተቆጣበት መለስ እያልኩ ውስጤ ካዘነበት መለስ እያልኩ እዚህ ደርሻለሁ።

**የእውነት ምስክር፡-** ሰው በምድር ላይ ሲኖር በልዩ ልዩ ፈተናዎች ሊፈተን ይችላል። አገልጋይ ይህን መሰል ልዩ ልዩ ፈተና ሲያጋጥመው በምን መልኩ ማየት አለበት ይላሉ?

**ቢሾፕ ደጉ፡-** እንግዲህ በአብላጫው አገልጋይም ይሁን ክርስቲያን ትልቁ የሚጠበቅበት ነገር እውነተኛ ክርስቲያን መሆን ነው። መሆን ያለበት እውነተኛና ሀቀኛ፣ ግብዝ ያይደለ (እንደሱ ብለው ይሻላል)፣ ፈሪሳዊ ያይደለ መሆን በጣም ጥሩ ነው። ይሄ የሚጠቅመው ለምንድነው ቢባል ለምሳሌ አንድ አገልጋይ በሰይጣን ሊፈተን ይችላል፤ በእግዚአብሔር ሊፈተን ይችላል፤ በራሱ የስጋ ምኞት ሊፈተን ይችላል። ማንም ክርስቲያን ይፈተናል። በተለይ በሰይጣን ተፈትኛለሁ የማለት አቅም ሊኖረው ይችላል። በእግዚአብሔር ግን ተፈትኛለሁ የማለት አቅም ሊኖረው አይችልም። በስጋዬ ምኞት ተፈትኛለሁ የሚል አገልጋይም ሆነ ምዕመን ብዙ ደፍሮ እንዲህ ለማለት ቅንነቱ ብዙ አይኖርም። ከዚህ የተነሳ መሳሪያዎቹ ይለያያሉና ሃቀኛነቱ ይጠቅማል።

አንድ ሰው በእግዚአብሔር ሲፈተን የሚያልፍበት ወይም ያን ፈተና የሚሻገርበት መንገድ ይለያል፤ ከሰይጣን ሲፈተን ደግሞ የሚያልፍበት መንገድ ከዚያኛው ይለያል፤ በስጋ ምኞት ሲፈተን ደግሞ የሚያልፍበት መንገድ ወይም የሚያሸንፍበት መንገድ ይለያል። በሰይጣን የመጣውን ፈተና በስጋ ምኞት ከመጣው ፈተና አይነት መሳሪያ ተጠቅሞ ልጋጠምህ ቢለው ያ በፍጹም አያስኬደውም። የሰይጣንንም ያው በእግዚአብሔር ከመጣው እንደዚያው ማለት ነው። ስለዚህ የመጀመሪያው ነገር እውነተኛ ሆኖ እነዚህን ሶስት ነገሮች መለየትና በየቦታው በትክክል ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

ስጋው እየፈተነው ከሆነ እውነተኛ ሆኖ ስጋ እየፈተነኝ ነው ብሎ ለይቶ ማስቀመጥ አለበት። ሰይጣን እየፈተነው ከሆነ ደግሞ ሰይጣን እየፈተነኝ ነው ብሎ ማስቀመጥ አለበት። በእግዚአብሔር ደግሞ እየተፈተንኩ ነው ከሚለው ጋር ያንን ደግሞ ለይቶ ማስቀመጥ መቻል አለበት። እውነተኛነት ነው እዚህ ጋ የሚያስፈልገው። ስለዚህ በእግዚአብሔር የመፈተንን ነገር በአብላጫው እግዚአብሔር ከእርሱ በላይ ወይንም ከእሱ ነገር በላይ የምንወደው፣ የምንታዘዘው፣ የምንገዛለት፣ የመሳሳሉትን ላለመኖሩ እግዚአብሔር ማረጋጋጥ ሲፈልግ የሚያመጣቸው ፈተናዎች

ወይም ማረጋገጫ (Check ማድረጊያ) ነው ብለው ይሻላል። ምክንያቱም "እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው"። ለምን? ያ ፈተና የሰጠሁትን ነው የበለጠ የሚወድደው ወይንስ እኔን ሰጪውን? የሚለውን ለማረጋገጥ ሲፈልግ እግዚአብሔር ልጅህን ስጠኝ አለው። ያን ልጅ ስጠኝ የማለት አባባል መጽሐፍ ቅዱሳችን "እግዚአብሄርም አብርሃምን ፈተነው" ይላል። ስለዚህ ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር ፈተና የሚባለው የእግዚአብሔር Check ማድረጊያ ነው።

ለምሳሌ አሁን ዘዳግም ውስጥ ሲናገር "እግዚአብሔር በልብህ ውስጥ ያለውን ያውቅ ዘንድ፣ ይፈትንህም ዘንድ እነዚህን አርባ አመታት መና አበላህ" ይላል። እና ይህ ማለት ያንን ሲበሉ እግዚአብሔርን ምን እንደሚሉት እግዚአብሔር ቆሞ ይታዘባል ማለት ነው። ከልባቸው ምን እንደሚያወጡ ያን ጊዜ ልባቸውን ይፈትሽበታል። የእግዚአብሔር ፈተና የሚለውን አባባል በዛ መልኩ ደርበብ አድርጌ ወይንም ሰብሰብ አድርጌ ላስቀምጠው እችላለሁ። ስለዚህ ያ ፈጽሞ የተለየ እግዚአብሔር የሚጠይቀው እግዚአብሔር የሚያየው ማለት ነው።

በሰይጣን ያለው ፈተና የሚታገለው ነው። ይህ ቅድም ከተጠቀሰው የስጋ ምኞት ፈተና ጋር በጣም ኅረቤታም ነው። የተቀራረበ ስለሆነ አንዳንድ ጊዜ አንዳንዱ ተደርቦ ተመሳሳይ ይመስላል። የሰይጣን ፈተና የሚባለው በቀጥታ ወይንም በተዘዋዋሪ እንደየመንገዱ አገልጋይ ከሆነ በአገልጋይ መንገድ፣ ምዕመንም ከሆነ በምዕመን መንገድ እየተቃወመ የሚታገለው ነገር ማለት ነው። የሚቃወመው ሲባልም ልክ ሰይጣን ኢየሱስ ክርስቶስን በፈተነው ጊዜ የተጠቀመባቸውን የፈተና አይነቶች ማለት ነው። ይዘታቸው ያው ነው።

የስጋ ምኞት ፈተና የሚባለው ግን መነሻው ከምንድነው የሚለውን ያ ሰው ከስጋ ፍላጎቱና ከስጋ ምኞቱ፣ ስጋ ሊደርስበት ከሚሻው ነገር ተነስቶ የሚሆኑ ፈተናዎች ናቸው። እነዚህን መቋቋም የሚቻለው ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል ነው። በእግዚአብሔር ቃል የተጻፈውን እየጠቀሱ "ልክ አይደለህም፣ በእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ተብሎ ተጽፎል፣ ይህንን እንዲህ አታድርግ ተብሏል፣ ይህንን እንዲህ አትይ ተብሏል፣ እንደዚህ አትመኝ ተብሏል፣ ይህን የሚያደርጉ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግስት አይገቡም ተብሏል" እያሉ አንድ ሰው ለራሱ እየሰበከ ከዚያ ውስጥ መውጣት አለበት። አንዳንድ ሰው ያ የስጋ ምኞት ሲመጣበት ያን የሚደግፍ ጥቅስ ይፈልጋል። ለማመንዘር ተፈትኖ ከሆነ "ዳዊት ተፈትኖ ነበር ምን ማድረግ ይቻላል" ሊል ይችላል። ነገር ግን እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል እያለ ስጋውን የሚገዛበት መንገድ ነው መከተል ያለበት። በሰይጣን ደግሞ ሲፈተን ሰይጣንም እንዲሁ በእግዚአብሔር ቃል ፊት ለፊት በመቃወም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በመቃወም የሚወገድ ነው።

በኢየሱስ ክርስቶስ የሆነውን ፈተና ግን ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ነው የምናልፈው ማለት ነው።

**የእውነት ምስክር:–** አንድ ሰው በእግዚአብሔር መጠራቱን በምን ያውቃል?

**ቢሾፕ ደጉ:–** "በእግዚአብሔር የተጠራ አገልጋይ" በሚለው መጽሀፍ ላይ ተቀምጦአል። ነገር ግን አጠር አድርጌ ከዛው ለመጥቀስ ልሞክር። የመጀመሪያው ነገር ውስጣዊ ምልክት አለ፣ ውጫዊ ምልክት ደግሞ አለ። አንዱ ምልክት ምንድነው ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ቅርርቦሽ ይበዛል፤ በጣም ይበዛል። ይሄ ቅርርቦሽ እጅግ በጣም ይበዛል። ቅርርቦሽ ማለት ምን ማለት ነው?

የውስጥን ስናይ ለምሳሌ እግዚአብሔር ሙሴን ሲጠራው መጀመሪያ ወደ እሳቱ ነው የቀረበው። ሙሴ በፊት ሽክም ነበረው። ስለ እስራኤል የሚያውቀው ነገር ቢኖር ቀንበሩን ነበር፤ ባርነቱን። በእውቀት ደረጃ እናትየዋ ያሳወቀችው አለ። ነገር ግን እግዚአብሔርን የማሽተት ነገር 80 ዓመት ሙሉ ከዛ አካባቢ አልነበረም። በሙሉ የነበረው ነገር ከሰው ጋር የተያየዘ ነበር። እንደገናም ደግሞ በእይታው የሚደርስባቸውን መከራ አየ ይላል መጽሃፍ ቅዱስ። ያንን አየ። ስለ እግዚአብሔር የሚያውቀው እውቀት አለ፣ የሰውም ዕውቀት አለ። እግዚአብሔርን ግን አላየም። ስለዚህ የመጨረሻ ጅምር የሚጀመረው/የሚነሳው እግዚአብሔርን በማየት ላይ ነው። እግዚአብሔርን ማየት የሚባለው ነገር ምንድን ነው? ከእግዚአብሔር ጋር የግል ልምምዱ ለየት ያለ ሲሆን ነው።

ሙሴ ከዚያ በፊት ወደ እግዚአብሔር አይጸልይም ማለት አይደለም። አሁን ለየት የሚያደርገው ነገር ጫማህን አውልቅ እያለው፣ ድምጹን እያሰማው፣ ምንድነው ይሄ ቁጥቋጦ የሚቃጠለው፣ የሚነድደው ግን የማይቃጠለው እስቲ ይሄንን የእግዚአብሔርን ራዕይ ልይ ነው ያለው። እግዚአብሔር የሚያሳየውንም ነገር ልይ ነው ያለው። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ያው ተናገረው ማለት ነው። የሚያየው አለ፤ የሚሰማው ነገር አለ፤ ጫማህን አውልቅ ተባለ፤ መሬቱ የተቀደሰ ነው አለው። እኔ እርግጠኛ ነኝ ጫማውን አውልቆ እግሩ ያን መሬት ሲነካው የሆነ ስሜት እንዲሰማው ፈልጓል እግዚአብሔር። ያኛው ከተፈጥሮ በላይ የሆነ እግዚአብሔር ብቻ በሰው ህይወት ውስጥ በደም ስሮቹ፣ በህዋሳቶቹ ውስጥ በቃ የሚሰማን ስሜት መፍጠር ነው።

ለምሳሌ:- አሁን በሰላም ሃገር እንዲያው ኢሳያስ እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት ነው የሚለው። ሲታይ የሆነ ነገር ነው የሚደረገው። "አንደበቴ የረከሰብኝ፣ እንደዚህ የሆንኩኝ እኔ በጣም ራሴን ተጸየፍኩ" አለ። ከዚያ በኋላ እሳት መጣ፤ ነካው፤ ከዚያ በፊት እነዚህን አይነት ልምምዶች አልነበሩም። የነዛ ሁሉ ነገሮች ውጤት እግዚአብሔር ማንን ልላክ? ሲለው እኔን ላከኝ አለ። እና ከእግዚአብሔር ጋር ያለ የግል ልምምድ ውስጥ ሰውየው አስቦ አይደለም የገባው። ፕሮግራም አውጥቶ እግዚአብሔር እንግዲህ አሁን ስለሚጠራኝ ጾም ጸሎት ልያዝ ብሎም አይደለም። እግዚአብሔር ግን ፕሮግራም ውስጥ ሙሴን ቅድም እንደጠቀስነው በጎቹን ሊያሰማራ በሄደበት ስፍራ ላይ እግዚአብሔር ተገናኝቶ ያንን ነገር አደረገ። እኔ ጥሪን በተለይ ከዚህ ጋራ በጣም በጣም አያይዘዋለሁ።

የኤልሳዕንም ነገር ስንመለከት ያ የኤልያስ መጎናጸፊያ ሲነካው ማን ይሁን አያውቅም ግን ነካው። አያውቅም ግን ወዲያው ቀንበር ሰባብሮ፣ በሬዎቹን አርዶ ከዚያ መጎናጸፊያ ጀርባ የእግዚአብሔር መንፈስ የእግዚአብሔር እጅ የዚህን ሰው ሁለንተና ነክቷል። ያን ሁሉ እስኪያስደርሰው ድረስ ነክቷል። እንዲህ የሚነካ የእግዚአብሔር እጅ አለ። በየትኛውም ጊዜና ሁኔታ የተነካውን የእግዚአብሔር ሰው ጠቅሰን ብንናገር ይህንን ነገር እናገኘዋለን። ስለዚህ ይሄ ትልቁ ክፍል ነው ብዬ አስባለሁ። ይህንን እንደ መጀመሪያ አድርጌ የምቆጥረው የዚህኛው ስለሚበረታ ነው እንጂ ያኛው ትልቅ አይደለም ለማለት አይደለም።

ሁለተኛው በሰው ውስጥ የሚኖር የነፍሳት ሸክም፣ የእግዚአብሔር ስራ ረሃብ፣ የጽድቅ ሸክም፣ የወንጌል ሸክም እነዚህ ሸክሞች ናቸው። እነዚህ ሸክሞች ግን በዚህ መደገፍ አለባቸው። አሁን ካልኩት ከግል ልምምድ ጋርም መደጋገፍ አለባቸው። ምክንያቱም ሙሴ ሸክም ነበረው፣ ራስን መካድ ነበረው፣ የሚጠበቀው ማን ነው? እግዚአብሔር መጥቶ ከዚህ ከዚህ ከተካደው ነገር ጋር ከዚህ በቃ እኔ እነዚህን ሰዎች ልታደግ ከሚለው ጋር የእግዚአብሔር መንካት አብሮ ሲጨመር ነው ውጤት የሚመጣው። እነዚህ ሁለት ነገሮች አብረው ይሄዳሉ። ስለዚህ ቅድሚያ የእግዚአብሔር መንፈስ ሲነግረው ነው። አለበለዚያ ውጤቱ አይኖርም። ያ የነካው እግዚአብሔር እኔ ከአንተ ጋር ነኝ ካለው ከዚያ ሸክሙ ጋር፣ ከዚያ ቅንዓቱ ጋር ስራ ይሰራል።

ውጫዊ:- የምንለው ደግሞ ጸሎቱ ማለት ሰውዬው በማይቆጣጠረው ሁኔታ ጸሎቱ

ቅድም ያልኩት እራስን መካዱ የሚሰራው ስራ፣ የሚያገኘው ደሞዝ፣ የሚኖረው ኑሮ እነዚህ  ነገሮች በሙሉ እንዳለ መሬት ላይ ሲወድቁ ምን ነካኝ? እያለ ምን ሆንኩኝ? እያለ ምንም ስሜት የለኝም ምንም እና በደመ-ነፍስ ስራ የሚሄድ፣ በደመ-ነፍስ የሚበላ፣ በደመ-ነፍስ የሚጠጣ ትዝታውና ነገሩ በዚያ በእግዚአብሔር ነገር ሙሉ በሙሉ ሲያዝ ይህቺ ነገር አላት።

**የእውነት ምስክር:-** አንድ የክርስቶስ ወንጌል አገልጋይ በማህበራዊ ህይወቱ ማለትም ከቤተሰቡ ጋር እንዲሁም ከሌሎች ሰዎች ጋር ከሌላው ምዕመን በተለየ ምን አይነት ግንኙነት ማድረግ አለበት ብለው ያስባሉ?

**ቢሾፕ ደጉ:-** ይህ እንግዲህ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ነገር ነው። ሃላፊነትም ነው። እና ሶስት ነገሮች ከፊቱ ይኖራሉ አንድ አገልጋይ:- እግዚአብሔር አደራ የሰጠው አለ፣ እግዚአብሔር አደራ ያልሰጠው አለ፣ ደግሞ ማህበራዊ ህይወትም አለ ማለት እችላለሁ። ከዚህ የተነሳ መጽሐፍ ቅዱሳችን የቤተሰብን ነገር ሲናገር ለቤተሰቡ የማያስብ ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሁሉ ይልቅ የሚከፋ ነው ይላል። በሌላም ቦታ ለአንድ አገልጋይ ከተቀመጡ መመዘኛዎች ውስጥ በዋናነት የተቀመጠው ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም ማስተዳደር እንደሆነ ይገልጻል። ካልሆነ የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን እንዴት ሊያስተዳደር ይችላል? ብሎ ቤተሰብን በአግባቡ ማስተዳደር ዋና ነገር እንደሆነ ይናገራል። ስለዚህ ትልቅ ሃላፊነት አለበት እንዲህ ማለት ይቻላል። ከምዕመናን በላይ ለቤተሰቡ ትልቅ ሃላፊነት አለበት። ይሄን ሲባል ሃላፊነት ሲባል እንግዲህ ትንሽ ጥንቃቄ ያስፈልገው ይሆናል።

ሃላፊነት ሲባል የእግዚአብሔርን ሃላፊነት ወይም እግዚአብሔር የሰጠው የአገልግሎት ሃላፊነት ባልዘነጋ መልኩ፤ አካሄዱንና መስመሩን ባልቀየረ መልኩ መሆን አለበት ለቤተሰቡ ያለበትን ኃላፊነት የሚወጣው። ለምሳሌ ልጆች፣ ሚስት፣ በቤተክርስቲያንም ሆነ በአገልግሎት የሚያገኘውን ገንዘብ አልበቃ ብሏቸው እነርሱ ካላቸው ፍላጎት የተነሳ ሚስት ከምትፈልገው ፍላጎት ልጆችም ከሚፈልጉት ፍላጎት የተነሳ ጉሮሮውን አንቀው ይሄ ገንዘብ አይበቃንምና አንተ ይህን አገልግሎት ትተህ ስራ ሰርተህ በቂ ገንዘብ አምጣልን። ዋናው የቤተሰብ አገልግሎት አለብህ ቢሉት ይህን አያካትትም። ባለው ጊዜ፣ ባለው ገንዘብ፣ እግዚአብሔር በባረከው መጠን እንጂ በሌለው አይደለም። ባለው ልብ፣ ባለው አእምሮ፣ ሁለንተናውን ሰጥቶ ባለው ነገር፣ እግዚአብሔር በሰጠው ክልል ውስጥ ሆኖ ያን ቤተሰብ ወይንም ያን ህይወት ጊዜ የመስጠት፣ የማስተናገድ፣ የሚቻለውን ሁሉ በማድረግና በመንከባከብ ጥሩ የእግዚአብሔር ሰዎች አድርጎ የመቅረጽ ኃላፊነት አለበት፤ ይሄ መታየት ያለበት ነው።

ወደ ሌላው ማህበረሰብ በሚኬድበት ጊዜ ማህበረሰባችን እንኳን ለሰባኪ ለሌላውም ምዕመን "ቢቻላችሁስ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ" ይላል (ሮሜ 12:18)። "ለምን ቢቻላችሁስ?" አለ። የማይቻልበት ሁኔታ አለ ማለት ነው። ምክንያቱም እንግዲህ እድር ውስጥም፣ ምን ውስጥም፣ እዚያ ውስጥም እዚህ ውስጥም ልግባ ካለ ሰውዬው የውጪው ማህበረሰብ የሚችለው እሁድ ነው፤ ስለዚህ እድሩ እሁድ ነው፣ የቤተሰብ ጉባኤው እሁድ ነው፣ ስለዚህ ሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች እሁድ ናቸው የሚከናወኑት። እርሱ እንግዲህ ጸሎት ቤቱን ትቶ ወደዛው ሊዞር ነው ማለት ነው። አገልጋይ በሚችለው ሁኔታ ላይ ነው የሚሳተፈው። ለሰው ነውና የሚመሰከረው፣ የተከፈተ በር ማለት በዛ ባለ ግንኙነት ላይ ስለሆነ በሚችለው አጋጣሚ ሁሉ ምንም በር መዝጋት የለበትም። ሆኖም የእግዚአብሔር የእግዚአብሔርን ሲያስብ የቤተሰቡንም ነገር በተቻለው መጠን ማሰብ አለበት።

ለምሳሌ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 12 ላይ አንድ በጣም ጠቢብ የሆነ ሰውዬ ወንድምየው ርስቱን አልሰጥ ብሎኛል ስላለው አሁን ይህ ኢየሱስ ነብይ ነው ንግግሩ በጣም ከባድ ነው ማንንም መርታት ይችላል እና እርሱን ሽማግሌ አድርጌ (ሁነኝ) ብዬ ብልክ በቀጥታ ርስቴን አገኛለሁ ብሎ ኢየሱስ ክርስቶስን እባክህን ሽምግለኝ፣ ወንድሜ ርስቱን እንዲያካፍለኝ አለው። ይህ እንግዲህ ማህበራዊ ግንኙነት ነው። ግባ ምን አለበት ሽማግሌ ሁን ዝም ብለህ ብቻ ስብከት የእግዚአብሔር መንግሥት ምን ያደርጋል? ቢለው እኔ ለዚህ ነው ወይ ተልዕኮዬ? ማን ሾመኝ? ለዚህ በእናንተ ላይ ፈራጅ እንድሆን ማን ሾመኝ? አለው። ስለዚህ በማህበረሰቡ መካከል ተወዳጅ ስለሆንን ብቻ ወይም ተጽዕኖ መፍጠር ስለሚቻል ቢቃ በጣም ጥሞት ደስ ብሎት ሰዎች ስለፈለጉት ለዛ እራሱን የሚያዘጋጅ ከሆነ ለእግዚአብሔር መንግስት ተሻሚ ነገር ለእግዚአብሔር ስራ ተሻሚ ነገር ስለሚያዘጋጅ የተደነቀ መስሎት ነገ ወደሚዋረድበት ደረጃ ይሄዳል። የእግዚአብሔር ስራ ደግሞ በእጁ ላይ ይወድቃል። ውጤታማ አይሆንም። ስለዚህ ሌላው ላይ ደርበብ አድርጎ ይኖራል ማለት ነው። በአጭሩ ይህን ይመስላል።

**የእውነት ምስክር:-** ሰው ለወንጌል አገልግሎት ከተጠራ በኋላ፣ የእግዚአብሔርን ድምጽ አረጋግጦ ማገልገል ከጀመረ በኋላ ከአገልግሎቱ በተጓዳኝ ሌሎች ስራዎችን ቢሰራ እንደ እግዚአብሔር ቃል እና እንደ ቤተክርስቲያን መመሪያ ችግር ይኖረዋል? በሙሉ ጊዜና በከፊል ጊዜ ለሚያገለግሉ አገልጋዮችም ጭምር እንዲጠቅም አድርገው ቢያብራሩልን?

**ቢሾፕ ደጉ:-** ይህ እንግዲህ ከበድ ያለ ጥያቄ ነው፤ አመላለሱም ትንሽ ሚዛን መጠበቅ ያስፈልጋል። አንደኛ ይህንን ሰው በእግዚአብሔር ከተጠራ በኋላ ጥሪውም በእግዚአብሔር ከተረጋገጠ በኋላ እና አገልግሎቱን ከጀመረ በኋላ በተጓዳኝ ሌላ ለኑሮው የሚጠቅመውን ስራ መስራት ይችላል ወይ? የሚለው ይህን የሚወስነው በእርሱና በጠራው አምላክ መካከል ያለው ግንኙነት ነው እላለሁ። እንደመጀመሪያ መካሪ እነርሱ መካከል ያለ ነገር ነው። ለምን ቢባል በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ "ሰው ሁሉ እግዚአብሔር እንደጠራው ይመላለስ" የሚል ስላለ ነው። ለምሳሌ:- በሐዋርያው ጳውሎስ ጥሪ እና በሌሎቹ ሐዋርያት የጥሪ አይነት መካከል እንኳን ልዩነት እንዳለው እናያለን። አንዳንዱ ላይ አሁን ሐዋርያው ጳውሎስ ምን ይላል:- እንደውም የእነርሱ ነገር ትንሽ ያስቀናው እህት ሚስታችንን ይዘን ልንወጣ ሙብት የሌለን እኔና በርናባስ ነንን? ስራ የመተውስ? እያለ የሚናገረው ነገር አለ። ስለዚህ ከጠሪው ጋር ያለ ግንኙነት ይመስለኛል። ምክንያቱም ሰውየውን በህግ እንዲህ ብትሆን ማለት አይቻልም። ምክንያቱም በማመልከቻ አልተጠራም። እግዚአብሔር ጠርቶኛል ብሎ ነውና የቀረበው ያው እግዚአብሔር እንዴት እንደጠራው ከርሱ ጋራ ቢነጋገሩና ቢጨርስ መልካም ነው። እንደ መነሻ አድርገን የምናነሳው ይህንን ነው።

ሁለተኛው አንድ ሰው መጀመሪያ ላይ ጥሪ መጥቶልኛል ሁሉን ትቼ አገለግላለሁ ብሎ በእግዚአብሔር ፊት በእግዚአብሔርም ህዝብ ፊት በቤተክርስቲያን ፊት ቃል ገብቶ ያንን ቃል ማፍረስ የለበትም እላለሁ። ምክንያቱም ቃልን ማፍረስ «የተሳልከውን ስዕለት» ማፍረስ ነው። ጸጉራቸውን እንኳን የማይላጩ ናዝራዊያን ጸጉራቸውን እንዲላጩ አይፈቀድላቸውም። ለእግዚአብሔር በዚያ ሁኔታ ራሳቸውን ስለለዩ ማለት ነው። በዚያ ሁኔታ ራሳቸውን ለመለየታቸውም ለእግዚአብሔርም ተናግረዋል። ቀድሞ ለቤተክርስቲያንም ተናግረዋል። በአደባባይ በተቀባበትም ቀን በእግዚአብሔርም ህዝብ ፊት ተናግሮ ያንን ቃል ወደ ኋላ አጥፎ ስራ እፈልጋለሁ ማለት ይሄ ባትሳል ይሻልሃል እንደማለት ነው። ባትናገር ይሻልሃል ነው። ይህንን ያመጣው ምንድን ነው? ኋላ ላይ ይህንን ምን አመጣው? ሐዋርያው ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች ሲጽፍላቸው "በመንፈስ ጀምራችሁ እንዴት በስጋ ትጨርሳላችሁ?"ይላል።

በእንዲህ አይነት መንፈስ የጀመረው ነገር መሃል ላይ እግዚአብሔር መጥቶ ለዚሁ በኋላ ላይ ለቀረው ሰውዬ ጥያቄ ይጠይቀዋል። እዚህ ላይ አንድ ምስክርነት ስለ ራሴ ብሰጥ ጥሩ ይመጣል ብዬ አስባለሁ። እኔ በ1968 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ለስራ ወጥቼ ሐረር ላይ እያለሁኝ በዕድገት በኅብረት ዘመቻ ውስጥ ባለሁበት ስፍራ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር ጥር ወር ከብዙ ትግል በኋላ ውሳኔ ስወስን እነዚህን ጥያቄዎች በቃ ሁሉን ትቼ፣ ትምህርትም ትቼ፣ ስም ትቼ፣ መላ ህይወቴን ለእርሱ አስረክቤ፣ ብሞትም ልሙት ብዬ ወስኜ ደብዳቤ ለቤተክርስቲያን እዛው እያለሁ ልኬያለሁ። ቤክርስቲያንም ተቀበለች። ከዚያም በኋላ ጨርሼ መጣሁ። አገልግሎትም ጀመርኩ። ፈተናውና የኑሮ ትግሉ ከባድ ነበር። ቤተሰብ ዘመድ በሙሉ ተማምኖበት የነበረ ሰው ሆኖ ፈተናው ከባድ ነበር። ወቅቱም ገና አብዮት የተጀመረበት ሰዓት ነውና የሚያወላዳ ነገር አልነበረም። እዚያ ውስጥ ጓደኞቼም ለመኑኝ፤ በጣም ብዙ ለመኑኝ። “እየው አሁን ጊዜው እንደዚህ ነው፤ እያሯሯጠ የሚያሰራም የአገልግሎት ስራ የለህም፤ ቢያንስ ቢያንስ ማታ እንኳን አስተምር እና ከምትራብ ማታ አስተምረህ በዛች እንኳን በምታገኘው ገንዘብ ጥቂትም ቢሆን መኖር ትችላለህ” የሚል አስተያየት ሰጥተውኝ .ለሁለት ሰዓታት የማስተምርበትን አመቻቹ።

እኔ ባደግሁበትም አስተዳደግ በተለይ በመንፈሳዊው የሰው ነገር መንካት፣ ከሰው ገንዘብ ማግኘት፣  ሰውም የለም ያኔ አስራትም ምንም የለም ከዚህ የተነሳ እኔ የሰውን ፊት ለምን አያለሁ? ሰውስ እኔን ለምን ተራብ ለምን ተጠማ ይላል? ስለዚህ እነዚህ ልጆች ያሉኝን ነገር በቃ እሺ ልበላቸው ብዬ ወስኜ ለማንኛውም ወ/ም ተክሌን ላማክር ብዬ በጠዋት ሄድኩ። ስሄድ እንደምን አደርክም አላለኝም። “ወ/ም ደጉ ድሮ ምን አስቤ ነበር መሰለህ? የሰው አስራት ከምበላ ከሰው ገንዘብ ከምቀበል የማታ ትምህርትም ቢሆን አስተምሬ በዚያ እራሴን አስተዳድራለሁ ስል “እኔኮ ከሰው እጅ ገንዘብ እያገኘህ እንድታገለግል የማደርግህ ትሁት እንድትሆን ብዬ ነው።” አለኝ። እግዚአብሔር ይመስገን! እስኪ ሜክሲኮ እንሂድ” አለኝ አቤት ጌታ ሆይ! እንደዚህ አይነት አነጋገርም አለ ብዬ ወዲያው በጣም ደንግጬ ልቤ ፈሶ  ያሰብኩትን ነገር ሳልነግረው ማረኝ ጌታ የሱስ ሆይ ሁለተኛ እንዲህ አይነት ነገር አይለምደኝም ብዬ ያችን ንግግር እግዚአብሔር በሱ አንደበት አድርጎ አናግሮ ከዛኛው ሁኔታ መለሰኝ የሚል አለ በህይወቴ የተሰራ ነገር።

አንዳንድ ጊዜ በአእምሮአችን የምናስባቸው ነገሮች አሉ፤ ማለት እኔ አንድ ጊዜ በአእምሮዬ ያሰብሁት ስጸልይ ከመዋል ውጪ የሚሰበክበት ነገር የለም፣ የሚሰበክበት ቸርች አዳራሽ የለም። ስለዚህ ምን አለበት ብሰራ በሚል በአእምሮ በሂሳብ የተደረገ ነገር ነው። ዛሬ ላይ ሆኜ ግን ሳስበው የእግዚአብሔር የአገልግሎቱ መጠን በጣም እንዲታይለት ክብሩ በጣም ትልቅ መሆኑ እንዲታይለት ወንጌልን እንደ አንድ ትርፍ ስራ እንዲሰራ አይፈልግም እግዚአብሔር ከጠራ ማለት ነው። በትርፍ ስራ የሚሰሩ ሰዎች፣ ጊዜ የሚሰጡ ሰዎች፣ የሚያገለግሉ ሰዎች አይኖሩም አላልኩም። ሰው እግዚአብሔር እንደጠራው ይመላለስ ነው። ግን እግዚአብሔር ለይቶ የሚጠራቸውን ሰዎች የሚጠራቸው የአገልግሎቱን ክብር ለማሳየት ነው። እንደ አንድ ማስተማሪያ የማየው ነገር ምንድነው ወደ ሐዋርያት ጥሪ ስንመጣ ሐዋርያት ወይም ደቀመዛሙርቱ ስራ ነው የነበራቸው፤ የራሳቸው የግል ኩባንያ ልንለው እንችላለን። ያ የአሳ ማጥመድ

እንደጠቀስኩት ተጠሪውና ጠሪው ምን ነበር የተነጋራችሁት? የሚለው ወሳኝነት አለው የሚል ነው።

**የእውነት ምስክር:–** እንደ እግዚአብሔር ቃል የወንጌል አገልጋይ ውጤታማ ነው ወይም ፍሬያማ ነው የሚባለው ምን ደረጃ ሲደርስ ነው?

**ቢሾፕ ደጉ:–** አንድ እግዚአብሔር የጠራው አገልጋይ ውጤታማ ወይም ፍሬያማ ነው የሚባለው አንደኛ እግዚአብሔር ሰውዬውን በጠራው የጥሪ መስመር ላይ ነው መታየት ያለበት። እግዚአብሔር ሰውዬውን በጠራው ጥሪ መስመር ላይ ነው ዳኝነቱ መሰጠት ያለበት፤ ወይም ደግሞ ፍሬያማ አይደለም ውጤታማ ነው ውጤታማ አይደለም የሚለው የሚታየው እዛ ላይ ነው። አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ አገልጋዮች ተጠርተዋል፤ ነገር

**”**

**አንድ ሰው መጀመሪያ ላይ ጥሪ መጥቶልኛል ሁሉን ትቼ አገለግላለሁ ብሎ በእግዚአብሔርና በህዝቡ ፊት ቃል ገብቶ ያንን ቃል ማፍረስ የለበትም እላለሁ።**

ስራ አንደኛ ሌሊት ነው የሚጠመደው፣ ቀን አሳ የለም። ከዚያ ሌሊት ይጠመዳል፤ ጠዋት ተጣጥቦ ወደ ገበያ ይሄዳል። ቀን መረባቸው የተቀደደ ካለ መሰፋፋት ምናምን እንደዚህ ካልሆነ በስተቀር ምንም ስራ የላቸውም።

አንዳንድ ጊዜ ሙሉ ጊዜውን ለአገልግሎት የተጠራ ሰው ሲባል ስራው በጣም ሰፊ ስለሆነ ተብሎ መተርጎም የለበትም። በእንደዚያ አይነት አተረጓጎም ብቻ መተርጎም የሉብንም። የአገልግሎቱ ጥሪ ክብር በጣም ትልቅ ሆኖ እንዲታይለት እግዚአብሔር ስለሚፈልግ ጊዜ እያላቸውም ቢሆን ይጠራቸዋል። ከፈለገ ደግሞ አንድ ሳምንት ዘግተው ሁለት ሳምንት መዝጋት ሲችሉ የራሳቸው ማናጀር እራሳቸው ሆነው እያሉ መረባቸውን አስጥሎ አሳ አጥማጅ እንዲሆኑ አደረጋቸው። ሙሉ ትኩረታቸውን እዚህ እግዚአብሔር የጠራቸው ጥሪ ላይ፣ ሰው ማጥመድ ላይ ብቻ እንዲሆን ስለፈለገ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ባሉበት መጀመሪያ ይህን ተረድቶ ለወጣ ሰው ራስን ማጠላለፉ ለጢሞቲዎስ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደጻፈው ‹‹የሚዘምተው ሁሉ ለጦር ያስከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም›› እንዳለው ይመስለኛል። ሆኖም መጀመሪያው ላይ

ግን የጥሪያቸውን አቅጣጫ ሳያውቁት ይቀራሉ። እንደ ምሳሌ ብጠቅስ:– አንዱ መጋቢ ሆኖ ተጠርቶ ሊሆን ይችላል፤ ያለበት አገልግሎት ደግሞ ወንጌላዊ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ወንጌላዊ ሆኖ ተጠርቶ ይህንን እርሱ ባለመለየት መጋቢ ሆኖ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ እዚያጋ በተጠራበት መስመር ላይ ሆኖ ውጤታማ ወይም ፍሬያማ ባይሆን ፍሬያማ አይደለም ይሄ ሰው ብሎ መደምደም ትንሽ አስቸጋሪ ነው። መጀመሪያ ይሄ ሰውዬ የተጠራበት ቦታ ላይ ነው ወይ ያለው?  የሚለውን ማረጋጋጥ ይመስለኛል።

ሆኖም የተጠራበትን ትክክለኛ ቦታ አውቆና ተረጋግጦ እዚያ የጥሪ መስመር ላይ ውጤታማ ነው ፍሬያማ ነው የሚባለው ከዚህ ነው የሚጀምረው። ከምንድነው የሚጀመረው በቅድሚያ በጀመረበት ራስን የመካድ፣ በመንፈስ የመመራት፣ ለኢየሱስ ተሰጥቶ የመኖር ህይወት፣ ህይወቱ እስከ መጨረሻ መቀጠል፣ መሃል ላይ ሌላ አቅጣጫ የማይይዝ፣ ሌላ መስመር የማይሄድ፣ ወደ ስጋዊ ነገር የማይሄድ፣ ሌላም ሌላም ነገር ውስጥ ሳይገባ፣ ራስን የመካድ ለኢየሱስ ተሰጥቶ ራስን በካደ በተዋረደ ህይወት እስከመጨረሻ የሚቀጥለው ከሆነ ፍሬያማነትና ውጤታማነት ሲጀምር

ከሰውየው ነው ሚጀምረው፤ ይሄ ነው ደምበኛ የመጀመሪያ መለያ።

**የእውነት ምስክር:–** ወዲያው ውጤት ላያይ ይችላል እንደጀመረ?

**ቢሾፕ ደጉ:–** አዎን! ጸንቶ፣ ግራ ቀኝ ሳይል፣ አስተሳሰቡን ሳይቀይር ወደ ስጋዊነት ሳያደላ ወደ ሌላ ሌላ ነገር ሳይገባ በጣም የጸና መንገድ ይዞ ሲቀጥል ይሄ ሰውዬ በጣም ውጤታማ ነው ይባላል። ለምን? አንድ ሰው ዝብርቅርቅ ያለ ህይወት ኖሮት የጀመረበትን መሃል ላይ እያጠፋ እያበራም፤ የተዘበራረቀ ህይወት ኖሮት የሰራቸው ስራዎች በእግዚአብሔር ጸጋና ምህረት እግዚአብሔር እርሱን አይቶ ሳይሆን ጸጋውን አይቶ በሰራው ስራ ውጤት ያለው ስራ ተሰርቶ ሊሆን ይችላል። ይሄ ሰውዬ ውጤታማ ነው፣ ፍሬያማ ነው ማለት ግን ያስቸግራል። የእርሱ ህይወት የማይከተለው ውጤታማነትና ፍሬያማነት ፍሬያማነት አይባልም።

ይሄ በጣም መታየት አለበት። ውጤታማነት የሚባለው ላይ ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች ከእነርሱ ውጪ በሆነ የተሰራ ስራ ላይ በጣም ሲፎክሩና ሲመኩ፣ እኔ ያሳየሁት ፍሬ፣ እኔ ያሳየሁት ውጤት፣ እኔ ያስገኘሁት ነገር ሲሉ ይሰማል። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር የመስራት እነርሱን ትቶ እነርሱን ገፍቶ ሂዱ፣ ዞር በሉ ብሎ እነርሱን ትቷቸው እግዚአብሔር የመስራቱን ነገር እንጂ የሚያሳየን እግዚአብሔር በእነርሱ የመስራቱን አያሳየንም። እግዚአብሔር እነርሱን ትቶ ነው የሚያሳየን። ስለዚህ ይህንን ውጤታማነት ብለው የሚፎክሩበት እና የሚመኩበት ሰዎች አሉ። እንግዲህ ውጤታማትና ፍሬያማት የሚለውን ነገር እኔ የምረዳው ለየት ባለ ሁኔታ ነው። ስራው ላይ ብቻ ሳይሆን ሰውየውም ላይ ሰሪውም ላይ ማለት ነው። ይሄ የሰውየው ነው።

ወደ ስራው ስንመጣ ደግሞ በዚህ በተጠራ አገልጋይ አገልግሎት ቤተክርስቲያን ታንጻና አንድ ሆና አድጋ ከነበረችበት ደረጃ በእርሱ ጸጋ ከፍ ብላ ሲታይ ይሄ ውጤታማነት ይባላል። ከዚያ ከፍ ያለው ፍሬያማነት ደግሞ በእርሱ ጸጋ ተጽዕኖ ፈጣሪነት እንደእርሱና ከእርሱም የተሻሉ ሰዎች ሲፈጠሩ እነርሱን ደግሞ አሳድጎ ለአገልግሎት ሲያበቃ እዚያ ላይ ደግሞ አይቆምም። ትንሽ ከፍ ሲል ከዚያ ፍሬው የጎላ ነው፤ ይሄ አለቀ ተብሎ የሚባለው ያንን ደግሞ እንዲህ ያደረሰውን ስራ ተመልሶ እርሱ ያላፈረሰው ከሆነ ይሄ ነው ፍሬያማነት የሚባለው። ይሄ ደግሞ ወደ ዝርዝር ሲኬድ በጣም ብዙ ነው። እርሱ ራሱ ያላፈረሰው ከሆነ የሚባለው አሁን ሁለት ሴቶች ልጅ ወልደው ነበር ይባላል በሰለሞን ፊት የቀረቡት። እና ብዙ ጊዜ በዳኝነቱ ላይ ነው የምናየው ጥበቡን። ሁለቱም ሴቶች ግን ብናያቸው አንዷ ልጇን ጨፍልቃ የገደለች ነች ተኝታበት። አንደኛዋ ደግሞ ያሰረቀች ነች። ስለዚህ ሁለቱም ሰነፎች ናቸው። መውለድ አለ፤ የወለዱትን ደግሞ መግደልም አለ፣ ማሰረቅም አለ። ስለዚህ ቢጸናለት የሚለው ነገር ምንድነው ሌላ ሳይሆን እግዚአብሔር የሰጠውን አገልጋዮች አሰልጥኖ አገልግሎት ውስጥ አሰማርቶ ከዚያ በእነርሱ ሳይቀና የእነርሱን መንፈስ ሳይሰብር ስራውን ሳያፈርስ አጽንቶ ከቆመ ያ ሰው ስኬታማ ነው ይባላል።

**የእውነት ምስክር:–** በዚህ የክርስቶስ መምጫ ዋዜማ ላይ ያለ የወንጌል አገልጋይ በምን አይነት ራዕይ ሊጓዝ ይገባል ይላሉ? አያይዘውም ከዘመኑ ጋር የሚመጡ የዘመኑን ተግዳሮቶች እንዴት ማለፍ እና እንዴት ማሸነፍ አለበት? በአጠቃላይ በዚህ በመጨረሻው ዘመን አገልጋዩና አገልግሎቱ እንዴት ይሁን ይላሉ?

**ቢሾፕ ደጉ:–** ይህ እንግዲህ ብዙ የተለመደ አይነት የዘመኑ አጠያየቅ ይመስለኛል። እኔ ደግሞ ከተለመደው መልስ ወጣ ያለ መልስ ብሰጥ ጥሩ ነው ብዬ አስባለሁ። ያም ምንድነው ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንትና ዛሬም እስከ ለዘላለም ያው ነው። እኛ ነን እንጂ ስለ ዘመን የምናወራው ኢየሱስ ትላንትም ኢየሱስ ነው ዛሬም ኢየሱስ ነው ነገም ኢየሱስ ነው። ያው ነው። ከእርሱ ዘመናት አልተሰወሩም፣ ከእርሱ አንዳንድ ከአገልግሎት ጋር የተያያዘ ምሳሌ ልስጥህና:– አሁን ሙሴ የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ ካወጣ በኋላ የነበረው አገልግሎት የእርሱ ዘመን ነው። የእርሱ ተግዳሮቶች ነበሩ። የኤርትራ ባህርን መሻገር አለ፣ የምግብ ነገር አለ፣ የውሃ ነገር አለ፣ ብዙ ነገሮች አሉ። መንገድ ላይ አታልፉም ከሚሉ ከእነርሱ ጋር መጋጠምም አለ። የሰዉም ወደ ግብጽ እንመለስ ማለት አለ። እነዚህን እነዚህን ሁሉ ተግዳሮቶች እየተጋፈጠ ያለ አገልግሎት ነበር ያለው።

በዚያ ውስጥ እግዚአብሔር የተናገራቸው ነገሮች አሉ። ስርዓቱን፣ ፍርዱንና ቃሉን አሰምቶአል። በሙሴ በኩል ያም ለትውልድ የሚተርፍ ሆኖ ተቀምጦአል። በኋላ እርሱ ካለፈ በኋላ ኢያሱ መጣ። ኢያሱ ሲመጣ የእርሱ ዘመን ደግሞ አለ። የእርሱ ዘመን ተግዳሮት ከሙሴ ዘመን ተግዳሮት ይለያል። የሚገርመው ነገር ግን ኢያሱን እግዚአብሔር በሙሴ ዘመን ካስቀመጠው በኋላ ሌላ ተግዳሮት ሲገጥመው ኢያሱን "ከሙሴ ጋራ እንደነበርኩ ከአንተ ጋርም እሆናለሁ፣ አልጥልህም አልተውህም እና በሙሴ የተነገረህን ቃል አጥብቀህ ያዝ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል እና ከዚያ እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ" ነው ያለው። ምንም ችግር የለበትም። ይህንን ይዞ ነው የሄደው እና የእርሱ ዘመን ተግዳሮቶች ቢኖሩም ዋናው ትልቁ ነገር ያ የትላንትናው እግዚአብሔር ዛሬም ከእርሱ ጋር ከሆነ ይህንን ደግሞ ያሻግራል ማለት ነው።

**አገልጋይ ጸንቶ፣ ግራ ቀኝ ሳይል፣ አስተሳሰቡን ሳይቀይር ወደ ስጋዊነት ሳያደላ … በጣም የጸና መንገድ ይዞ ሲቀጥል ይሄ ሰውዬ በጣም ውጤታማ ነው ይባላል።**

ይሄ ማለት የአገልጋይን መሰረታዊ መርህ ሳንተው ሌላም አይነት መርህ ሳናመጣ ልክ እግዚአብሔር ለኢያሱ ሌላ ነገር ሳይሆን ያችኑ የሙሴን አካሄድ ተከተላት፣ ከቃሌ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ፈቀቅ አትበል፣ እኔ ከአንተ ጋ እሆናለሁ እዚያ ላይ ብቻ ተጠንቀቅ ያለውን መከተል ማለት ነው። ያንኑ የመጀመሪያውን መሰረት ያለውን፣ አንድ አገልጋይ መሆን ያለበትን፣ አንድ አገልጋይ ሊጓዝበት የሚገባውን አጓጓዝ የተቀየረ መስሎህ በአንተ ዘመን የተቀየረ መስሎህ ሌላ ነገር አትፈልግ፤ ሌላ ምርምር ውስጥ አትግባ። ያንኑ ይዘህ ሂድ። ለወንጌል የተጠሩ ሰዎች ለምሳሌ ሐዋርያት እነ ጴጥሮስ፣ እነ ጳውሎስ እነ አብርሃም እና ሌሎችም ከነቢያትም ከአዲስ ኪዳንም የተጠሩ ሰዎች የአጠራር መንፈስ አንድ ነው።

ይገርምሃል! አንድ ነው። እግዚአብሔር ከአንድ አገልጋይ የሚጠብቀው ነገር አንድ ነው። ያንን ይዘህ ሂድ ነው። ዘመኑ ቢቀያየርም፣ ከዘመኑ ጋር ተግዳሮቶች ቢቀያየሩም ዋና የሆነውን ይኼኛውን ይዘህ እስከሄድክ ድረስ እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፣ እኔ ደግሞ ከአንተ ጋር ያለሁት እግዚአብሔር ፈተናዎችህ ሁሉ የዚያኛው ዘመን አይነት ባይሆኑም እነዚህን ሁሉ ያንተን ፈተናዎች ሁሉ ደግሞ አሻግርሃለሁ፤ አሳልፍሃለሁ፤

የምትሻገርበትን መንገድ ደግሞ እኔ ሹክ እልሃለሁ፣ እነግርሃለሁ፣ አስተምርሃለሁ፣ እመክርሃለሁ። ነገር ግን ያንን የመጀመሪያውን አንድ አገልጋይ ሊሄድበት የሚገባውን የጸሎት ህይወት፣ የጾም ህይወት፣ ከእኔ ጋር የመቀራረብ ህይወት፣ ከቃሉ ጋር ተጣብቆ የመኖር ህይወት፣ ከእኔ ጋር በትህትና የመሄድና የመታዘዝ ህይወት፣ እነዚህና በዚህ መጽሃፍ ላይ የተቀመጡ ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ለአንድ የተጻፉ አይደሉም። ለኋለኛው ዘመን የማይሆኑ ሆነው አይደለም የተጻፉት።

ስለዚህ በኋለኛው ዘመንም ሁሉ እነዚህን እስካደረግህ ድረስ ያኔ ድል የሰጠሁህ እግዚአብሔር አሁንም በዚህ ዘመን ላሉ ተግዳሮቶች ድል እሰጥሃለሁ ነው የሚለን። ስለዚህ እኔ በጥቅሉ የምለው ነገር ያለሁት ምንድነው በአሁኑ ዘመን ያለ አገልጋይ ፈተናው የፈለገ ነገር ይሁን ሌላ የሚደምረው የሚቀንሰውን ነገር ትቶ ያንኑ የድሮውን መንገድ የአንድ አገልጋይን ህይወት፣ የአንድ አገልጋይን ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት፣ የአንድ አገልጋይን ከቃሉ ጋራ ያለውን ትስስር፣ የአንድ አገልጋይን የመታዘዝና የትህትና ህይወት እነዚህን በጣም ትልልቅ ቁም ነገር ያለባቸውን ጉዳዮች ይዞ እስከሄደ ድረስ የዘመኑ ፈተና ምንም ሊያመጣ አይችልም ብዬ በአጭሩ ብመልሰው ይሻለኛል።

**የእውነት ምስክር:–** አይቼው ልሙት የሚሉት ነገር ምንድነው? የህይወት ግብዎ ምንድነው?

**ቢሾፕ ደጉ:–** እኔ የምለው በእርግጥ ሊሰፋ ይችላል። ነገር ግን ጠበብ አድርጌ ‹‹አይቼው ልሙት›› የምለው ነገር ቤተክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ የእግዚአብሔር ሰዎች እዚህ ምድር ላይ ተንቀሳቀሱ ከሚባልበት ዘመን ጀምሮ እግዚአብሔር ያኔ ገና ላልዳነው ግን ሊወልዳት ላሰባት ቤተክርስቲያን በምሳሌ ወይም በጥላ መልክ ይናገረው፣ በቅኔ መልክ ይናገረው፣ ሊያደርሳት ያሰበው፣ ቤተክርስቲያንን ሊያጎናጽፋት ያለውን ነገር፣ ነቢያትን ሲያስጮህ ኖሮአል። አንዳንዶችን ከዚያ በጣም ከቁጥር በላይ የሆኑ በእውነት እነዚህ ለቤተክርስቲያን ይሆናሉ ወይ ተብሎ የማይገመቱ ነገሮችን ከማይገመቱ መካከል የመጨረሻ በጣም በጣም አነስተኛ መጠን፣ እንደው እኔ እንኳ እንደውም በጣም ከቁጥር በታች በሆነ የመቶኛ ድርሻ ነው እያንዳንዱ ያለቀሰ ትውልድና ነቢይ የእግዚአብሔር ሰው ያየው። ስለዚህ እየተከመረ ሌላ ትውድም ሲመጣ እግዚአብሔር ነገሩን አሁንም እየጨመረ ቆይ መጀመሪያ የተናገርኩትን መቼ ፈጸሙኩትና ሳይል ግን አሁንም እየጨመረና እየተናገረ ነው ያለው። ቃል ኪዳኑን አሁንም እየጨመረና እየተናገረ ከዛች ውስጥ ሐዋርያትም የተወሰነችውን አነስተኛ ድርሻቸውን አግኝተው ሌላው ጸሎት እየተከመረ ቃል ኪዳኑም እየተከማቸ ሄዶ እኛ ጋር ደርሶአል። መጨረሻው ዘመን ላይ ነው ያለነው።

ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ለቤተክርስቲያን የተነገሩ ቃልኪዳኖች ሁሉ መፈጸም ይኖርባቸዋል። በመንግስተ ሰማያት የቃል ኪዳን ፍጻሜ እንቅስቃሴ አይኖርምና። እዚሁ አልቆ ነው የሚኬደው። በተለይ በሐዋርያት ስራ ምዕራፍ 3 ላይ የተነገረው ቃል በጣም ሃይለኛ ነው። ይኸውም:– “እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ የተናገረው፣ ነገር ሁሉ እስከሚታደስበት ዘመን ድረስ ሰማይ ይቀበለው ዘንድ ይገበል›› ይላል። እነዚያ ሁሉ እየተጠራቀሙ ተከማችተው የኖሩ ቃሎች በሙሉ ታድሰው፣ ማለት እንደ አዲስ የሚፈጸሙ ሆነው ወይም ደግሞ በቃ ህያውነታቸውና ተጨባጭ ሆነው እስኪታዩ ድረስ ኢየሱስ ሰማይ ላይ ቁጭ ብሏል ማለቱ ነው። እርሱ የሚመጣው እነዚያ ቃላት ተፈጽመው ሲጠናቀቁ ነው። ስለዚህ እነዚህን በጣም አስደናቂ የመጨረሻ ዘመን የመታደስ፣ ህዝብ ወደ ቤተክርስቲያን ወደ ጽድቅ ወደ እውነተኛው ወንጌል መጉረፍ፣ የመጣው ሰው ደግሞ በጽድቅና በቅድስና ተውጦ፣ የፊት መጨማደድ ወይንም እርኩሰት ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይኖርባት ቅዱስና ያለ ነውር የሆነች ቅድስት ቤተክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ እንደተባለው ኢየሱስ የመጣበት የመንፈስ አስራር፣ የጸጋ አሰራር፣ የቃሉ አሰራር፣ የጽድቅና የተአምራት፣ ሰውን የመለወጥ፣ የማጠብ፣ የማንጻትና የማጥራት አሰራር በኃይል ተንቀሳቅሶ ቤተክርስቲያን ለሰማይ የተዘጋጀች እንድትሆን ይሄ የኔ የመጨረሻ የልቤ እረፍት ነው የምለው።

**የእውነት ምስክር:–** አሁን በማገልገል ላይ ላሉ ወይም ነባር አገልጋዮች እንዲሁም ወደፊት ለሚጠሩ አገልጋዮች ያስተምራል የሚሉት የህይወት ተሞክሮ ካለ...?

**ቢሾፕ ደጉ:–** ማለት ምስክርነት ነው?

**የእውነት ምስክር:–** ማለቴ እንደ መርህ የሚቀመጥ

**ቢሾፕ ደጉ:–** እሺ ከዚህ ቀደም ብዬ ከተናገርኩት ጋር የተያያዘ ነገር ነው የሚሆነው በአብላጫው። በአሁኑ ዘመን የምንኖር አገልጋዮችም ሆንን ምዕመናን በልዩ ልዩ መረጃዎች የመናወጥ ወይም የመዋዠቅ ሁኔታ ይታይብናል። ትናንትና አምነን አጻልየን ጸልየን የነበርንበትን ነገር እግዚአብሔር አንድ ነገር አሳይቶን፣ ከቃሉም ላይ ማረጋገጫ ሰጥቶን የሰበክንበትን ነገር በዘመኑ ሁኔታ በሚዋዥቅ የዚህ አለም የተለያየ መረጃና ዕለት በዕለት በሚለዋወጡ ነገሮች ምክንያት ዝግ ማድረግ አለ። ትናንት የቀናንለትን ነገር ዝግ ማድረግ፣ ማቀዘቅዝ ‹‹አይ እንደዛ ብዬ አምኘ ነበር አሁን ግን አይመስለኝም›› ብለን መጣል፣ እንደገና ደግሞ እግዚአብሔር በሆነ ሰዓት ላይ ያመጣልንን ያንን ነገር ሰብከነው ፀልየን ያመንንበትን እግዚአብሔር ይሰራል ብለን አምነንበት ሰውን አነቃቅተን እያለን አለም በምታመጣው ደግሞ ወሬ በሆነ ንግግር፣ በሆነ ሁኔታ ደግሞ አሃ ለካ እንደዚህ አይደለም ብለን ያንን ነገር ደግሞ መልሰን እየጣልነው የምንሄድበት ነገር ‹‹ይቁም!›› ብዬ እንደ አዋጅ እናገራለሁ።

እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር፣ ተስፋ የገባልንን ነገር፣ በመጨረሻው ዘመን እያደረገ ላለው ነገር እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር የእግዚአብሔር ቃል ማሰሪያ በሰጠን ነገር አለም ምንም ትበል፣ ምንም ትሁን፣ ምንም አይነት አዋጅ ታውጅ፣ ምንም አይነት ኢንፎርሜሽን ይንቀሳቀስ፣ ፈፅሞ ለዚያ ተንበርካኪዎች ወይም ለዚያ ነፍስ ወዲያና ወዲህ የምንንሳፈፍ ሳንሆን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ይዘን ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር ሊያደርሳት ወዳለው አቅጣጫ ዝም ብለን እንቀጥል። እንባስበት የሚል መልዕክት ነው ያለኝ። እነዚህ ሁሉ ምስክሮች እንደደመና በዙሪያችን ካሉልን ሲል እየመሰከሩልን ያለው ነገር አለ ማለት ነው። ስለዚህ ዘመን ላለንበት ነገር በሐዋርያት እየተመሰከረልን፣ በእምነት ጀግኖች መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባሉት እየተመሰከረልን ጀሮአችን ሲሰማው፣ እየተመሰከረ ያለውን በእርሱ እየበረታን ቶሎ የሚከብበንን ኃጢአት አስወግደን የእምነታችንን ራስና ፈፃሚውን እየሱስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን ሩጫ መሮጥ ነው የሚያስፈልገን። ይህ ዘመን መክሊቱ ኢንፎርሜሽን ነው። እግዚአብሔር የሚናገረው/የሚሰጠው ነገር አለው፣ አለምም እንዲሁ አላት። ያን ደግሞ አለም የሚሰጠውን የሚሰጠው እግዚአብሔር የሚሰጠውን ለማስጠፋት ነው። ሰለዚህ እኛ ድምፅን ለይተን በጎቹ ድምጼን ያውቃሉ ስለሚል ድምጹን ለይተን፣ የእግዚአብሔር ድምፅ ላይ ሙጭጭ ብለን እግዚአብሔር ተናግሮአል ብለን የምንቀጥልበት ነው። እና ሁልጊዜ እንድ አይነት መሀላ ላይ እንቅፋቶች ይመጣሉ። እኛ እንጥላለን፣ እንደገና ደግሞ እግዚአብሔር ይመጣል፤ እንደገና ደግሞ ይናገራል። አንድ ሰሞን ደግሞ እንበረታታለን፤ ከዚያ ደግሞ አለም ድብልቅልቋን ታመጣለች። ከዚያ ደግሞ ያ እኛ ላይ ተጽዕኖ ይፈጥራል። እንዲህ እየሆነ ይህን ጉዞ መቀጠል አንችልም። እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ተናገረ፣ እኔም ይህን ብቻ ሰማሁ፣ ኃይል የእግዚአብሔር ነው። ■

# መንፈሳዊ ህይወት

# መንፈሳዊ ህይወት ለመንፈሳዊ አገልግሎት

ከቄስ ካሳሁን ዓባይ | ከዳንግላ አጥቢያ

እግዚአብሔር የመጀመሪያ የሆነውን ሰው አዳምን ፈጥሮ በገነት ሲያኖረው በገነት ውስጥ ለአዳም የተሰጠው አገልግሎት እንደነበር ዘፍ. 2፥15 እንዲህ ይነግረናል፥-*“.....እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔደን ገነት አኖረው።”* አዳም በገነት ሲኖር የሚኖርባትን ገነትን እንዲጠብቃትና እንዲያበጃት አገልግሎት ተሰጠው፤ ለአዳም በገነት አገልግሎት ብቻ ሳይሆን የተሰጠው ያንን አገልግሎት የሚያገለግልበት የህይወት ብቃት እንዲኖረው ደግሞ ህግ ተሰጠው። *“እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡- ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና”* (ዘፍ. 2፥16-17)። አዳም በኤደን የተቀበለውን አገልግሎት ስኬታማ የሚያደርግለት የተሰጠውን ህግ በመጠበቅ በገነት መኖር ሲችል ብቻ ነበር፤ ይህን ህግ መጠበቅ ሲሳነው ግን የገነትን አገልግሎት ብቻ ሳይሆን በገነት የመኖርንም መብት ጭምር ተነጠቀ (ዘፍ. 3፥22-24)።

እውነተኛ በሆነች የክርስቶስ ቤተክርስቲያንም ከሐዋርያ እስከ አስተማሪ እንዲሁም ለቅዱሳን የተሰጡትን ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ጨምሮ ለእያንዳንዱ እንደ ጥሪውና እንደ አቅሙ የተሰጡ አገልግሎቶች እንዳሉ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል ። (ኤፌ. 4፥11-13፣ 1ቆሮ. 12፥27-28፣ ማቴ. 25፥14-18) እነዚህ መንፈሳዊ አገልግሎቶች ፍሬያማ የሚሆኑት ደግሞ መንፈሳዊ የህይወት ብቃት ባላቸው አገልጋዮች መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ጨምሮ ያስገነዝበናል።

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ለአገልግሎቱ የጠራቸው አገልጋዮቹ አገልግሎቱን ብቻ ሳይሆን አደራ የሰጣቸው ለተቀበሉት አገልግሎት የሚመጥን መንፈሳዊ ህይወት እንዲኖራቸውም ጭምር ነው። *“ፊተኛይቱም ደግሞ የአገልግሎት ስርዓትና የዚህ ዓለም የሆነው መቅደስ ነበራት። . . . ይህም እንደዚህ ተዘጋጅቶ ሳለ፥ ካህናት አገልግሎታቸውን እየፈጸሙ ዘወትር በፊተኛይቱ ድንኳን ይገቡባታል፤”* (ዕብ. 9፥1-6)። በብሉይ ኪዳን መቅደስና በመቅደሱ የሚያገለግሉ ካህናት አሉ፤ የሚያገለግሉ ካህናት የአገልግሎቱን የሥራ ዝርዝር ብቻ ሳይሆን የተቀበሉት አገልግሎቱ የሚገለገልበትን የቅድስና ህይወት እንዲኖራቸው የሚያደርግ መንፈሳዊ ህግጋትን ጭምር ነው። ከእግዚአብሔር ዘንድ ሙሴ ቃሉን ተቀብሎ የተሰጣቸውን የአገልግሎት ዝርዝር በዘሌዋውያንና ዘኍልቁ መጻህፍት ላይ ሲያስታውቃቸው፣ አገልግሎቱን የሚያገለግሉ ካህናት ደግሞ ምን ዓይነት ህይወት ሊኖራቸው እንደሚገባም ተጽፎአል። የተለያዩ የአገልግሎት ዓይነቶች የነበሩት የመቅደስ አገልግሎት በውስጡ ላሉት መንፈሳዊ አገልግሎት የሚመጥን መንፈሳዊ ህይወት ሲኖር ብቻ አገልግሎቱ ይሰምራል (ዘሌ. 21፥1-24፤ዘኍ. 4፥1-33)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ በአገልግሎታቸው ከእግዚአብሔር ቅጣትን የተቀበሉ ካህናትንና ልዩ ልዩ አገልጋዮችን ስንመለከት በአብዛኛዎቹ የአገልጋዮቹ ህይወት ሲበላሽና የሚነቀፍ ህይወት ሲኖራቸው ነው። ለዚህም እንደ ምሳሌ የዔሊ ልጆች የሆኑትን አፍኒንና ፊንሐስን እንመልከት። በዘመኑ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ የሚያገለግሉት እነዚህ ካህናት በአገልግሎት ላይ እንደነበሩና ሕዝቡም በእነርሱ እየተገለገለ እንደነበር ይታወቃል፤ ሆኖም የካህናቱን ህይወት በተመለከተ ቃሉ እንዲህ ይገልጸዋል፥- *“ዔሊም እጅግ አረጀ ልጆቹም በእስራኤል ሁሉ ላይ ያደረጉትን ሁሉ፥ በመገናኛውም ድንኳን ደጅ ከሚያገለግሉት ሴቶች ጋር እንደ ተኙ ሰማ። እርሱም አላቸው፥- ስለ ክፉ ሥራችሁ ከዚህ ሕዝብ ሁሉ ሰምቻለሁና ስለምን እንዲህ ያለ ነገር ታደርጋላችሁ? ልጆቼ ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ኃጢአተኛ በማድረጋችሁ ስለ እናንተ የደረሰኝ ወሬ መልካም አይደለምና ይህ አይሆንም። ሰውስ ሰውን ቢበድል እግዚአብሔር ይፈርድበታል ሰው ግን እግዚአብሔርን ቢበድል ስለ እርሱ የሚለምን ማን ነው? እነርሱ ግን እግዚአብሔር ሊገድላቸው ወድዶአልና የአባታቸውን ቃል አልሰሙም።”* (1ሳሙ. 2፥22-25)። የዔሊ ልጆች በሚነቀፍ ህይወት ሆነው የሚያገለግሉት አገልግሎት ራሳቸውንም ህዝቡንም ከመከራ አላዳነም፤ እንዲያውም የቃልኪዳኑ ታቦት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሴሎን እንዲለቅና ዳግም ወደዚያ ስፍራ የመመለስ እድል እንዳይኖረው በማድረግ በህዝቡ ላይ በደልን አድርሰዋል። (ኤር. 7፥12-14፣ 26፥6-9)

የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት በዔሊ ልጆችና በመቅደሱ አገልጋዮች ኃጢአት ምክንያት ከተማረከ በኋላ በእስራኤል ላይ ነቢይ እንዲሆን ያስነሳው ሳሙኤል እስራኤልን ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ሲመራ የእግዚአብሔር ጉብኝት በምድሪቱ ላይ እንዲሆን ያደረገው በነቢዩ ሳሙኤል ህይወት የሚታየው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው አካሄድ አምላኩን ደስ ስላሰኘ ነው። በቀጣይ ትውልድ በሳሙኤል ልጆች ይህ ሁኔታ ባለመቀጠሉ ጉቦኛና ለገንዘብ የሚሳሳ ልብ ያላቸው ልጆች በመሆናቸው እስራኤልን አስመርረዋል (1ኛ ሳሙ. 8፥1-5)።

በአገልጋይ ህይወት ውስጥ የሚታይ ሥጋዊነት ወይም ለኃጢአት የሚመች አካሄድ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠሩ አይቀርም። መንፈሳዊ አገልግሎትን እግዚአብሔር የመሰረተው በመንፈሳዊ ህይወት ብቃት ላይ ነው። ያለ መንፈሳዊ ህይወት አገልግሎት፣ አገልግሎቱን የሰጠውን እግዚአብሔርንም፣ ተገልጋዩን የእግዚአብሔርን ሕዝብ አይባርክም።

ናዝራዊው ሶምሶን እግዚአብሔር ፍልስጥኤማውያንን ለመበቀል ያስነሳው የእግዚአብሔር ሰው ነው፤ ሶምሶን የእግዚአብሔርን መንፈስ በኃይል እየተሞላ ታላላቅ ተዓምራቶችን ሲያደርግ የነበረ ሰው ቢሆንም፣ ኃይል የተቀመጠበትን ናዝራዊነቱን ወይም ለአምላኩ ብቻ የተለየበትን ህይወት ሲጥልና ከተለያዩ ሴቶች ጋር በመሴሰኑ ምክንያት ኃይሉንና አገልግሎቱን አጥቷል። የአገልግሎት ጸጋዎች ያለመንፈሳዊ ህይወት ቀጣይነት ያለው የአገልግሎት ፍሬ ከማፍራት ይገደባሉ። ሶምሶን ከእግዚአብሔር በሚወርድለት ኃይል ፍልስጥኤማውያንን ቢበቀልም ፍልስጥኤማውያን ደግሞ ሕይወቱን በኃጢአት እንዲረክስ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ተበቅለውታል (መሳ. 14 ፥16)።

በአምላኩ የተወደደውና እንደ ልቤ የተባለው ዳዊት ለጥሪውና ከአምላኩ ለተቀበለው አገልግሎት ፍሬ ያየባቸውን ስኬቶች ስንመለከት በህይወቱ ውስጥ ይታይ የነበረው የእግዚአብሔር ፍርሃት ያለበት የህይወቱ ፍሬ ውጤት ነው። *"ዳዊትም በአካሄዱ ሁሉ አስተውሎ ያደርግ ነበር እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበረ። ሳኦልም እጅግ ብልህ እንደ ሆነ አይቶ እጅግ ፈራው። ነገር ግን በፊታቸው ይወጣና ይገባ ስለ ነበረ እስራኤልና ይሁዳ ሁሉ ዳዊትን ወደዱ"* (1ኛ ሳሙ. 24፥16-17)። ዳዊት በሕዝቡ ፊት ሲወጣና ሲገባ በሕዝቡ ይታይ ነበር፣ የሚታየው የዳዊት ህይወት በፊታቸው የሚወጣውንና የሚገባውን ሕዝብ የሚማርክና የሚያስደስት፣ ነገሮችን ሁሉ አስተውሎ በማድረግ የሚታወቅ ብልህ ሰው ነው። ዳዊት በህይወቱ ያለው መንፈሳዊ ልምምድ ከሳኦልና ከሌሎችም ከሚደርስበት በደል ራሱን ጠብቆ የእግዚአብሔርን አሳብ እንዲያገለግል አስችሎታል።

*"... እንዲህም ሆነ ዳዊት ይህን ቃል ለሳኦል መናገር በፈጸመ ጊዜ፥ ሳኦል፦ ልጄ ሆይ ዳዊት፥ ይህ ድምፅህ ነውን? አለ ሳኦልም ድምፁን ከፍ አድርጎ አለቀሰ። ዳዊትን አለው። እኔ ክፉ በመለስሁልህ ፋንታ በጎ መልሰህልኛልና አንተ ከእኔ ይልቅ ጻድቅ ነህ።"* ሳኦል ለዳዊት እንደመሰከረለት ከእኔ ይልቅ ጻድቅ ነህ ብሎታል፤ ዳዊት በላዩ ላይ የፈሰሰውን የአምላኩን ቅብዓት ጽድቅን በመከተልና የጽድቅን ህይወት በመኖር ለድሆች በጽድቅ እየፈረደና የተበደሉትን በማጽናናት የወደቁትን በማንሳት አምላኩን አከበረበት እንጂ ለህዝቡ ቀንበርን አላከበደም።

ወደ አዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር አገልግሎት ስንመለስ (1ኛ ጢሞ. 3፥1-13) እንዲህ ይላል፥-*"ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል የሚለው ቃል የታመነ ነው። እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ የማይነቀፍ፥ የአንዲት ሚስት ባል፥ ልከኛ፥ ራሱን የሚገዛ፥ እንደሚገባው የሚሰራ፥ እንግዳ ተቀባይ፥ ለማስተማር የሚበቃ፥ የማይሰክር፥ የማይጨቃጨቅ ነገር ግን ገር የሆነ፥ የማይከራከር፥ ገንዘብን የማይወድ፥ ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፤... እንዲሁም ዲያቆናት ጭምቶች፥ በሁለት ቃል የማይናገሩ፥ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይጎመጁ፥ነውረኛ ረብ የማይወዱ፥ በንጹሕ ሕሊና የሃይማኖትን ምሥጢር የሚይዙ ሊሆኑ ይገባቸዋል።"* ኤጲስ ቆጶስነት (Bishop) እንዲሁም ዲያቆንነት አገልግሎት ነው፤ ይህን አገልግሎት የሚፈልግና ለዚህ የተጠራ ሁሉ ግን የተዘረዘሩትን መንፈሳዊ ህይወት ሊኖር ይገባል። ለአዳም ገነትን አብጅ ጠብቅ የሚል ትዕዛዝ አገልግሎቱ ነው፤ በገነት ካሉት ዛፎች የማይበላውን አትብላ የሚበላውን ብላ የሚል ትዕዛዝ ደግሞ ህይወቱ ነው። አገልግሎት ሲሰጠን ለተሰጠን አገልግሎት የሚጠበቅብን መንፈሳዊ ህይወት እንዳለ መልዕክቱ ያስረዳናል።

የሐ.ሥራ 1፥17 እንደሚነግረን ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ጋር ተቆጥሮ የነበረው የአስቆሮቱ ይሁዳ በአገልግሎቱ ፍሬያማ እንዳይሆን ያደረገው በህይወቱ የተለማመደው ከአገልግሎት ይልቅ በገንዘብ በልጥጎ መገኘትን መናፈቁ ነው፤ ይህም ገንዘብን የመውደድ ምልክት ነው። (ዮሐ. 12፥4-6፣ 1ኛ ጢሞ. 6፥6-10)። የአገልጋይ ህይወት ገንዘብን በመውደድ ፍቅር ከተነደፈ ለመንፈሳዊ ህይወቱ ወጥመድ ከመሆኑም ባሻገር በአገልግሎቱ እንዳይቀጥል እንቅፋት ይሆንበታል። ለምንወደው ገንዘብ ስንል ማድረግ የማይገባንን እንድናደርግና መገኘት በማይገባን ህይወት ውስጥ እንድንገኝ የሚያስገድድ ተጽዕኖ ሊፈጥርብን ይችላል፤ እግዚአብሔርንም በህይወታችን ሊያሸከመን ከሚፈልገው ኃላፊነት ወደ ኋላ እንዲል ያደርገዋል።

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በሐዋርያት ለተተከሉ አብያተ ክርስቲያናት የተሾሙ አገልጋዮችና ሽማግሌዎችን ስንመለከት በህይወታቸው የማይነቀፍ አካሄድ የነበራቸው ናቸው (ሐዋ. 6፥3-6)። አንድ የቤተክርስቲያን አገልጋይ በቤተክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በሚኖርበት ማህበረሰብም መልካም ምስክር ሊኖረው ይገባል (1ኛ ጢሞ. 3፥7)። ሐዋርያው ጳውሎስ ቲቶንና ጢሞቴዎስን በመልዕክቶቹ የእርሱን አካሄድ፣ እምነት፣ አሳብና መጽናትን እንዲከተሉና ከሌሎች ሥጋውያን እንዲርቁና እንዲሸሹም ይመክራቸዋል። በቤተክርስቲያን በኃላፊነት የሚሾሙ ከሥራ ልምዳቸው ይልቅ በመንፈሳዊ ህይወታቸው በሚታይ መንፈሳዊ ፍሬ ላይ ትኩረት አድርገው እንዲሾሙም ያሳስባል (1ኛ ጢሞ. 6-11-12፣ 2ኛ ጢሞ. 3፥10-17፣ ቲቶ 1፥5-16፣ ቲቶ 2፥1-10)።

**የአገልጋይ ህይወት ገንዘብን በመውደድ ፍቅር ከተነደፈ ለመንፈሳዊ ህይወቱ ወጥመድ ከመሆኑም ባሻገር በአገልግሎቱ እንዳይቀጥል እንቅፋት ይሆንበታል።**

ሐዋርያው ጳውሎስ እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እናንተ ደግሞ እኔን ምሰሉ በማለት ፍለጋውን እንድንከተል ይመክረናል፤አገልግሎት ከነቀፌታ የሚጠበቀው ክርስቶስን ለመምሰል ስንተጋም ነው። *"አገልግሎታችንም እንዳይነቀፍ በአንዳች ነገር ማሰናከያ ከቶ አንሰጥም። ነገር ግን በሁሉ እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳችንን እናማጥናለን፤ በብዙ መጽናት፥ በመከራ፥*

*በችግር፥ በጭንቀት፥ በመገረፍ፥ በወኅኒ፥ በሁከት፥ በድካም፥ እንቅልፍ በማጣት፣ በመጦም፥ በንጽህና፥ በእውቀት፥ በትዕግሥት፥ በቸርነት፥ በመንፈስ ቅዱስ፥ ግብዝነት በሌለው ፍቅር፥ በእውነት ቃል፥ በእግዚአብሔር ኃይል፥ ለቀኝና ለግራ በሚሆን በጽድቅ የጦር ዕቃ፥ በክብርና በውርደት፥ በክፉ ወሬና በመልካም ወሬ ራሳችንን እናማጥናለን፤ አሳቾች ስንባል እውነተኞች ነን…"* (2ኛ ቆሮ. 6፥1-10)። በጽድቅና ነቀፋ በሌለው ህይወት የሚመላለስና በዚሁ ህይወት የሚያገለግል አገልጋይ የአማኞችን ህይወት የሚያንጽ፣ የእግዚአብሔር መንግስት ናፍቆት ያላቸውንና መዳናቸውን ነቅተው የሚጠብቁ ነፍሳትን ያፈራል (1ኛ ተሰ. 2፥9-12፣ 2ኛ ተሰ. 2፥1-2)።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለአገልግሎት ብቻ የሚሮጥና ትኩረቱን በሙሉ በአገልግሎት ላይ ብቻ ያደረገ ሰው እንዳልሆነ የጻፋቸው መልዕክቶች አስተማሪዎች ናቸው። በታላላቅ ጸጋ ከሁሉም ሐዋርያት ይልቅ በአገልግሎት የደከመ መሆኑን ብቻ ሳይሆን የጻፈልን፣ በዚህ ታላቅ ጸጋ ሲያገለግልና ሲሮጥ ሥጋውን ለእግዚአብሔር እያስገዛ እንደሚያገለግል ጭምር ነው። በሥጋው በኩል በጎ ነገር እንደሌለ የተረዳው ጳውሎስ ሥጋው ኃጢአትን ስቦ ወደ ህይወቱ እንዳያስገባ፣ ለኃጢአት ህይወት ተገዢ እንዳያደርገውና ድካሙን ከንቱ እንዳያደርግበት ለመንፈሳዊ ህይወቱ ልዩ ትኩረት በመስጠት ለአገልግሎት የሚተጋውን ያህል ህይወቱንም ለመቀደስ የሚተጋ መልካም ምሳሌያችን ነው። ከእርሱ ጋር ወንጌልን የሚያገለግሉ አገልጋዮች ይህን ዓለም ወደው ከእርሱ የተለዩ እንዳሉም ለትምህርታችን ሳይጠቁመንም አላለፈም (ሮሜ 7፥17-25፣ 1ኛ ቆሮ. 9፥26-27፣ 2ኛ ጢሞ. 4፥9)።

ነቢዩ ኤልያስ በዘመኑ ከተጠሩት የእግዚአብሔር ነቢያት ብቻውን መቅረቱንና ነፍሱንም አምላኩ እንዲሰበስብለት አምላኩን የተማጸነ ሰው መሆኑን 1ኛ ነገ. 19፥1 ይነግረናል። ምናልባትም ኤልያስ ነፍሱን አምላኩ እንዲወስድ ሲማጸን ከእርሱ ጋር አብረው እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ እንደነበሩ ነቢያት ኋላም አምላካቸውን ክደው የበዓል ነቢያትና የኤልዛቤል አቀንቃኝ እንደሆኑ የእርሱም ህይወት ተበላሽቶ እንደ እነርሱ እንዳይሆን ለህይወቱ ሰግቶ እንደሆነስ የለመነው? ለመንፈሳዊ ህይወት ጥንቃቄ ያላደረገ አገልጋይ ህይወቱ ሲበላሽ ጥንቃቄ ያላደረገለት ህይወቱ አገልግሎቱንም ያሳጣዋል። አገልጋዮች የአገልግሎት ፍሬአቸው የሚለካው ለወንጌሉ እንደሚገባ በሚኖሩት ህይወት ነው። ንጉሱ ዳዊት ከማስተዋል ህይወት ወጥቶ ኃጢአትን ወደ ጓዳው ሲያስገባ ሽንፈትም አብሮ በመግባቱ ጉልበትና ኃይል የሚያገኝበትን ዙፋኑን ጥሎ ለመሸሽ ተገዷል። ህይወት መንፈሳዊ ፍሬና መንፈሳዊ ኃይል ሲጎድለው አገልግሎቱም ጎድሎ ፍሬያማ ያልሆነ ይሆናል። (2ኛ ሳሙ. 15፥1)

አገልግሎት ማለት ወንጌል መስበክ፣ ነፍሳትን በቃሉ መማረክ፣ ልዩ ልዩ ተአምራቶችንና ድንቅ ሥራዎችን መስራት ያለበት ታላቅ ተግባር ቢሆንም ለአገልጋዩ የሚጠቅመው ግን በአገልግሎቱ ውጤታማና ታዋቂ መሆን አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስም ለዚህ ነው *"ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ"* ያለው (1ኛ ቆሮ. 9፥27)። ለራስ የሚጠቅመው ዋና ነገር ሥጋን ማስገዛቱ ነው። ከጌታ ኢየሱስ የተራራው ስብከት አገልግሎትም እንደምንማረው ስለብጽዕናና ስለጽድቅ በማስተማር ጽድቅን እንከተላለን ብለው ከሚያስቡ ከፈሪሳውያንና ጻድቃን በልጦ መገኘት እንደሚገባ ነው። አገልግሎት ከመንፈሳዊ ህይወት በሚመነጭ መንፈሳዊ ፍሬዎች የታጀበ መሆን እንደሚገባው የተራራው ስብከት ያስተምራል።

*"መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ፤ በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንና መራብንም መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ። ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ"* (ፊል. 4፥12)። የክርስቶስን ህይወት መኖር በአገልግሎት ህይወት ሁሉንም ያስችላል። የክርስቶስን ህይወት ለሚኖር የክርስቶስ አገልጋይ መዋረድ ለእርሱ አስቸጋሪ አይሆንበትም፤ ከሁሉም ይልቅ እጅግ አስቸጋሪ የሚሆነው መጥገብ ነው። ሥጋ ያለ ልክ ከጠገበ በሥጋ ፍሬዎች መከበቡ የማይቀር ይሆናል፤ ለዚህ ታዲያ መድኃኒቱ የክርስቶስን ህይወት መኖር ነው። የክርስቶስን ህይወት መኖር ስንጀምር መጥገብንም እንችላለን። የአገልግሎት ጸጋ በዝቶልን ፍሬያማ ብንሆንና ቢሳካልን፣ ሃብትና የኑሮ ተድላ ተሟልቶ ከሌሎች የተሻለ ኑሮ ብንኖርም፣ የትኛውም ከፍታ ላይ እንዳለን ቢሰማንም፣ የክርስቶስን ህይወት ለሚኖር የጥጋብ ትዕቢት ሳይነካው በትህትና አምላኩን ማገልገል ይችላል።

ታላላቅ መሪዎች አገልግሎታቸውን በስኬት ያጠናቀቁት ለመንፈሳዊ ህይወታቸው ስለሚጠነቀቁና ራሳቸውን ከነቀፌታ ስለሚጠብቁ ነው። እኛም አገልግሎታችን በስኬት ተጠናቆ በመጨረሻም በዕጣ ክፍላችን እንድንቆም ከዳንኤልና ከባልንጀሮቹ እንማር፤ ኑሮአቸውን በጠጅና በጮማ የተደላደለ ከማድረግ ይልቅ ህይወታቸውን በቅድስና መጠበቃቸው በአምላካቸው ፊት መታሰቢያ ሆኖ ከልዩ ልዩ ፈተና በድንቅ አዳናቸው። ዳንኤል የስራ ባልደረቦቹ የሚነቀፍበትን ህይወት ፈልገው እስኪያጡ ድረስ የተመሰከረለት ህይወት እንደነበረው ተጽፎአል፤ ይህም ታማኝና ትጉ ህይወቱ ኑሮውንና አገልግሎቱን አቀናለት። ከአምላኩ ህግ በስተቀር ዳንኤል ስሙ የሚጠራበት ሌላ ምክንያት እስከማይገኝበት ድረስ ታማኝነቱን አስመሰከረ። በዚህ በመጨረሻው ዘመንም ያለን የእግዚአብሔር አገልጋዮች በጊዜያዊ ተድላ ሳንታለል ከሚያስነቅፍ ህይወት ራሳችንን ብንጠብቅ የተዘጋጀልንን መንግስት ወራሾች እንሆናለን፤ ነገር ግን ለግል ኑሮ መቃናትና ለጊዜያዊ ተድላ ከተሸነፍን ለዚህም የምንሮጥ ከሆነ ዕድል ፈንታችን ከማያምኑና ከሴሰኞች ጋር በተዘጋጀላቸው የዘለዓለም የገሃነም ፍርድ ይሆናልና፤ ከዚህም ለማምለጥ ህይወታችንን ከክፉ ነገሮች ሁሉ እንጠብቅ! (ዳን. 12፥13፣ ራዕ 21፥8)። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም በሁሉ ይርዳን! ■

# አንተ ግን!

- አንተ ግን በአምላክህ በእግዚአብሔር ዘንድ ፍጹም ሁን! (ዘዳ. 18፥3)
- አንተ ግን እግዚአብሔርን ፍራ! (መክ. 5፥7)
- መልካም ባታደርግ ኃጢአት በደጅ ታደባለች… አንተ ግን በእርስዋ ንገስባት! (ዘፍ. 4፥7)
- አንተ ግን የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከዚህ ሽሽ! (1ኛ ጢሞ. 6፥11)
- አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር! (2ኛ ጢሞ. 3፥14)
- አንተ ግን በእኔ ዘንድ ቁም! (ዘዳ. 5፥31)
- አንተ ግን ወገብህን ታጠቅ! (ኤር. 1፥17)
- አንተ ግን እስከፍጻሜው ድረስ ሂድ! (ዳን. 12፥13)
- አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ! (2ኛ ጢሞ. 4፥5)
- አንተ ግን ትምህርቴንና አካሄዴን፣ አሳቤንም፣ እምነቴንም፣ ትዕግሥቴንም፣ ፍቅሬንም፣ መጽናቴንም፣ ስደቴንም፣ መከራዬንም ተከተልህ! (2ኛ ጢሞ. 3፥10) ■

# ደቀመዝሙር

# ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው!

✍ ከምስራቅ አያት አጥቢያ ስነጽሁፍ አገልግሎት

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በማይቆጠሩ ዘመናት የሚኖር ዘላለማዊ አምላክ እንደሆነ ይነግረናል፤ በአንጻሩ የሰው ልጆች ግን ሊተላለፉ በማይችሉት ዳርቻ የተገደበ የዕድሜ ዘመን እንዳላቸው ያስተምራል። (ኢሳ. 40፥28፣ ኢዮ. 14፥5) እንዲሁም እግዚአብሔር በሰው ልጆች ላይ ያለውን ዘላለማዊ ሃሳብ በተወሰነላቸው ዘመን እየመጡ በሚሄዱ ትውልዶች መካከል አጽንቶ በትውልድ ቅብብሎሽ በኩል የሚፈጽም አምላክ እንደሆነም በቃሉ የሚስተዋል እውነት ነው።

እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ያደረገውን መስተጋብርና የፈጠረውን ግንኙነት በቃሉ ስናጤን ሥራውን በአንድ ትውልድ ይጀምር እንደሆነ እንጂ በአንድ ትውልድ ጀምሮ ሲጨርስ አይስተዋልም። ይህም በባህርይው ዘላለማዊ የሆነው ጌታ የጊዜ ዳርቻ ባበጀላቸው የሰው ልጆች ዘንድ ሥራውን እንዴት እንዲከውን አሠራሩን ያሳየናል። በአብርሃም ላይ ሥራውን ጀመረ እንጂ በእርሱ ዘመን የተጀመረ የእግዚአብሔር አጀንዳ በእርሱ ዘመን አላለቀም፤ ይስሃቅ፣ ያዕቆብ፣ እስራኤል እያለ ትውልድን ተሻግሮ ቀጥሏል።

በእነ ሙሴም ዘመን ሆነ በነቢያቱ ብሎም በሐዋርያቱ ዘመን የእግዚአብሔር አሠራር አልተለወጠም፤ የእግዚአብሔር ሃሳብ በአንድ ትውልድ የእድሜ ዘመን ተፈጽሞ የማያልቅ በትውልድ ቅብብሎሽ የሚከወን ሆኖ ዘልቋል። ስለሆነም የአንድ ትውልድ ቤተክርስቲያን መለኮታዊ አደራዋን በሙላት የምትፈፅመው በተሰጣት ዘመን አገልግሎቷን ከመፈፀም ባሻገር ይህን ትውልድ ተሻጋሪ የሆነውን መለኮታዊ አደራ ለቀጣዩ ትውልድ በሙላት ያስተላለፈች እንደሆነ ነው።

ስለዚህም እውነት ቢሾፕ ደጉ ከበደ “በእግዚአብሔር የተጠራ አገልጋይ – ከጅምር እስከ ፍጻሜ” በሚል ባዘጋጁት ድንቅ መጽሐፍ ገጽ 203 ላይ “እግዚአብሔር ለወንጌሉ ጠርቶ የለየው አገልጋይ አገልግሎ አገልግሎ ደክሞ አገልግሎቱን የሚረከብለት ትክክለኛ የእግዚአብሔር ጥሪ ያለው አገልጋይ ካላፈራ ድካሙ ሁሉ ከንቱ ሆነ ማለት ነው። የሙሴ ጥሪ ትልቁ ማረጋገጫ የሚታየው በራሱ ዘመን በሠራው ሥራ ላይ ሳይሆን በተተኪው በኢያሱ በኩል በተሠራው ሥራ ነው።” በማለት አጽንኦት ሰጥተው አስፍረውታል።

እንግዲህ ይህ አደራ ወደ ግብ ይደርስ ዘንድ በእግዚአብሔር ቃል የተቀመጠው ሁነኛ መንገድ “ደቀመዛሙርት”ን በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ለይቶ በማወቅ ተልዕኮውን ተረክበው ማስቀጠል ወደሚችሉበት የመንፈሳዊ ህይወት ሙላት ማድረስ ነው።

እንግዲህ በዚህች አጭር ጽሁፍ ደቀመዛሙርትን ስለማፍራት በእግዚአብሔር ቃል የተገለጠውን ሰፊ ትምህርት ሙሉ በሙሉ ለማቅረብ የሚሞከር ባይሆንም በዚህ ርዕስ በቀጣይነት ለሚቀርቡ መልዕክቶች መንደርደሪያ የሚሆኑ ሃሳቦችን እንዳስሳለን።

## “ደቀ መዝሙር” ምን ማለት ነው?

“ደቀመዝሙር” የሚለው ቃል ማቴቴስ (Mathetes) ከሚል የግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን የጥሬ ቃሉ ቀጥተኛ ትርጓሜም ተማሪ፣ ተከታይ፣ የአንድ ርዕዮተ አለም፣ ፍልስፍና ወይም ትምህርት ተከታይና አራማጅ፣ አንድን ሙያ እየተለማመደ ያለ ተለማማጅ የሚል ነው። ሆኖም የቃሉን አጠቃላይ ፍቺ ስንመለከት ደግሞ “ደቀመዝሙር” ማለት መሪውን/መምህሩን ለመምሰል ራሱን ሰጥቶ የሚከተል ተመሪ (ተማሪ) ማለትን ያመለክታል።

ደቀመዝሙር የሚለው ቃል ራሳቸውን ከአንድ መምህር ስር አድርገው እንደ መምህሩ ለመሆን የሚማሩና የሚጣጣሩ ተማሪዎችን የሚወክል ነበር (ማቴ 10፥25 ፣ ሉቃ 6፥40)። ራሱን ለመምህሩና ለትምህርቱ ከሁሉ አብልጦ የሰጠ ተማሪም በትምህርቱ የመለወጥና የመምህሩ ተተኪ የመሆን እድሉ የሰፋ ነበር። ይህ “ደቀመዝሙር” የሚለው ቃልም በቀጥታ በወንጌላት እና በሐዋርያት ሥራ ብቻ እንኳን 264 ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል።

በመጽሐፍ ቅዱስ  የተለያዩ አይነት ደቀመዛሙርት ተጠቅሰው እናገኛለን፤ እነዚህም፡-

- የሙሴ ደቀመዛሙርት (ዮሐ 9፥28)
- የፈሪሳውያን ደቀመዛሙርት (ማቴ 22፥16፣ ማር 2፥18)
- የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀመዛሙርት (ማቴ 9፥14 ፣ 14፥12 ፣ ማር 2፥18 ፣ ሉቃ 11፥1 ፣ ዮሐ 3፥25)
- የክርስቶስ ደቀመዛሙርት (ማቴ 5፥1 ፣ ዮሐ 4፥1 ፣ 8፥31 ፣ 9፥27-28፤ በተለይ አስራ ሁለቱ ሐዋርያት – ማቴ 10፥1 ፣ 11፥1 ፣ 20፥17 ፣ ሉቃ 9፥1) ናቸው።

ደቀመዝሙር ተማሪና ተከታይ ነው። ከተማሪነት አንጻር ካየነው ደቀመዝሙር ለመማር ራሱን የሰጠ ተማሪ ማለት ሲሆን ከመከተል አንጻር ካየነው ደግሞ ደቀመዝሙር ሁሉን ትቶ መሪውን ፈጽሞ ለመከተል የቆረጠና በነገር ሁሉ መሪውን ለመምሰል የሚከተል ማለት ነው። የዚህ ጽሁፍ ማጠንጠኛ የሆነው የክርስቶስ ደቀመዝሙርነት ከክርስቶስ ጋር

እየጨመረና እያደገ የሚሄድ ግንኙነትን መስርቶ በነፍስ ፈቃድ ለእግዚአብሔር ዘወትር መገዛትን ግብ ያደረገ የህይወት ይዘትን የሚገልጽ ነው። ይህም በክርስቶስ የመስቀል ፍቅር የእውነት የተነካ ሰው በፈቃዱ በሚሰጠው የህይወት ምላሽ የሚገኝ ነው። ሰው በታላቅ ፍቅሩና ምህረቱ ላዳነው አምላክ ሊሰጠው የሚችለው ተገቢ ምላሽ እርሱን በፍጹም ልብ ማምለክ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ ለእግዚአብሔር የምናቀርበው አምልኮ በዜማ ከሚቀርብ ዝማሬና ምስጋና ያለፈ እንደሆነ ያስተምረናል። ይህም የአምልኮ ሙላት ሰው ሙሉ ህይወቱን ህያውና ቅዱስ መስዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ያቀርብ ዘንድ ይጠይቀዋል። (ሮሜ. 12፥ 1-2) ይህ አይነቱ ህይወት ደግሞ በክርስቶስ የተገለጠ የህይወት አይነት ሲሆን ሰውም በዘመኑ በሙላት የእግዚአብሔርን ሃሳብ አገልግሎ ሊያልፍ የሚችልበትን መንገድ የሚያሳይ ነው፤ እርሱም ክርስቲያን በደቀመዝሙርነት የህይወት መንገድ የሚቀዳጀው ነው።

በአጠቃላይ የክርስቶስ ደቀመዝሙር የክርስቶስ ህይወት በህይወቱ የሚገለጥና ወደ ክርስቶስ ሙላት ለመድረስ የሚያድግ ህይወት ያለውም ነው። እንዲያውም "ክርስቲያን" ተብለው የተጠሩት የመጀመሪያዎቹ የክርስቶስ ተከታዮች የእግዚአብሔርን እውነትና የተከተሉትን የክርስቶስን ህይወት በመኖር በሙላት የገለጡ የህይወት መዓዛቸው ክርስቶስን የሚያውድ የክርስቶስ ደቀመዛሙርት እንደነበሩ የእግዚአብሔር ቃል ያስተምረናል። *"በቤተክርስቲያንም አንድ ዓመት ሙሉ ተሰበሰቡ፥ ብዙ ሕዝብንም አስተማሩ፤ ደቀመዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ"* (ሐዋ. 11፥26)።

ስለዚህ የክርስቶስ "ደቀመዝሙር" ክርስትናን በሙላት እንዲገልጥ የተወሰነውን የህይወት ይዘት የሚያሳይ እንደሆነ መረዳት እንችላለን። በሌላ በኩል ደግሞ ደቀመዝሙር አማኝ በእግዚአብሔር ቃል በመኖር የሚቀዳጀውን እውነትን በማወቅ አርነት የሚወጣ የክብር ህይወትን የሚያሳይ እንደሆነም የእግዚአብሔር ቃል ያስተምረናል።

*"ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ:- እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤ እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው።"* (ዮሐ.8፥31-32)

## ደቀመዛሙርትን ማፍራት ለምን አስፈለገ?

ደቀመዛሙርትን የማፍራት አስፈላጊነት እጅግ በርካታ ቢሆንም ለዚህ ጽሁፍ አንዱን ብቻ መርጠን እናያለን። ደቀመዛሙርትን ማፍራት በእግዚአብሔር ቃል የተገለጠ የእውነት ወንጌል ለፍጥረት ሁሉ የሚደርስበትና ለቀጣይ ትውልም የሚተላለፍበት መንገድ በመሆኑ ነው። ይህም ጌታ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ በሰጠው "ታላቁ ተልዕኮ" ተብሎ በሚታወቀው ትዕዛዝ በግልጽ የሰፈረ እውነት ነው።

ጌታ ኢየሱስ በማቴ. 28፥19 ለደቀመዛሙርቱ ህዝብን ሁሉ ወንጌልን እየሰበኩና እያስተማሩ ደቀመዛሙርት እንዲያደርጓቸው ማዘዙ ደቀመዛሙርትን ማፍራት እስከአለም ፍጻሜ ድረስ የሚነሳ ትውልድን በወንጌል የምንደርስበት ሁነኛ መንገድ አድርጎ መስጠቱን ያመለክተናል። ደቀመዛሙርትን በማፍራት ውስጥ ያለንን የመስፋፋትና የመዝለቅ መርህ በቀላሉ ለመረዳት እንዲቻለን በምድር ላይ ያሉ ምሳሌዎችንም ወስደን ማየት እንችላለን።

**"ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ። እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤ እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው።"**
(ዮሐ.8፥31-32)

በምድር ላይ ከትውልድ ትውልድ ተላልፈው ከፍተኛ ተጽዕኖ የፈጠሩ አስተምህሮዎችን ብንመለከት ለዚህ ያበቃቸው ዋነኛው ምክንያትና የተጠቀሙት መንገድ ደቀመዛሙርትን በማፍራት ላይ የተመሰረተ ስለነበረ ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት ሲቀነቀን የነበረው የግሪክ ፍልስፍና ትውልድና ዘመናትን ተሻግሮ የሐዋርያትን ወንጌል እስኪበርዝ ድረስ የበረታውና በሰዎች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ መፍጠር የቻለው ፍልስፍናውን ተምረው በመቀበል በትምህርቱ የተጠመቁና ራሳቸውን ለትምህርቱ በሙላት የሰጡ ተተኪ ደቀመዛሙርት በማግኘቱና በማፍራቱ ነው።

ደቀመዛሙርትን ማፍራት ሁነኛ የመስፋፋትና የመዝለቅ መንገድ ሆኖ በእግዚአብሔርም ቃል የተቀመጠልን መርህ እንደሆነ ቃሉ ያሳየናል። ለአብነት ያህልም ከብሉይ ኪዳን ሙሴን ከአዲስ ኪዳን ደግሞ ክርስቶስን ወስደን እናያለን። ሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ህጉንና ትምህርቱን ወደ ቀጣይ ትውልድ በስኬት እንዲሻገር አስችሏል። ይህም የሆነው የተቀበለውን ህግ ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ የሚችሉ ደቀመዛሙርትን ማፍራት በመቻሉ ነው። እንዲያውም ሺህ አመታትን ተሻግሮ በክርስቶስ የስጋ ወራት እንኳ ራሳቸውን "የሙሴ ደቀመዛሙርት" ብለው የሚጠሩ ተከታዮችን ማፍራት ችሏል። (ዮሐ 9፥28) ይህንም እንዲያደርግ እግዚአብሔር ሲያዘው፤ እርሱም ኢያሱን ተተኪ አድርጎ ሲያዘጋጅ በእግዚአብሔር ቃል ተጽፎ እንመለከታለን። (ዘዳ. 3፥28፣ ኢያ. 1፥1-9)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም በስጋ ወራቱ ደቀመዛሙርትን መምረጥና ማዘጋጀት የጀመረው በአገልግሎቱ መገባደጃ ጊዜ ሳይሆን ገና ጅማሬው ላይ ነበረ። (ማቴ. 4፥17-25) በዚህም ክርስቶስ የመንግስት ወንጌል ለፍጥረት ሁሉ እንዲደርስ የተጠቀመበት አሠራር ደቀመዛሙርትን በመምረጥ፣ በማሰልጠን፣ በመሾምና በኋላም ከእነርሱ ጋርና በእነርሱ ውስጥ ሆኖ በመስራት መሆኑን ወንጌላት ይተርኩልናል።

በዚህም ዘመን ያለች የክርስቶስ ቤተክርስቲያን የምትቀጥለው ለቀጣዩ ትውልድ እግዚአብሔር በጠራቸው ተተኪ ደቀመዛሙርት በኩል በመሆኑ ወንጌልን የሚያስቀጥሉ ደቀመዛሙርትን ማፍራት ክርስቶስን እና ቤተክርስቲያንን በሚወድ የእግዚአብሔር አገልጋይ ዘንድ ቸል ሊባል የማይገባ አንገብጋቢ የሰማይ አደራ ነው። የእግዚአብሔርን መንግስት ሥራ በዘመኗ በሙላት ለመግለጥና የወንጌልን አደራ ለቀጣይ ትውልድ ያለ ክፍተት በሙላት ለማስተላለፍ የሚቻለው ደቀመዛሙርትን በማፍራት

በኩል መሆኑን አጥብቆ መረዳት እጅግ ያስፈልጋል።

በእግዚአብሔር የተጠራ አገልጋይም እድሜው ገፍቶ አቅም ሲያንሰውና ሲደክም ሳይሆን ከክርስቶስ በመማር ከአገልግሎቱ ጅማሬ አንስቶ ልብ ሊለውና ሊተጋለት የሚገባ ደቀመዛሙርትን የማፍራት ትልቅ ሃላፊነት እንዳለበት ማወቅ ይኖርበታል። በተለይ በዚህ የመጨረሻ ዘመን ሰይጣን የራሱን ደቀመዛሙርት እየመለመለ እና አማኞች ደግሞ ደቀመዛሙርት እንዳይሆኑ በልዩ ልዩ መባከንና ትኩረት አልባ ጥድፊያ በጠመደመበት ዘመን፤ የዓለም ደቀመዛሙርት፣ የገንዘብ ደቀመዛሙርት፣ የፖለቲካ ደቀመዛሙርት በዝተው በሚርመሰመሱበትና ለአማኝ እጅግ አስጨናቂ በሆነ ዘመን ቤተክርስቲያን የአለም ብርሃን በመሆን ክርስቶስን የሚገልጡና ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑ የክርስቶስ ደቀመዛሙርት ማፍራት ላይ ሙሉ ትኩረቷን አድርጋ ልትሰራ ይገባል።

በዚህ የመጨረሻ ዘመን በክፉ ትውልድ መካከል በእጥፍ መንፈስና ቅባት ቤተክርስቲያንን የሚያስቀጥሉ ደቀመዛሙርትን ለማፍራት እግዚአብሔር ጸጋን እንዲያበዛልንና እንዲረዳን ዘወትር መጸለይና ራስንም ለዚህ ቅዱስ ተግባር መስጠት እንድንችል ጌታ ኢየሱስ ይርዳን። አሜን! ■

## ምክር፣ ትዕዛዝ፣ ፍርድና ጸሎት!

- ትዕቢት ከመጣች ውርደት ትመጣለች! (ምሳሌ 11፥2)
- ትህትናም ክብረትን ትቀድማለች! (ምሳሌ 18፥12)
- አንዳች በትዕቢት የሚያደርግ ሰው እግዚአብሔርን ሰድቦአል! (ዘኍ. 15፥30)
- የትህትናን ነገር ለመስራት ትጉ! (ሮሜ 12፥16)
- አቤቱ ልቤ አይታበይብኝ፤ አይኖቼም ከፍ ከፍ አይበሉብኝ! (መዝ. 131፥1)
- ትህትናን እንደልብስ ታጠቁ! (1ኛ ጴጥ. 5፥5)
- የትዕቢት እግር አይምጣብኝ! (መዝ. 36፥11) ■

# ከቤተክርስቲያን አካባቢ

**"ይህን የሠራና ያደረገ፥ ትውልድንም ከጥንት የጠራ ማን ነው? እኔ እግዚአብሔር፥ ፊተኛው በኋለኞችም ዘንድ የምኖር እኔ ነኝ።" ኢሳ. 41፥4**

ከሐምሌ 1 ቀን 2010 ዓ.ም አስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን በሚገኙ አጥቢያዎች የእግዚአብሔር መልካሚቱ እጅ በሁላችንም ላይ ሆና ብዙ ነፍሳት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠምቀዋል፣ ከአጋንንት አስራት ተፈተዋል በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተዋል። ሪፖርት ያልተደረጉ ኢየሱስ በእጁ ፈውሶ ያዳናቸው እንዳሉ ሆነው ብዙ ቅዱሳን የልጆች እንጀራ የሆነውን ፈውስ ተቀብለዋል። ወንጌል በየምድረበዳው እየተሰበከ አዳዲስ አጥቢያዎች ተከፍተዋል።

እግዚአብሔር ቢፈቅድ ብንኖርም በፊታችን ባለው ዘመን የእግዚአብሔርን ክንድ ፊቱን በመፈለግ እያንቀሳቀስን የኋላችንን እየረሳን ሁላችን ይህንን በድንቅና በተዓምራት የሚታጀብን ወንጌል ለጠፋው አለም እንድናውጅ ጌታ ኢየሱስ ይርዳን።




"አሕዛብ እንዲታዘዙ ክርስቶስ በቃልና በሥራ፥ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል፥ በመንፈስ ቅዱስም ኃይል በእኔ አድርጎ ከሠራው በቀር ምንም ልናገር አልደፍርም፤"

ሮሜ 15፥18-19

# አምልኮ

# መዝሙርን ከምንጩ

✍ ወንድም ዮሐንስ ኃይሉ ׀ከሰሜን አ.አ ርኆቦት አጥቢያ

የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ የሚሞትበት ቀን በቀረበ ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴንና ከእርሱ በኋላ የእስራኤልን ልጆች የሚመራውን ሰው ኢያሱን ጠርቶ *"አሁንም ይህችን መዝሙር ለእናንተ ጻፉ፥ ለእስራኤልም ልጆች አስተምሩአቸው፤ ይህችም መዝሙር በእስራኤል ላይ ምስክር ትሆንልኝ ዘንድ በአፋቸው አድርጓት። ... ዛሬ ወደ ማልሁላቸው ምድር ገና ሳላገባቸው የሚያስቡትን አሳብ አውቃለሁና፥ ከልጆቻቸውም አፍ አትረሳምና ብዙ ክፉ ነገርና ጭንቀት በደረሰባቸው ጊዜ ይህች መዝሙር ምስክር ሆና በፊታቸው ትመሰክራለች"* ብሎ መዝሙርን እንደሰጣቸው እናያለን (ዘዳ 31፥19-21)። የመዝሙሩ ሙሉ ቃል በዘዳግም 32 ላይ ተጽፎ ይገኛል።

በዚህ የእግዚአብሔር ቃል ክፍል *"... መዝሙር ምስክር ትሆንልኝ ዘንድ..."* የሚለው የጥቅሱ አንኳር መልዕክት ያለበት ስለሆነ ትኩረት ሰጥተን ከሌላ የእግዚአብሔር ቃል ክፍል ጋርም አስተያይተን ብንረዳው መልካም ነው። እስኪ ከዚህ ቀጥሎ ከብሉይም ከአዲስም የተወሰዱትን ስለ "ምስክር" የተጻፉ ጥቅሶችን እንመልከት፥-

1. መዝ (119) ፥36 *"ልቤን ወደ ምስክርህ አዘንብል፤ ወደ ስስትም አይሁን።"*

2. ማቴ 24፥14 *"ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፤ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል"* ይላል።

ከእነዚህ ጥቅሶች በመነሳት "የእግዚአብሔር ምስክር" ማለት "የእግዚአብሔር ቃል ወይም ሕግ" ማለት መሆኑን እንረዳለን። ሰው በምድር ላይ እንዲኖር በተሰጠው ዘመን ሕይወቱን ሁሉ እንዲመራበት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ የሰጠው ቃል (ወይም ሕግ) ከሚጠራባቸው መጠሪያዎች አንዱ "የእግዚአብሔር ምስክር" የሚለው እንደሆነ ግልጽ ነው። በተጨማሪ መዝ (119)፥14ን ይመልከቱ። የእግዚአብሔር ቃል በሌላ አጠራር የእግዚአብሔር ሕግ (መዝ (119)፥97)፣ የእግዚአብሔር ፍርድ (መዝ (119)፥13)፣ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ (መዝ (119)፥15) እና የእግዚአብሔር ሥርዓት (መዝ. (119)፥24፣ 48) በመባል ይታወቃል። የእግዚአብሔር ታቦት የሚያድርበት ድንኳን ራሱ በታቦቱ ውስጥ በጽላቶቹ ላይ ከተጻፈው ከእግዚአብሔር ቃል (ሕግ) የተነሳ "የምስክሩ ድንኳን" ሲባል ታቦቱም "የምስክሩ ታቦት" በመባል ይታወቅ ነበር (ዘጸ 31፥7፤ ዘኁ 9፥15)። ስለዚህ "ምስክር" የሚለውን ቃል በዘዳ 31፥19-21 በተቀመጠው አገባብ የእግዚአብሔር ቃል ወይም የእግዚአብሔር ሕግ መሆኑን ከላይ ያየናቸው ጥቅሶች በግልጽ ያስረዳሉ።

በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ነቢያት ከእግዚአብሔር የሚቀበሉትን መልዕክት *"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥-..."* እያሉ ለእስራኤል ልጆች ያስተላልፉ እንደነበረ በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ሥፍራ የምናነበው ነው። ሙሴም ከእግዚአብሔር ለእስራኤላውያን መልዕክት በተቀበለ ቁጥር *"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥- ..."* እያለ ሲያስተምር ኖሮ ኖሮ፣ በዘዳ 31 ላይ ግን ለየት ባለ ሁኔታ ወደ እስራኤል ልጆች መጣ፣ የእግዚአብሔርን ሕግ በመዝሙር መልክ ይዞ ማለት ነው። ሕጉን በትምህርት መልክ ሲሰጥ የኖረው ያው እግዚአብሔር ሕጉን በመዝሙር መልክ ደግሞ ለሕዝቡ ያስተምሩ ዘንድ ለሙሴና ለኢያሱ ሰጠ። ለዚህ ነው እነሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበሉት መዝሙር "ምስክር" የተባለው፤ ከእግዚአብሔር በመዝሙር መልክ የተቀበሉት የእግዚአብሔር ቃል (ሕግ) ስለሆነ ማለት ነው።

እንግዲህ በዚህች በእውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ አሁን የምንዘምራቸው፣ ወደፊትም ልንዘምራቸው ያሉ መዝሙሮች ከጥንት ጀምሮ የነበረውን እግዚአብሔርን የመሳብና ክፉ መንፈስን የማራቅ ጉልበቱን ይዞ እንዲቀጥል ያስፈልጋል። ታዲያ የመዝሙር ጉልበት ምንጩ ከእግዚአብሔር መሆኑ ላይ እንደሆነ አስቀድመን ልንገነዘብ ይስፈልጋል። በቤተክርስቲያን ውስጥ በየደረጃው ያሉ እግዚአብሔር ያስቀመጣቸው አገልጋዮች የመዝሙርን አገልግሎት በተመለከተ ድርሻቸው ምንድነው መሆን ያለበት? የሚለው ጥያቄ ወደ አዕምሮአችን መምጣቱ አይቀርም። የእግዚአብሔር ቃል *"... አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፏልና"* (ሮሜ 15፥4) እንደሚል እኛም የቤተክርስቲያን አገልጋዮችን ከላይ በተጠቀሰው በዘዳ 31፥19-21 ካለው ከእግዚአብሔር ቃል እንማር እንላለን።

አንደኛ የምንማረው ነገር መዝሙር ከእግዚአብሔር የምንቀበለውና በዚህም ምክንያት "የእግዚአብሔር ምስክር" ሆኖ የሚቆም መሆኑን ነው። እነሙሴ ከእግዚአብሔር መዝሙርን ተቀበሉ፣ ጻፉ፣ በሕዝቡም አፍ አደረጉ/አስተማሩ። በዚህም በቤተክርስቲያን ዘመን ይኸው መዝሙርን ከእግዚአብሔር የመቀበል ልምምድ መቀጠል አለበት። ይህ ሲባል እስከዛሬ የወጡ መዝሙሮች ከእግዚአብሔር አልነበሩም ማለት አይደለም፤ የመዝሙር ጸጋ ያላቸው ወንድሞችና እህቶች በእግዚአብሔር መዝሙር እውቀት ይበልጥ እንዲያድጉና በእግዚአብሔር ቃል እውቀት ሲመዘን

ትክክል ያልሆኑ በአንዳንዶች ዘንድ የሚስተዋለው ስለ መዝሙር ያለው አረዳድ እንዲስተካከል ነው እንጂ። እንግዲህ መዝሙርን ከእግዚአብሔር እንቀበል ስንል ምን ማለታችን ነው? በአጭር ቃል መዝሙርን ከቃሉ እንቀበል ማለታችን ነው። ትንሽ ዘርዘር አድርገን እንመልከት።

አሁን በእጃችን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ምስክርም ይሆን ዘንድ ጌታ ኢየሱስ ዳግም ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት ለሰው ሁሉ የሚነገር መለኮታዊ ቃል ነው። ታዲያ ቃሉን በምናጠናበት ወቅት ከገለጥነው የመጽሐፍ ክፍል ሁሉ ግጥምን አዘጋጅተን ዜማ ብንሰጠው ቃሎቹ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለሆኑ ብቻ "ይህች መዝሙር ከእግዚአብሔር ናት" ማለት እንችላለን? እንደሱ አይደለም። የእግዚአብሔር ቃል አገልጋዮች ቃሉን በየጥናት ፕሮግራሞቻቸው በሚያነቡበት ወቅት የሚያነቡት/የሚያጠኑት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሁሉ የጊዜው መልዕክት አይሆንላቸውም። የጊዜውን መልዕክት የሚቀበሉት ግን ከቃሉ ነው እንጂ ከሌላ አይደለም። እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያስፈልገውን የጊዜውን መልዕክት የሚሰጠው ከቃሉ ስለሆነ አገልጋዩ የእግዚአብሐርን ቃል በጸሎት ውስጥ ሆኖ በሚያነብበት ወቅት እግዚአብሔር በልዩ ሁኔታ በልቡ ውስጥ የሚያስቀምጠው ነገር ይኖራል። እንዲሁ አገልጋይ የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ያለው ከሆነ እግዚአብሔር አንድን ቃል ወደ ልቡ በልዩ ሁኔታ እያቀረበ መልዕክት አድርጎ ሊሰጥ ይችላል። በሌላ አነጋገር፣ የእግዚአብሔርን ድምጽ የሚሰማ ሰው ማለት በቅድስና እየተመላለሰ ከጸሎትና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው ሰው ነው ማለት ይቻላል። መዝሙርም እንዲሁ ነው። ያነበብነው የመጽሐፍ ቅዱስ (የእግዚአብሔር ቃል) ክፍል ሁሉ መዝሙር አይሆንም፤ ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ ደግሞ መዝሙር አይወጣም፤ ከወጣም የእግዚአብሔር መዝሙር መሆን አይችልም። እግዚአብሔር ከቃሉ ውስጥ ለአገልጋዮቹ መልዕክትን ይሰጣል፣ መዝሙርንም ደግሞ ይሰጣል። እንደዚህ በመንፈስ ቅዱስ ከቃሉ ውስጥ የተቀበልነው ሲሆን መዝሙሩ፦ የእግዚአብሔር ምስክር፤ የእግዚአብሔር መዝሙር ይባላል።

በ2ኛ ዜና 29፥27 "<u>የእግዚአብሔር መዝሙር</u> ደግሞ ተጀመረ" የሚለው ቃል የመዝሙር ባለቤት እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን በግልጽ ያመለክታል። እንዲሁም የእግዚአብሔር ቃል በመዝ. (119)፥54 ላይ *"በእንግድነቴ አገር ሥርዓትህ <u>መዝሙር ሆነችኝ</u>"* በማለት የእግዚአብሔር መዝሙር ምንጩ የእግዚአብሔር ሥርዓት (የእግዚአብሔር ቃል) መሆኑን ያስተምረናል።

በኢዮ 35፥10-11 *"ነገር ግን <u>በሌሊት መዝሙርን</u> የሚሰጥ፣ ... እግዚአብሔር ወዴት ነው? የሚል የለም።"* ይላልና ልክ ሙሴና ኢያሱ መዝሙርን ከእግዚአብሔር ተቀብለው እንደጻፉ እና ለእስራኤልም ልጆች እንዳስተማሩት በእኛም ዘመን መዝሙሮች ከእግዚአብሔር የምንቀበላቸው እንጂ ከራሳችን ወይም ከሌላ (ከዓለም) በምንም ሁኔታ የተኮረጁ መሆን እንደሌለባቸው የማስተማር ኃላፊነት በየአገልጋዩ ላይ ነው ያለው። ቤተክርስቲያን መዝሙርን ከምንጩ ትቀበል።

መንፈስ ቅዱስን የተሞላና የመዝሙር ጸጋ የተሰጠው ወንድም ከእግዚአብሔር መዝሙርን መቀበል እንዲችል በተቀደሰ

የመዝሙርን ዜማ የሚያስተምር ወይም የሚሰጥ ማነው? ዓለም ናት ወይስ እግዚአብሔር? በቤተክርስቲያን ውስጥ ከዓለም በተወረሰ ዜማና አጨዋወት አምልኮ እያቀረብን ዓለማዊ የሚመስል ክርስቲያን ሆነን እንዳንገኝ ያስፈራል።

የእስራኤልን ልጆች እግዚአብሔር ከግብጽ ምድር በብዙ ተዓምራት ካወጣቸው በኋላ በምድረ በዳ ከሰማይ መናን እያበላቸው ከዓለት ውኃን እያጠጣቸው በድንቅ እየመራቸው እያለ የእስራኤል ልጆች ግን የግብጽን ዱባና ሽንኩርት ይመኙ እንደነበረ የእግዚአብሔር ቃል ያስተምረናል። ሰማያዊ መገለጥ ባለባትና የክርስቶስ እጮኛ በሆነችው በብቸኛዋ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሆኖ የዓለምን "መዝሙር" መመኘትና አልፎም ወደ

> **የቤተክርስቲያን መዝሙሮችና የመዝሙር መሣሪያ አጨዋወቶች የተቀደሱ (የተለዩ)፣ ከዓለም ያልተቀዱ እና የራሳቸው ቃና ያላቸው እንዲሆኑ እንመኛለን።**

ሕይወት እየተመላለሰ ለጸሎት የሚተጋ፣ ቃሉን የሚወድና ለማንበብም የሚተጋ መሆን እንዳለበት ልናስተምር ይገባናል። በመዝ. (40)፥3 *"አዲስ ዝማሬን ለአምላካችን ምስጋና በአፌ ጨመረ፤"* ስለሚል መዝሙር ከእግዚአብሔር ተቀብለን ለእግዚአብሔር የምናቀርበው መስዋዕት ስለሆነና አገልግሎቱም የሌዋውያን አገልግሎት እንደመሆኑ መጠን አገልጋዮች መዘምራንም ለመዝሙር የሚገባውን ትኩረት እንድንሰጥ ያስፈልገናል።

መዝሙርን ከእግዚአብሔር የመቀበል ልምምድ ሳይኖር ሲቀር በመዝሙሮቻችን ላይ በተለያየ መልኩ የሚገለጽ የዓለም ተጽዕኖ መስተዋሉ አይቀሬ ነው። ከሌሎች የእምነት ድርጅት "መዝሙሮች" በቀጥታ ወይም እጅግ በተቀራረበ ሁኔታ የተኮረጀ ዜማ፣ ቃላት፣ አዘማመር እና የመዝሙር መሣሪያ አጨዋወት በአሁን ጊዜ በአንዳንድ የቤተክርስቲያን መዝሙሮች ላይ እየታየ ያለ እግዚአብሔርንም ሆነ ቅዱሳንን የማያስደስት ተግባር ነው። የጸጋ ሁሉ አምላክ የሆነን እግዚአብሔርን የሚያመልክ ዘማሪ እንዴት ከኤልዛቤል ሰፈር ይቃርማል?! ዛሬ ለቤተክርስቲያን ልጆች (ዘማሪዎች)

ቤተክርስቲያን ማምጣት ከእስራኤል ልጆች ታሪክ በምን ይለያል? ያ የእስራኤል ልጆች ታሪክ እግዚአብሔርን እጅግ ያስቆጣ ታሪክ ነበር። ዛሬም የእግዚአብሔር ልጆች በዚህ ነገር እጅግ ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል።

የእግዚአብሔር ቃል *"ከእናንተ <u>ማንም ጥበብ ቢጎድለው</u> ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን <u>ይለምን</u> ለእርሱም ይሰጠዋል።"* (ያዕ 1፥5) ተብሎ እንደተጻፈ በጾምና በጸሎት በተሰበረ ልብ ወደ ጸጋው ዙፋን ለሚቀርብ የሚያስፈልገውን ሁሉ ሊሰጥ እግዚአብሔር በቃሉ ታማኝ ነውና አምላካችንን ለምነን እንቀበል እንጂ አንድ የምንወደውን ነገር ለመሥራት እርዳታ ወይም ልምድ ፍለጋ ወዲያና ወዲህ ስንል የማይገባ ነገር ውስጥ እንዳንዘፈቅ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል። በሌላም ሥፍራ *"እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠትን ካወቃችሁ፥ በሰማያት ያለው አባታችሁ <u>ለሚለምኑት</u> እንዴት አብልጦ መልካም ነገርን ይሰጣቸው?"* (ማቴ 7፥11) ስለሚል እንለምን እንጂ እግዚአብሔር ይሰጣል።

በዘሌ. 22፥29 ላይ "የምስጋናንም

# መትጋት ወይስ መባከን?

አገልጋይ እግዚአብሔር በሰጠው አደራ ላይ ብቻ በማተኮር ያልተሰላቸ ትጉ አገልግሎት ለማበርከት እንዲችል ራሱን ካላስፈላጊ መባከኖች ሰብሰብ ማድረግ ይኖርበታል። መባከንና መትጋት ፍጹም የተለያዩ ናቸው። አንዳንድ ጊዜ የመባከናችን ብዛት ትጋት ተደርጎ መቆጠር የለበትም። ለየትኛው ቅድሚያ መስጠት፣ የትኛውን ማስከተል፣ ለየትኛው አብላጫውን ጊዜ መስጠት፣ ለየትኞቹ ደግሞ ትርፍ ጊዜ ካለ ማስተናገድ የሚለው ተለይቶ ካልታወቀ ሁሉንም እየነካኩ በአንዱም ፍሬያማ ሳይኮን ዕድሜ ሊያልፍ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ብዙም የማይጠብቃቸው ነገሮች ላይ ጊዜንና አቅምን አሟጦ ጨርሶ እንደ ወንጌል አገልጋይ እግዚአብሔር እንዲተኮርበት የፈለገውን አገልግሎት ለመፈጸም አቅምም ሆነ ጊዜ ሊጠፋ ይችላል። ለዚህ ሳይሆን አይቀርም ነቢዩ ኢሳይያስ "... እኔ ግን በከንቱ ደከምሁ፥- ምንም ጥቅም ለሌለውና ለከንቱ ጉልበቴን ፈጀሁ፤" ያለው። (ኢሳይያስ 49፥3-4)

ሁለቱ እህትማማቾች ማርያምና ማርታ ኢየሱስን ለማስደሰት የተጠመዱበት አገልግሎት ነበራቸው። ማርያም በኢየሱስ እግር ሥር ተቀምጣ፣ ሁለንተናዋን ሰጥታ ቃሉን መስማትን ምርጫዋ አደረገች። ማርታ ኢየሱስን ለማስተናገድ በሚያስፈልጉ የጓዳ ሥራዎች ተጠመደች።

በአንድ በኩል እንደ ማርያም እርሷም ኢየሱስ እግር ሥር መቀመጥን ሳትፈልግ አልቀረችም። በሌላ በኩል እንደምንም ተንጎዳጉዳ ለኢየሱስ የሚቀርብ ነገር ማቅረብ ብትፈልግም አልሞላ አላት። ውስጥዋ አላረፈምና እህትዋን ከሰሰች። ኢየሱስ ይኸንን አየና "ማርታ ማርታ በብዙ ነገር ትጨነቂአለሽ፣ ትታወኪማለሽ የሚያስፈልገው ግን ጥቂት ወይም አንድ ነገር ነው፤ ማርያምም መልካም ዕድልን መርጣለች ከእርስዋም አይወሰድባትም አላት።" (ሉቃስ 10፥38-42) በዚያ ወቅት ጌታ ኢየሱስ ወደእነዚህ እህትማማቾች ቤት ሲመጣ ፈቃዱና ሃሣቡ ቁጭ ብለው እንዲሰሙት ብቻ ነበር። ማርያም ያንን ፈቃድ በማወቋ ዕድለኛ ተባለች። ከዚያ ፈቃድ ውጪ ያለው እንቅስቃሴ ደግሞ መባከን ተባለ። ■

ምንጭ፥- በእግዚአብሔር የተጠራ አገልጋይ - ከጅምር እስከ ፍጻሜ | ቢሾፕ ደጉ ከበደ

... መዝሙርን ከምንጩ የቀጠለ

*መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ስትሠዉ እንዲሠምርላችሁ ሠዉለት"* ይላል። ስለዚህ መዝሙር በጸጋ የሆነና እግዚአብሔር የሚቀበለው፤ ቅዱሳንም የሚታነጹበት ይሆን ዘንድ ጸጋን ለመቀበል ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት ከመቅረብ ውጪ ሌላ አቋራጭ መንገድ የለም። የተወሰነ ጥገና (ማሻሻያ) የተደረገለት ከዓለም የተወሰደ የመዝሙር ዜማ፣ ቃላት ወይም መሣሪያ አጨዋወት በእግዚአብሔር ፊት የሚሰምር መስዋዕት አይሆንም፣ ቅዱሳንንም አያንጽም ደግሞም ከጊዜ በኋላ መገለጡ (መታወቁ) አይቀርም።

በ1ኛ ሳሙ 15፥1-23 እግዚአብሔር ወደ ሳኦል ሳሙኤልን ልኮ *"... አሁንም ሄደህ አማሌቅን ምታ፣ ያላቸውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ፣ አትማራቸውም ወንዱንና ሴቱን ብላቴናውንና ህጻኑን፣ በሬውንና በጉን፣ ግመሉንና አህያውን ግደል" አለ። ሳዖልና ሕዝቡ ግን የእግዚአብሔርን ቃል አልሰሙም አማሌቃውያንን እና ያላቸውን ፈጽመው አላጠፉም፤ ምናምንቴዎችን አጠፉ ነገር ግን ለመልካካሞቹ ራሩላቸው።"* ይህን ለማድረጋቸው በአይናቸው ፊት ጥሩ ምክንያት የሆነላቸው ነገር ነበረ። ይኸውም በ1ኛ ሳሙ 15፥20 *" ሳዖልም ሳሙኤልን፥- የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቻለሁ ... ሕዝቡ ግን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር በጌልጌላ ይሠው ዘንድ ከእርሙ የተመረጡትን በጎችንና በሬዎችን ከምርኮው ወሰዱ አለው"* ይላል። ስለዚህ እግዚአብሔር አጥፉት ያለውን ነገር ያለማጥፋታቸው ምክንያት ከእርሙ የተመረጡትን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ የማቅረብ ፍላጎት ነበር። ነገር ግን ይህ መልካም መስሎ የታያቸው ነገር እግዚአብሔርን አላስደሰተውም፤ እንዲያውም ከዚህ የተነሳ ሳዖል በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንዳይሆን እግዚአብሔር ናቀው። ስለዚህ ለስሜታችን መልካም የሆነ፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ የሌለበት ነገር ከሆነ ከስሜታችን ይልቅ ጌታን ደስ ልናሰኘው ይገባልና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመርን እንድናደርግ ያስፈልጋል።

በመጨረሻም የቤተክርስቲያን መዝሙሮችና የመዝሙር መሣሪያ አጨዋወቶች የተቀደሱ (የተለዩ)፣ ከዓለም ያልተቀዱ እና የራሳቸው ቃና ያላቸው እንዲሆኑ እንመኛለን። ይህ ምኞት የሚሳካበት መንገድ ግን የተገለጠ ነው። ይኸውም፥- የቤተክርስቲያን ዘማሪዎች ሌሎችን እያደመጡ ከዚያ መቅዳትን ትተው ዝማሬን ከእግዚአብሔር ይቀበሉ ዘንድ ቃሉን ዘወትር ቢያነቡ፣ በጸሎት ቢተጉና በቅድስና ሕይወት ቢኖሩ መልካም ነው እንላለን፤ ጌታ ኢየሱስ በነገር ሁሉ ማስተዋልን ይስጠን። አሜን። ■

# አንደኛውን ለመገንባት ሌላውን አታፍርስ

ስለ አንድ ነገር አስፈላጊነት ለመስበክ ሲፈልጉ ሌላውን አስፈላጊ ነገር ማፍረስ በብዙ ሰባኪዎች ዘንድ የሚታይ ድክመት ነው። ለምሳሌ የመንፈስ ቅዱስን አሠራር አስፈላጊነት ሲሰብኩ መንፈስ ቅዱስ እንጂ ቃሉ ዋጋ የሌለው ፊደል ብቻ ነው፤ ወዘተ ... በማለት ያቀርባሉ። ሰዎችን ለመንፈስ ቅዱስ ትኩረት እንዲሰጡ መስበኩ ባልከፋም፤ ሆኖም በአንጻሩ ትልቅ ሥራ ያለውን የእግዚአብሔርን ቃል ከንቱ አደርጎ ማቅረብን ምን ይሉታል? እነዚህ ሰባኪዎች ነገ ስለ እግዚአብሔር ቃል አስፈላጊነት መስበክ ቢፈልጉ የጣሉትን እንዴት ሊያነሱት ነው? ቃሉስ ትናንትና ጥለኸኛል ባንተ አልነሣም ቢላቸውስ?

አንዳንዶች ስለ ሃሰተኛ መናፍስት ለማስተማር ሲሉ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችንም አቅልለው ቃሉ የሰጣቸውን ቦታ ነፍገውና ዝቅ አድርገው ይናገራሉ፤ ነገ ስጦታዎቹ በቤተ ክርስቲያን እንዲሠሩ ሲፈለጉ በምን አንደበት ሊጸልዩ ነው? የተገነባውን ሳያፈርሱ ሌላውን መገንባት ይቻላል፤ ይህ ካልሆነ ግን ሰሚም ግራ ይገባዋል፤ ሁሉን ይዞ ሚዛኑን ጠብቆ ማደግም ይሳነዋል፤ትናንት የጨበጠውን ዛሬ እየጣለ ዛሬ የጨበጠውን ነገ እየጣለ በእጁ የሚይዘው አንዳች የሌለው ሆኖ ይቀራል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ከሮሜ ምዕራፍ 3 እስከ 8 ባለው ክፍል በአዲስ ኪዳን ስለተገኘው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ሲያስተምር ጸጋውን ከሕግ ጋር በማነጻጸር የሕግን አስቸጋሪነት ቢገልጥም ሰዎች ሕግን ኃጢአት አድርገው እንዳይመለከቱ *"ሕግ ኃጢአት ነውን? አይደለም... ሕግ መንፈሳዊ እንደሆነ እናውቃለንና። ... ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም...* "(ሮሜ. 6፥2፣7፥7፣14) በማለት ሰዎች ሕግን ጥለው በጸጋ በማመካኘት በኃጢአት እንዳይጸኑ አንዱን በአንዱ እየገነባና እያጸና ሲሰብክ እናያለን። አንዱ ቃል ከሌላው ቃል ጋር የተገጣጠመ ነው ሕይወት የሚሰጠው፤ የሚያድገውም። ስለዚህ አንዱን ለመገንባት እግዚአብሔር የገነባውን ማፍረስ ወንጀል ስለሆነ ሚዛናዊ አቀራረብ ይኑር። ■

ምንጭ፥- አገልጋይና የእግዚአብሔር ቃል | ቢሾፕ ደጉ ከበደ

## ዶክትሪን

# የመረዳት ባለጠግነት

✍ ቢሾፕ አዲሱ በሪሶ | የምዕራብ አርሲ ቅርንጫፍ ሰበካ ኃላፊ

“ልባቸው እንዲጸናና በፍቅርም ተባብረው በማስተዋል ወደሚገኝበት ወደ መረዳት ባለጠግነት ሁሉ እንዲደርሱ የእግዚአብሔርንም ምስጢር እርሱም ክርስቶስን እንዲያውቁ እጋደላለሁ” (ቆላ.2፥2) በዚህ ቃል ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ “የመረዳት ባለጠግነት” ብሎ የጠቀሰው ክርስቶስን ማወቅ (የክርስቶስን ማንነት በሙላት መረዳትን) ነው። በ1ኛጴጥ. 3፥18-19 ላይም “ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመጸኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ። በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩት ነፍሳት ሰበከላቸው” ይላል። ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን (አቀረበን) ማለት አምላክ ወደ ሌላው አምላክ አቀረበን ማለት ነውን? ፈጽሞ አይደለም ብቻ ሳይሆን አይባልምም።

በዮሐ.1፥18 “እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም” ብሎ በዮሐ.6፥46 ላይ ደግሞ “አብን ያየ ማንም የለም ከእግዚአብሔር ከሆነ በቀር እርሱ አብን አይቶአል” ይላል። በ1ኛጢሞ.6፥15-16 ደግሞ “ብፁዕና ብቻውን የሆነ ገዥ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ያሳያል። እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳን አላየውም ሊያይም አይቻለውም  ለእርሱ ክብርና የዘላለም ኃይል ይሁን አሜን” ሲል በመለኮትነቱ ማንም ከቶ ያላየውና ሊያየውም የማይቻለው፤ መላዕክት እንኳን ዓይኖቻቸውን በክንፎቻቸው ሸፍነው የሚያገለግሉት ብቻውን የሆነ ገዥ ሰዎችን ለማዳን ወደዚህ ዓለም በሥጋ የመጣ መሆኑን ያስረዳል።

በዮሐ.14፥6 “...በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም” ሲል አንዱ አምላክ በር ላይ ቆሞ እየፈተሸ ለሌላው አምላክ ያሳልፋል ማለት ሳይሆን በዕብ.10፥19 በተገለጸው መሠረት እግዚአብሔር (አብ) በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል ወደ ራሱ አቀረበን፤ ታረቀን ማለት ነው። ቀጥሎ የተጠቀሱትን የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎችም በማስተዋል እንመልከታቸው።

1ኛጢሞ.3፥16 “በሥጋ የተገለጠ” ሲል ማን ነው የተገለጠው? እግዚአብሔር። በምን ተገለጠ? በሥጋ።

ዕብ.1፥1-3 “ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን።” (በልጁ ተገለጠ)

2ኛቆሮ.5፥19 “እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና በደላቸውንም አይቆጥርባቸውም ነበረ።”(በክርስቶስ ተገለጠ)

ሐዋ.17፥31 “እግዚአብሔር ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለው” ይላል። እነዚህ የተጠቀሱት አገላለጾች ሁሉ ማለትም በሥጋ፣ በክርስቶስ፣ በልጁ፣ ባዘጋጀው ሰው ተብሎ የተጠቀሱት ዓለምን ለማዳን ወደዚህ ዓለም ሲመጣ ቃሉን ሥጋ አድርጎ መምጣቱን እና አብ የተገለጠበትን ሰማያዊ ሥጋ (ሰውነት) የሚገልጹ ናቸው። ቀደም ሲል በ1ኛጴጥ.3፥18 እንደ ተመለከትነው እግዚአብሔር በሥጋ ሲገለጥ የሚታይና የማይታይ፤ የሚሞትና የማይሞት ባህሪያትን ይዞ እንደመጣ በግልጽ ያሳየናል። ሮሜ 1፥21 ም እንዲህ በማለት ይህንኑ እውነታ ያረጋግጥልናል። “... የማይታየው ባህርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና” በማለት የሚታይና የማይታይ ባህሪያት እንዳሉት ያረጋግጣል። የማይታይ አምላክ በሚታይ ሰውነት ተገለጠ፤ የማይሞት ዘላለማዊ አምላክ ሞትን ለዘለዓለም ለመዋጥ(ለመሻር) በሚሞት አካል ተገለጠ ማለት ነው።

ቆላ.1፥22 “እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ በፊት የተለያችሁትን ክፉ ሥራችሁንም በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ።”

የዘላለም ሕይወት (መዳን) የተቋጠረው አመጣጡንና ማንነቱን ለይቶ በማወቅ ላይ ነው። ዘካ.6፥13 “በዙፋኑም ላይ ተቀምጦ ይነግሳል፤ በዙፋኑም ላይ ካህን ይሆናል” ይላል። በንጉሥነቱ (በመለኮትነቱ) ፈራጅ፤ በካህንነቱ (በልጅነቱ) አስታራቂ አማላጅ ነው ማለት ነው። እግዚአብሔር በሥጋ የተገለጠበት ምክንያት በሰማይ ሆነ በምድር በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ቆሞ ለማስታረቅ የሚበቃ ጻድቅ ሰው(ሥጋ) ስለሌለ ነው። ስለዚህ ነው በዕብ.10፥5 “ስለዚህ ወደ ዓለም ሲገባ መስዋዕትንና መባን አልወደድህም ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ...” ያለው። በሮሜ.3፥11 ላይ ደግሞ “ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ...” ሲል እግዚአብሔር የራሱን ጻድቅ ማዘጋጀት እንደነበረበትና ቃሉን ሥጋ አድርጎ በሰው ቦታ ቆሞ መማለድና ማስታረቅ የሚችል ሥጋ ለብሶ መምጣት ግድ እንዳለው ያሳየናል።

በኢሳ.59፥16-17 ይህንኑ ሲያጸና “እግዚአብሔርም አየ፤ ፍርድም ስለሌለ ተከፋ፤ ሰውም እንደሌለ አየ፤ ወደ እርሱ የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ፤ ተደነቀም፤ ስለዚህ የገዛ ክንዱ መድኃኒት አመጣለት፤ ጽድቁም አገዘው። ጽድቅንም እንደ ጥሩር ለበሰ፤... በቀልንም እንደ ልብስ ለበሰ፤ በቅንዓትም መጎናጸፊያ ተጎናጸፈ” ይላል። ስለሆነም

ለማስታረቅ በተዘጋጀ ሰው(ሰውነት) ወደ ሰማይ እጆቹን ዘርግቶ አባት ሆይ ...ብሎ ቢጸልይ፣ ቢማልድ ምንም አይገርምም። ሁሉ በሁሉ ነው ማለት አማላጅም ተማላጅም ነው ማለት ነው። ሰውም እንደሌለ አየ ማለት በኃጢአተኛው ሰውና በቅዱሱ አምላክ መካከል ቆሞ ለማስታረቅ ብቃት ያለው ሥጋ የለም ማለት ነው እንጂ ኃጢአተኛው ሰውማ ምድርን አጣብቦአታል። በእኛ ቦታ ቆሞ ስለ እኛ በጸለየው ጸሎትና ምልጃ የማይሰናከል ሰው ብፁዕ ነው። በግነቱ አንበሳነቱን፣ ካህንነቱ ንጉሥነቱን፣ ልጅነቱም የዘላለም አባትነቱን (አብ መሆኑን)፣ በእኛ ቦታ ቆሞ መጸለዩ፣ መማለዱ፣ የራሱን ቦታ ወይም ማንነቱን አይጋርዱብን። እርሱ (ኢየሱስ) ብቻውን የሆነ አምላክና መድኃኒታችን ነው።

በእኛ እንኳን ጥያቄ የማይፈጥሩብን አባባሎች እንዴት ሁሉን የሚችል አምላክ ሲጠቀምባቸው ጥያቄ ይፈርሩብናል? ለምሳሌ፦ በ1ኛተሰ. 5፥23 "የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም፣ ነፍሳችሁም፣ ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ" ይላል። መንፈስ ነፍስና ሥጋ ተብሎ ሦስቱ ተጠቅሰው "ይጠበቁ" በሚል በብዙ ቁጥር ስለ ተዘጋ አንድ መሆናችንን ተጠራጥረን እናውቃለን ወይ?

እንዲሁም በሉቃ.12፥16-20 በተጻፈውስ ታሪክ እርሻው ፍሬያማ የሆነለት ባለጠጋው ሰውዬ፦ "ነፍሴን አንቺ ነፍሴ ለብዙ ዘመን የሚቀር ብዙ በረከት አለሽ፣ እረፊ፣ ብዪ፣ ጠጪ፣ ደስ ይበልሽ እላታለሁ አለ" ይላል። ሰው ራሱን አንቺ፣ ብዪ፣ ጠጪ፣ ደስ ይበልሽ፣ እላታለሁ እያለ መጥራት ከቻለ ሁሉን ቻዩ አምላክ አንድ ጊዜ "አባቴ"፣ ሌላ ጊዜ "የምወደው ልጄ" ... ብሎ ቢናገር ለምን ጥያቄ ይፈጥርብናል? ኢሳ.9፥6 እንደሚገልጸው ኢየሱስ ክርስቶስ ወንድ ልጅና የዘላለም አባት (አብና ወልድ) ሆኖ ነው የመጣው። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ በአመጣጡ ሕፃን በማንነቱ ኃያል አምላክ ነው፤ በአመጣጡ ልጅ (ወልድ) በማንነቱ የዘላለም አባት (አብ) ነው። ባይሆንማ ኖሮ እንዴት ስሙ ከስም ሁሉ በላይ የሆነ ስም ይሆናል? እንዴትስ "መዳን በሌላ በማንም የለም..." (ሐዋ. 4፥12) ሊባልለት ይችላል? መዳንም በሌላ በማንም የለም የተባለለት ከእርሱ ሌላ አምላክ ስለሌለ አብ፣ ወልድም መንፈስ ቅዱስም እራሱ ስለሆነና ሁሉ በሁሉም ስለሆነ ነው። ኢየሱስ የተባለው የመለኮት ስምም ከስም ሁሉ በላይ የሆነ ስም የሆነበት (ፊልጵ. 2፥9) ምክንያት የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ስም ስለሆነ ነው።

ዛሬም ይህን የመዳን ዕውቀት በማጣት ነው ብዙዎች የአማኝ ከሀዲዎች እየሆኑ በእምነት እየጠፉ ያሉት። (ማለትም ሃይማኖት አለን እያሉ አምላክን አማልክት የሚያደርጉት።) በኢሳ.8፥13 "ነገር ግን የሠራዊትን ጌታ እግዚአብሔርን ቀድሱት፤ የሚያስፈራችሁና የሚያስደነግጣችሁም እርሱ ይሁን። እርሱ ለመቅደስ ይሆናል ለሁለቱ ለእስራኤል ቤቶች ለእንቅፋት ድንጋይና ለማሰናከያ ዓለት በኢየሩሳሌምም ለሚኖሩ ለወጥመድና ለአሽክላ ይሆናል። ብዙዎችም በእርሱ ይሰናከላሉ፤ ይወድቁማል፤ ይሰበሩማል፤ ይጠመዱማል፤ ይያዙማል" ይላል።

እነዚህ የተቆጠሩትና የሚያስፈሩት ፍርዶች መሰናከል፣ መውደቅ፣ መሰበር፣ መጠመድና መያዝ ሁሉ የሚሆነው የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለመቅደስ ሲሆን (ማለትም በሥጋ ሲገለጥ) ነው፤ የዚህ ሁሉ ምክንያት ደግሞ የክርስቶስን ማንነት አለማወቅ ነው። ይህ ትንቢት ተፈጽሞ እግዚአብሔር በሥጋ ሲገለጥ (የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለመቅደስ ሲሆን) ይመጣል ብለው የጠበቁት የገዛ ወገኖቹ (እስራኤላውያን) እንኳን ተሰናከሉበት፤ ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ አደረግህ አሉትና (ዮሐ. 10፥33) ሰቅለው ገደሉት። ዛሬም ማንነቱን አለማወቅ ከቶ አላወቅኋአችሁም እናንተ ዓመጸኞች... (ማቴ. 7፥23) እንዳያስብል ኢየሱስ በሥጋ የተገለጠው አንዱና ብቸኛው አምላክ አብ መሆኑን በመረዳት ማመን አማራጭ የሌለው የመዳን ቁልፍ ነው።

በዮሐ.2፥19-22 "ኢየሱስም መልሶ ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀንም አነሳዋለሁ፤ ስለዚህ አይሁድ ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበረ፤ አንተስ በሦስት ቀን ታነሳዋለህ? አሉት። እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበረ።" "እርሱን እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን አስነሳው" ተብሎ በሐዋ.10፥40 እና በሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተጠቀሱት የሰውነቱን ቤተ መቅደስ አስነሳው ማለት ካልሆነ ምን ሊሆን(ሊባል(ይችላል? አምላክ ሞቶ በሌላው አምላክ እርዳታ ከሙታን ተነሳ ይባላልን?

ክርስቶስ ሞተ አብ ከሙታን አስነሳው ሲባል ኢየሱስ የመጣው ሊሞት የማይችል አምላክነቱን እንደያዘና ስለኃጢአተኞች ሊሞት በሚችል ሰውነት በመሆኑ በሰውነቱ መስዋዕት ከሆነ በኋላ በአምላክነቱ ለሰውነቱ ማለትም ለገዛ አካሉ ሕይወትን ሰጥቶ ተነሳ ማለት ነው (ዮሐ. 2፥19፣ 1ኛ ጴጥ. 3፥18)። በሌላ አነጋገር የክርስቶስ (የዚያ ሥጋ) መንፈስ ወይም ሕይወት አብ ስለሆነ "ሞተ" ማለት "ነፍሱን ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት አሳልፎ ሰጠ" ወይም "ነፍሱን ተወ" ማለት ሲሆን (ማር 15፥37, ማቴ 27፥50) "ከሙታን አስነሳው" ማለት ደግሞ በ1ኛ ጴጥሮስ መልእክት 3፥18 በግልጽ እንደተጻፈው "በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ" ማለት ነው።

በዮሐ.5፥19 ደግሞ እንዲህ ይላል፦- "ስለዚህ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም አላቸው እውነት እውነት እላችኋለሁ አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም"። ብሎ በቁጥር 20 ደግሞ "አብ ወልድን ይወዳልና የሚያደርገውንም ሁሉ ያሳየዋል..." ይላል። ከላይ እንደተጠቀሰው ወልድ (የእግዚአብሔር ልጅ) ማለት የአብ መገለጫ አካሉ (ሰውነቱ) ነው። ስለዚህ ነው የእግዚአብሔር ልጅ የተባለው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "እግዚአብሔር ልጅ" የሚል ፈጽሞ አልተጻፈም "የእግዚአብሔር ልጅ" እንጂ። አይደለም የሚል ካለ ሁሉን የማይችልና ሁሉን የማያውቅ በሌላ አምላክ ዕውቀትና ችሎታ እየታገዘ የሚሠራ ጥገኛ አምላክ አለ ሊል ነው? የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረን እውነት ግን "ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም" ማለት ሥጋ ያለ መለኮት ምንም ሊያውቅም ሊያደርግም አይችልም ማለት ሲሆን ይህም መለኮትንና የተገለጠበትን የሥጋ ሰውነት መለያየት እንደማይቻል ያስረዳል። በቆላስይስ 2፥9 እንደተጻፈውም የመለኮት ሙላት ሁሉ በሥጋው ሰውነት (በልጁ) ተገልጦ ይኖራል ማለት ነው።

በቁጥር 26 ላይ ደግሞ "አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና" ይላል። መለኮት (አምላክ) ከአምላክ ሕይወት አይቀበልም፤ ወይም ደግሞ መለኮት ለመለኮት ሕይወትን አይሰጥም። ይልቁንም የሕይወት ምንጭ የሆነው አንዱ አምላክ(መለኮት (መዝ 36፥9) በሥጋ ተገልጦ የዘላለምን ህይወት ለሰው ልጆች ይዞ ሲመጣ የዘላለምን ህይወት በሥጋው ሰውነት ላይ ወይም በልጁ ላይ እንዳስቀመጠ ያስረዳል እንጂ። ቃሉም በ1ኛ ዮሐ. 5፥11 እንደዚህ ይላል "እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው"። ስለዚህም ብቻውን አምላክ የሚሆን፣ በአጠገቤ ምንም አታድርጉ ብሎ ያስጠነቀቀ ቀናተኛው አምላክ በሥጋ ተገለጠ፤ አምላክና መድኃኒታችን ሆነ፤ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ አልነበረም፤ የለም፤ ለዘላለምም አይኖርም። (1ኛጢሞ.1፥17፣ ዘጸ. 20፥22፣ ይሁ.24-25)። ■

## ያዳናቸው ይናገሩ

# ታላቁ ስደትና ፍሬው

✍ ወ/ም ደሜ አበራ | ከአዳማ የሰሜን አጥቢያ

ታሪኩ 28 ዓመት ወደ ኋላ ይወስደናል፣ ቀኑ እለተ ሰንበት ግንቦት 2 ቀን 1984 ዓ.ም። በዚሁ እለት በቀድሞ ስያሜ በምዕራብ ሸዋ አዲስ ዓለም ወረዳ (በአሁኑ ኤጄሬ) በአረብሳና ኦዶ ቀበሌ ልዩ ቦታው ኦዶ ተብሎ በሚታወቀው መንደር በምትገኝ ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ይነሳል።

በወቅቱ የሸዋ ዙሪያ ሰበካ ኃላፊ የነበሩት ቢሾፕ ደጉ ከበደ ከአዋሽ ወንዝ ድፍርስ ውሃ ጠጥተው ጨጓራቸውን በጠና በታመሙበት የወንጌል አገልግሎት ካስገኛቸው ፍሬዎች የያያ፣ የሮጌ፣ የተጂ አጥቢያዎችን ተከትላ በመጨረሻ በተገኘችው በኦዶ የወንጌል ብርሃን መፈንጠቅ የጀመረው በ1983 ዓ.ም ነበር። በወቅቱ የነበረው የአካባቢው አገልጋይ ከሰበታ አካባቢ ወደዚህች መንደር መጥቶ የእውነትን ወንጌል ሲሰብክ ጥቂት ነፍሳት አምነው በኢየሱስ ስም ይጠመቃሉ፤ ቁጥራቸውም እያደገ መጣ። የ60 ዓመቱ አዛውንት የኦዶ ነዋሪ ወንድም እትቻ ብሩ ባለቤታቸው ባመኑ በዓመቱ ከነልጆቻቸው ያምናሉ። በዚያው ጊዜ የመጀመሪያ ልጃቸው ተማሪ ድሪርሳ የዚያው አካባቢ ነዋሪና የሥጋ ዘመዳቸው ከሆኑት ከነተማሪ ገቢሳ ፉንዳሳ ጋር በአዲስ ዓለም ከተማ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኙ ነበር።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ቤተሰባቸው በቁሱ በኩል የሐዋርያትን እምነት ሲቀበሉ ተማሪዎቹ ደግሞ ትምህርታቸውን በሚማሩበት በአዲስ አለም ከተማ ከፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ጋር ይገናኙና የአንድ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ይሆናሉ። ተማሪዎቹ ቀድሞ ከነበሩበት የወላጆቻቸው ሃይማኖት ወጥተው ወደ ፕሮቴስታንት እምነት ገብተው የሃይማኖቱን አስተምህሮ እየተከታተሉ ሳሉ ቤተሰቦቻቸው የሃሰት እምነት የተቀበሉ መስሏቸው ከሐዋርያት መንገድ ወደ ፕሮቴስታንት ለመመለስ ከአዲስ ዓለም ወደ ቤታቸው ይመጣሉ። ቤተሰቦቻቸውም ከአገልጋያቸው ጋር እንዲገናኙ ያደርጉአቸውና በቃሉ ላይ መነጋገር ይጀምራሉ፤ ከብዙ ክርክርም በኋላ ጌታ ቃሉን ያበራላቸውና በእውነት ወንጌል አምነው በኢየሱስ ስም ለኃጢአታቸው ስርየት ተጠምቀው በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው እውነተኛውን መዳን ይቀበላሉ። እንግዲህ ተማሪዎቹ እንደ እነርሱ የዓለም ትምህርት ሳይማሩ ግን የእውነት ወንጌል በርቶላቸው መዳንን የተቀበሉ ቤተሰባቸውን ለመመለስ መጥተው ለራሳቸውም በእውነት ወንጌል  ተማርከው ይቀራሉ። ከዚያም መስከረም 1984 ዓ.ም በጎፋ በተደረገው የአገልጋዮች ስብሰባ ላይ በቢሾፕ ደጉ ከበደ የተሰጠውን የአገልጋዮች ትምህርት ከወሰዱ በኋላ ወንድም ድሪርሳ የኦዶ አጥቢያ፣ ወ/ም ብርሃኑ የሮጌና ወ/ም ገቢሳ የያያ አጥቢያ አገልጋይ ሆነው ይመደባሉ።

ከዚያም “ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም” (ፊል.1፥29) ተብሎ በእግዚአብሔር ቃል እንደተጻፈ የኦዶ ክርስቲያኖች የመዳናቸው ምልክት የሆነው ታላቅ ስደት ይነሳባቸዋል። በኦዶ የተለኮሰው የወንጌል እሳት በአካባቢው ወደሚገኙ ሌሎች ቀበሌዎች በፍጥነት እየተዛመተ ሲሄድ እያንዳንዱ ምእመን እለት እለት መስቀሉን ተሸክሞ መመላለስ ግድ ሆነበት። በተለይ በ1983 ዓ.ም በአገሪቱ በተደረገው የመንግስት ለውጥ ምክንያት የተፈጠረውን ህገ ወጥነት እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ሕዝቡ በምእመናኑ ላይ ልዩ ልዩ ዓይነት መከራን ያደርሱባቸው ነበር። ይህ ሁኔታ ቀስ በቀስ እያደገ መጥቶ ምእመናኑን ከምድረ ገጽ እናጠፋለን እያሉ በአደባባይ ከመናገር አልፈው ከስምንት ቀበሌ የተውጣጡ የጥፋት ሃይሎች ተደራጅተው ውጥናቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚሰባሰቡበትን ቀንና ቦታ ይቆርጣሉ።

ለስደቱ ውጥን መነሻ የሆነው ወንድም ድሪርሳ እና እህት አለሚቱ ግንቦት 2 ቀን 1984 ዓ.ም ይጋባሉ የሚል ወሬ በአሳዳጆቹ ዘንድ መሰማቱ ነበር። ይሁን እንጂ የእህት ዓለሚቱ ቤተሰቦች ያላመኑ ስለነበሩ “ቆንጤ” ልጃችን ስላልሆነች የምንድራት ልጅ የለችንም “ቆንጤ” አማችም አንፈልግም በማለት ጋብቻው እንዳይፈጸም ያስተጓጉላሉ። “ቆንጤ” በዚያ አካባቢ በተለምዶ “ጴንጤ” ተብሎ በጥላቻ የሚጠሩት አማኞችን የሚጠሩበት ቃል ነበር። በዚህ ምክንያት ጋብቻው ለሌላ ጊዜ እንዲዘገይ ተደረገ። ይሁን እንጂ የሰርጉ ቀን ለሌላ ጊዜ መዛወሩን አሳዳጆቹ ስላላወቁ ክርስቲያኖቹን ለማጥፋት የተቆረጠው የጥፋት ቀጠሮ እንደተጠበቀ ነው።

በሌላ በኩል አሳዳጆቹ ያዘጋጁላቸውን የስደት ጽዋ ያላወቁ የኦዶ ክርስቲያኖች በመጋቢያቸው በቄስ ድሪርሳ አስተባባሪነት በበቾ አካባቢ የመጀመሪያ የሆነውን የእግዚአብሔር ጉባኤ ለማዘጋጀት በከፍተኛ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛሉ። የጥፋት ልጆች የአመጽ ተግባራቸውን ለመፈጸም ሲዘጋጁ፣ የምህረት ልጆች ደግሞ ለፈጣሪያቸው አምልኮ ለማቅረብ በተመሳሳይ ቀን ለግንቦት 2 ቀን 1984 ዓ.ም ቀጥረው በተለያዩ አካባቢ ለሚገኙ ክርስቲያኖችም ጥሪ አድርገዋል። ለጉባኤው ስኬት ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ ነው፣ ወንድም እትቻ ብሩ ለጸሎት ቤት መስሪያ የሚሆን ሁለት ቀርጥ ቦታ ከእርሻ መሬታቸው ቆርሰው ለቤተክርስቲያኗ ሰጥተዋል፣ በአካባቢው

የሚገኙ ወንድሞች በሩቅ የሚገኙ ሳይቀሩ ለጸሎት ቤት መስሪያ የሚውል እንጨት እያመጡ ቤቱ ዓርብና ቅዳሜ ተሰርቶ እስከ ግድግዳው ተጠናቅቆ ለእሁዱ አገልግሎት ዝግጁ ተደርጓል። በጊዜው የኦዶ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የነበረው ወንድም ድሪርሳ በወቅቱ የአካባቢው ንዑስ ተጠሪ የነበረውን አገልጋይ ዓርብ ዕለት ከሰበታ አምጥቶ ሮጌ አሳድሮ ቅዳሜ ወደ አመሻሹ ላይ ወደ ኦዶ ይዞት ይመጣል። የእነ ፋንዳሳና ወንድም እትቻ ቤተሰቦች ከተለያዩ ቦታዎች በተለይ ከከተማ አካባቢ የመጡትን እንግዶች በፍቅር ተቀብለው እያስተናገዱ ይገኛሉ። ከእንግዶቹም አንዱ ከአዲስ ዓለም ከተማ ተጋብዤ የመጣሁ የዚህ ታሪክ ዘጋቢ ወንድም ደሜ አበራ የወቅቱ ብላቴና የ5ኛ ክፍል ተማሪ ስሆን በወቅቱ ገና አልተጠመቅሁም ነበር።

እንግዲህ የተዘጋጀልንን ታላቁን የስደት ጽዋ የምንጎነጭበት ቀንና ሰዓት ደረሰ፤ ግንቦት 2 ዕለተ ሰንበት። ጠዋት ምዕመናን ከተለያዩ አካባቢዎች በበቾ ብቸኛውና የመጀመሪያ በሆነው አዲሱ የጸሎት ቤት ተሰብስበው በአምላካቸው ፊት ተንበርክከዋል። ወንድም እትቻ ለጸሎት ቤቱ መስሪያ እንዲውል ቦታ የሰጡበት የውል ሰነድ በሶስት ቅጂ ተዘጋጅቶ አንዱ ለቀበሌው ሊቀመንበር መግባት ስለነበረበት እኔና ሌሎች ሶስት ወንድሞች ደብዳቤውን አድርሰን እስከምንመጣ ሌላው ወንድም ፕሮግራም እየመራ እንዲቆይ ይወሰናል፤ እኛም ወደ ቀበሌው ጉዞ ጀመርን።

ስንሄድም አሳዳጆቻችን የሆነ ጥጃ ሞቶ ጉድጓድ ቆፍረው እየቀበሩ ነበርና ከዚያው ኋል እያነሱ ወደ እኛ መወራወር ይጀምራሉ፣ ወንድም ድሪርሳ የሚወረወረው ሌሎቻችንን በተለይ ቄሱን እንዳይመታው በሚወረወረው አቅጣጫ ሆኖ ይከልለናል፣ ሰዎቹ አብዝተው መወራወራቸውን ቀጠሉ፣ ወዲያም ከእነርሱ ውስጥ የአንድ ባለ ውቃቢ ልጅ ቁሙ! አለን። እኛም እሽ ብለን ቆምን። ቆመን ስንጠብቃቸው ወደ እኛ እየመጡ ሳሉ በመካከል አንዱ የባለ ውቃቢውን ስም እየጠራ ኡኡ (የማህበር ያለህ) ድረሱልን እከሌ ሞቷል ብሎ ጩኸቱን ሲያቀልጥ አስቁመውን ወደ እኛ እየመጡ የነበሩት ምንም ሳያደርጉን ሁሉም ሞተ ወደተባለበት ግለሰብ ቤት ይሄዳሉ፤ ጩኸቱ ለጸቡ መነሻ እንዲሆን ሆን ተብሎ የተቀናበረ ድራማ እንጂ በእርግጥ ባለውቃቢው ሞቶ አልነበረም።

ይህን ተከትሎ ስደቱ በሁለት አቅጣጫ ተከፈተ፤ አንደኛው በጩኸቱ ምክንያት ከእኛ ወደ ጸሎት ቤቱ በተመለሱት ቡድን የተከፈተው ሲሆን፣ ሌላኛው እኛ ደብዳቤውን ማድረስ ትተን ስንሸሽ በተከተሉን የተደረገው ነው። ቀድሞውኑ በተጠንቀቅ ሲጠባበቅ የነበረው የአካባቢው ሕዝብ ጩኸቱን ሲሰማ ከልጅ እስከ አዋቂ ከየቦታው አዲስ ወደተሰራው የማምለኪያ ስፍራችን መጥተው ምዕመናኑን እንዳልነበሩ ያደርጋሉ፣ እያሳደዱ በእጃቸው በያዙት ሁሉ በከፍተኛ ደረጃ ይደበድቧቸዋል። የጸሎቱንም ቤት ወዲያው አፍርሰው ቦታው እንዳይታወቅ ያርሱታል፤ አብዛኞቹን ይዘው አረብሳ እስር ቤት ያስገቧቸዋል።

በድብደባው ብዙ ክርስቲያኖች ከፍተኛ ጉዳት ይደርስባቸዋል። አንዲት በእድሜ የገፉ እህት ሎሚ የሚባሉ እናት ከከባድ ድብደባ የተነሳ አረብሳ እስር ቤት እንደገቡ የእስር ቤቱ ጠባቂዎችና ሕዝቡ እያዩአቸው ሕይወታቸው አለፈ። የ60 ዓመቱ አዛውንት ወንድም እትቻም በገጀራና በዱላ ጭንቅላታቸው ላይ ብዙ ቦታ ተመተው መሬት ላይ ተዘርረዋል፤ እጃቸውንም ድቅቅ አድርገው ሰብረዋቸው ሞተዋል ብለው ነፍሷ እስከምትወጣ ድረስ እንደ እባብ ቀጥቅጠዋት ከሄዱላት በኋላ ጌታ ሃይሉን ሰጥቷት ከዚያ ተነስታ ወደ ተጂ ሄዳ ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ተሳፍራ ጎፋ ቤተክርስቲያን ሄዳ ክስተቱን ሪፖርት ታደርጋለች። በዚህ የተነሳ ጉዳዩ በመላ ኢትዮጵያ በሚገኙ በአብዛኛው ሐዋርያት ምእመናን ዘንድ ተሰማ፣ የቄሱም ቤተሰቦች ሰምተው እጅግ ተጨነቁ።

ሌሎችም ምእመናን በተለያየ ደረጃ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። አንዳንዶቹም ሸሽተው በየስርቻው ተደብቀዋል። ከስደቱ ሸሽተው ጎተራ ውስጥ ለመደበቅ የሞከሩት በአጋጣሚ ሁሉም ጎተራዎች በእህል ተሞልተው ስለነበረ አማራጭ ሲያጡ እዚያው ከስራቸው እስከ ማታ ተደብቀው ሌሊት የወጡም አሉ። ሌሎችም ቤት ውስጥ ተደብቀዋል።

አሳዳጆቹ በወንድም እትቻ ቤት የተደበቁትን ከነቤቱ በእሳት ለማጋየት ይወስናሉ። ይሁን እንጂ ይህን ሲያስቡ

> **በዚህ የተነሳ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ይህን ታሪክ የሚያውቁ በኦዶና አካባቢዋ የሚገኙ የቀድሞ ነዋሪዎች ስለ ሐዋርያት እምነት ተከታዮች መናገር ይፈራሉ።**

ሜዳ ላይ ጥለዋቸው ይሄዳሉ። አዛውንቱ በወደቁበት ደማቸው እንደ ጎርፍ እየፈሰሰ የሚያነሳቸው ጠፍቶ እስከ ማታ በጌታ ጥበቃ በሕይወት ይቆያሉ።

ሮጌ ከሚባል አካባቢ የመጣች የሚቷ ልጅ የሆነችው እህት አበቡ ዓለሙም ልቧ ላይ ተመትታ ራሷን ስታ የሆነ ጉድጓድ ውስጥ ወድቃ ተኝታለች፤ ፕሮግራም ሲመራ የነበረው ወንድም በከፍተኛ ድብደባ ተጎድቷል፣ የሆነውን በቅጡ ያላወቀው ወንድም ንጉሴ የሚባለውም አገር ሰላም መስሎት ገና ከቤቱ ወደ አዲሱ ጸሎት ቤት እየመጣ ሳለ መንገድ ላይ አግኝተውት እስከሚበቃው ደብድበውት ከንፈሩን ይቀድዱታል። እህት ጽጌ የምትባል ከግንጪ ከተማ የመጣች ወጣት በከፍተኛ ደረጃ ተመትታ ጉድጓድ ውስጥ ወድቃ ባለችበት ሆና በእግዚአብሔር መንፈስ ተሞልታ ሃሌ ሉያ ስትል ደብዳቢዎቹ በኦሮሚኛ ቋንቋ በባለጌ ቃል እየተሳደበች መስሏቸው ጭራሽ እንዲህ ትሳደባለች እንዴ በማለት በአጋጣሚ የባለ ውቃቢው ቤት ከጎኑ ስለነበረ አብሮ እንዳይቃጠል ፈርተው ይተዉታል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በአረብሳ እስር ቤት ውስጥ ጌታ ኢየሱስ በአህዛብ ፊት አንድ ተአምር ሰራ። ቆንጤ ቆንጤዎች ምን ይመስሉ ይሆን እያሉ ልዩ ፍጥረት መስለዋቸው ሊመለከቱአቸው ሰዎች ከያሉበት ወደ አረብሳ እስር ቤት እየተመሙ ይገኛሉ። ሰው በሰው ላይ እየተንጠራራ እያዩአቸው ባሉበት እነርሱ ግን በድብደባው በጣም የተጎዱ ምእመናንና የሟች እህታቸውን አስከሬን ይዘው ተቀምጠዋል። ከመካከላቸውም እምነት የመጣለት አንዱ ተነስቶ በዙሪያው ተሰብስበው ለቆመው ሕዝብ እኛ የምናመልከው አምላክ ሁሉን የሚችል ኤልሻዳይ አምላክ ስለሆነ የሞተውንም ማስነሳት አይሳነውምና እናንተ ከዚህ ውጡልን እኛ በእርሱ ፊት ተንበርክከን ጸልየን እህታችንን ከሞት እናስነሳለን አላቸው። ሕዝቡ ግን እያሾፉባቸው በውኑ የሞተን ሰው ታስነሳላችሁ? እስኪ

እንያችሁ አድርጉት ይሉአቸዋል። ሕዝቡ እያዩ በጉልበታቸው ተንበርክከው ሲጸልዩ ጌታ ወዲያው ጸሎታቸውን ሰምቶ መለሰላቸው፣ ሚቿ ሕያው ሆነች፣ መሞቷ በአህዛብ ጭምር የተረጋገጠው ተነሳች። ምእመናኑ በታላቅ ደስታ ሀሴት ሲያደርጉ አሳዳጆቹ ግን ይህን ተአምራት አይተውም እንኳን እግዚአብሔርን አልፈሩም። እኚህ እህት ከዚያ በኋላ በወንጌል ሃይማኖታቸው ጸንተው ብዙ ዓመት ከኖሩ በኋላ በመልካም ሁኔታ አንቀላፍተዋል።

አሳዳጆቹ በጸሎት ቤቱ በነበሩት ምዕመናን ላይ እስከ ነፍስ ግድያ የሚደርስ ጉዳት ካደረሱ በኋላ ወደ እኛ ደግሞ ተመለሱ። ደብዳቤውን ማድረስ ትተን ከነበርንበት ቦታ የአንድ ሰዓት የእግር ጉዞ ወደሚወስደው ወደ እናፍቱ እግሬ አውጭኝ አልን። ታዲያ በዚህ ፍጥነት በሽምጥ እየሸሸን ሳለ አንድ ብላቴና እየሮጠ ደርሶብን አንድ አስደንጋጭ ዜና ይነግረናል፣ ወንድም እትቻን ገደሉት ይለናል፤ በእርግጥ እኚህ ወንድም በሞት አፋፍ ላይ ናቸው እንጂ አልሞቱም ነበር። ወንድም ድሪርሳ ይህን አሳዛኝ ወሬ ሲሰማ ወደ ኋላ ሊመለስ ሲል ቄሱ እኛን ጥለህ አትሄድም ብሎት እጁን ይዞ ያስቀረዋል፣ ትንሽ ቆይቶ ከእኛ ጋር መሆኑ ያልተመቸው አንድ ወንድም ከእኛ ሊለይ ሲል ወንድም ድሪርሳ በተራው ጥለኸን አትሄድም የሚገድሉንም ከሆነ አብረን እንሞታለን እንጂ ብሎት እንዳይሄድ እጁን ይዞት ያስቀረዋል።

አሁንም እየሸሸን ሳለ ሌላ ልብ የሚሰብር አሳዛኝ ነገር ይከሰታል። አሳዳጆቻችን እየቀረቡን መሆኑን የተመለከተው ወንድም ደሜ ሳልጠመቅ ልሞት ስለሆነ እባክህን ከፊታችን ባለ ወንዝ አጥምቀኝ እያለ ቄሱን ሲማጸን ቄሱ በዚያ ሁኔታ ውስጥ ራሱን ከስጋ ሞት ከማዳንና የባልንጀራውን ነፍስ ከማዳን የቱን መምረጥ እንዳለበት ለመወሰን ይቸገራል። ያልተጠበቀ አስጨናቂ ነገር ገጠመው፤ ይሁን እንጂ አንዱን መምረጥ ግድ ነውና ራሱን ማዳኑን መረጠ፣ ህሊናው እየወቀሰው ሸሽታችንን ቀጠልን። በመንገዳችን ላይ ያጋጠሙንን ሁለት ወንዞች ወንድም ድሪርሳ ቄሱን ተሸክሞ አሻገረው። እንደዚያም ሆኖ ቄሱ በወቅቱ የከተማ ሰው በመሆኑና ለመሮጥ የማይመች ሙሉ ኮትና ሱሪ ለብሶ ስለነበረ መሮጥ ስላልቻለ ነፍሱ ከሥጋው ልትለይ ምንም አልቀራትም። ሰዎቹ እህል ውሃ የማያሰኝ ዱላ፣ ገጀራና መጥረቢያ ይዘው እየቀረቡን ሲመጡ በቁማችን የሞትን ያህል ተሰማን፣ ግን በድናችን ይሮጣል።

በዚህ ሁኔታ በእግር ከአንድ ሰዓት በላይ ይፈጅ የነበረውን መንገድ ከ20 ደቂቃ ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አጠናቀን ሰዎቹ ሳይደርሱብን እናፍቱ የምትባል አንዲት መንደር ደረስን። እንደደረስን አቶ ገመቹ በንቲ በተባሉ የእናፍቱ መንደር ታዋቂ ሰው ቤት በጓሮ በኩል ገባን። ድንገት ስንገባም ሰውዬው ማዕድ ቀርቦለት በእንቁላል በቀበጠ የዶሮ ወጥ ምግብ እየተመገበ ነበር፤ እርሱም ብቻውን መብላት እንደማይሆለት ኢትዮጵያዊ ያጎርሰን ጀመር። እንደገባንም ቄሱ በሃይማኖት ምክንያት ነው ሊገድሉን የሚያሳድዱን ምንም አላጠፉንም የሰራነውም ወንጀል የለም በማለት ትንፋሹ እየተቆራረጠ ለሰውዬው አስረግጦ ያስረዳል፤ ሰውዬውም ወዲያውኑ ሽጉጡን መዝዞ ካፖርቱን ደርቦ ጎረቤቱን አስተባብሮ ቤቱን እንደ ንብ ወደከበቡት ሰዎች ይወጣል።

ከዚያም ሰዎቹ ነፍሰ ገዳዮች ናቸው ባለውቃቢውን ገድለው ነው ሸሽተው የመጡት አሳልፋችሁ ስጡን በማለት በውሸት ይወነጅሉናል። አቶ ገመቹ ግን ሰዎቹን አረጋግተው ሁሉም በህግና ስርዓት ባለው መንገድ እንደሚታይ ካግባቡ በኋላ ቀስ ብለው ለእኛ ደህንነት ሲሉ እናፍቱ እስር ቤት አስገቡንና ራሳቸው ጠበቁን። እኛ በህግ ጥላ ስር ውለን እስር ቤት ገብተን የዲያብሎስን ሥራ እየተቃወምን ሲሆን ሰዎቹ ግን ዙሪያችን ከበው እየጨፈሩ ይገኛሉ።

በመጨረሻም እዚያው እስር ቤት እያለን በተለይ ቄሱን ለማስገደል አንድ በአካባቢው የታወቀ ዱለኛ (የበቾ ጎሊያድ ሊባል የሚችል ቁመና ያለው) ገዝተው አመጡ። እስራኤሎች ጎልያድን ሲያዩት ልባቸው እንደፈሰሰ እኛም ዱለኛውን ስናየው የሞትን ያህል ተሰማን። እርሱም ወደ እስር ቤቱ ገብቶ ቄሱን ሲያየው ቀጠን ያለና መልከ መልካም ሆኖ ሲመለከተው አሳዝኖት ይህች ምኗ ትመታለች ብሎ ሳይመታው ጥሎት ይሄዳል። በዚህ አኳኋን አምላካችን ልቡን ቀይሮት ሁላችንንም ከሃይለኛ እጅ አዳነን።

ከዚያም እኛ እናፍቱ እስር ቤት የነበርነውን በጥበቃ አሳጅበው ወደ አዲስ ዓለም ሲልኩን አረብሳ እስር ቤት የነበሩትም እንደእኛው ታጅበው መጡና በአዲስ ዓለም ማዘጋጃ ቤት ቅጥር ግቢ ተገናኘን። ከጎፋ ዋናዋ ቤተክርስቲያን የተላኩት ወንድም አማረም አዲስ ዓለም መጥተው አገኙን። ቤተሰብ ጠያቂዎችም እዚያው ድረስ መጡ። ከእነዚህ ውስጥ የቄሱ ቤተሰቦችና የወንድም ድሪርሳ እጮኛ እህት አለሚቱም ይገኙባቸዋል።

ከዚያም መረጃና ማስረጃ ተደራጅቶ ከአሳዳጆቹ ቀንደኞቹ ተመርጠው ክስ ተመስርቶባቸው ተፈርዶባቸዋል፤ በእርቅም ተይዞ ላደረሱት የአካልና የንብረት ጉዳት ተገቢውን ካሳ እንዲከፍሉ ተደርጓል። ከዚያም በላይ ክፉዎች በከፍተኛ መቅሰፍት ተቀስፈዋል፤ አንዳንዶቹ የሚወርሳቸው እንኳ እስከሚጠፋ ተደርገዋል። በሰዎቹ ላይ የደረሰውን መቅሰፍት በማየት በአካባቢው ላይ ፍርሀት ሆነ። በዚህ የተነሳ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ይህን ታሪክ የሚያውቁ በኦዶና አካባቢዋ የሚገኙ የቀድሞ ነዋሪዎች ስለ ሐዋርያት እምነት ተከታዮች መናገር ይፈራሉ።

በዚህ ዓይነት ከፍተኛ ስደት ውስጥ ያለፈችው የኦዶ ቤተክርስቲያን ዛሬ ብዙ ፍሬ አፍርታለች። ከስደቱ በኋላ ስፋቱ ዘጠኝ በአስራ አምስት ሜትር በሆነ ቦታ ላይ 150 ቆርቆሮ የለበሰ ጸሎት ቤት ተሰርቶ እግዚአብሔር እየከበረበት ይገኛል። ብዙ አገልጋዮችም ከዚህ ቤተክርስቲያን ወጥተዋል።

በዚህ ሁሉ ውስጥ ተሸክሞ ከክፉም ጠብቆ ያሳለፈን ቤተክርስቲያኑንም የሚሰራ የሰማይ አምላክ ጌታ ኢየሱስ ይባረክ! አሜን። ■

# መጋቢነት

ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ቅዱሳን በጻፈው ሁለት መልዕክቶች ውስጥ ከእነርሱ ጋር በመጋቢነት በቆየባቸው ጊዜያት ያሳያቸውንና የሆነላቸውን ነገሮች ጠቅሷል፥፥ የመጋቢን ሥራ በመልዕክቶቹ ውስጥ እንደሚከተለው እናገኛለን፥፥

- መጸለይ (1 ተሰ. 2፥3፤ 3፥9-13)
- ወንጌልን መናገር (1 ተሰ. 1፥4-5፣9-10)
- ማሰልጠን (1 ተሰ. 1፥8)
- መውደድ (ማፍቀር) (1 ተሰ. 2፥7-8)
- ምሳሌ መሆን (1 ተሰ. 2፥10)
- መምራት (1 ተሰ. 2፥1-12)
- መመገብ (1 ተሰ. 2፥13 )
- መጠበቅ (1 ተሰ. 3፥1-8)
- ማስጠንቀቅ (1 ተሰ. 4፥1-8)
- ማስተማር (1 ተሰ. 4፥9-5፥11)
- መምከር (1 ተሰ. 5፥12-24)
- ማጽናናት (1 ተሰ. 1፥3-12 )
- ስህተትን ማረም (2 ተሰ. 2፥1-12 )
- ያለ ሥርዓት ከሚሄዱ ምዕመናንን መለየት (ማውገዝ)(2 ተሰ. 3፥4-6፣ 14) ■

ምንጭ፥- Christian Leadership and Pastoral Ministry

# ቅድስና

# ትሕትና እና ትዕቢት

✍ ቄስ ኤልያስ ሸባባው | የአስኮ ጽዮን አጥቢያ መጋቢ

የወንጌል አገልጋይ ከሚፈተንባቸው ነገሮች መካከል አንዱ “ትዕቢት” ነው። ለዚህም ነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ *“ከእኔም ተማሩ፣ እኔ የዋህ፣ በልቤም ትሁት ነኝና”* ያለው (ማቴ. 11፥29)። ይህንን በማሰብ ለዛሬ በዚህ ርዕስ ጥቂት ነገር ለማለት ወደድሁ። እነሆ በቅንነት አንብቧት!

እግዚአብሔር ከሰው ከሚፈልጋቸው 3 ነገሮች መካከል አንዱ ሆኖ በሚክያስ መጽሐፍ የተጠቀሰው በትሕትና መሄድ ነው። *“... ሰው ሆይ፥ መልካሙን ነግሮሃል፤ እግዚአብሔርም ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው? ... ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ አይደለምን?”* (ሚክያስ 6፥8)። ይህ ማለት የትህትና ጉዞ በዘዳግም 10፥12-13 እንደተጻፈው እርሱን መፍራት፣ በመንገዱ መሄድ፣ በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ እና በፍጹም ኃይልህ እግዚአብሔርን እንድትወደው ትዕዛዙን ምስክሩን እንድትጠብቅ የሚለውን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው ማለት ነው። አንድ ሰው ትሕትናውን አጣ ሲባል የሚያጣው የተጠቀሱትን እነዚህን ነገሮች ሁሉ ነው።

ከእግዚአብሔር ጋር በትሕትና መሄድ ቀጣይነት ያለው ጉዞ ነው እንጂ የአንድ ሰሞን ልምምድ አይደለም። የመሰጠት ሕይወት ነው፤ እርሱን በማይጠፋ ክብር መከተልና ዓላማውን መፈጸምን ያካትታል። ስለዚህም ትሕትና በዕለት ተዕለት ኑሮ የሚታይ ሕይወት ነው። ውጤቱም በሌሎች ሰዎች ላይ በሚያመጣው የጽድቅ ተጽዕኖ ጭምር ይለካል።

ሰው የትሕትና ጉዞው ወደ ላይ (vertical) ማለትም ከእግዚአብሔር ጋር ልክ ሲሆን የጎንዮሽ (Horizontal) ግንኙነቱም ጭምር ልክ ይሆናል። ከእግዚአብሔር ጋር የተጣላ ነው ዙሪያውን የሚያምስ። *“አሁንም ከእርሱ ጋር ተስማማ፥ ሰላምም ይኑርህ፤ በዚያም በጎነት ታገኛለህ”* (ኢዮብ 22 ፥21) ተብሎ እንደተጻፈው ነው።

እግዚአብሔርን የማይፈራ ተብሎ ሰውን የሚያከብርና የሚወድ ሊባል አይችልም። *“በአንዲት ከተማ እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰውንም የማያፍር አንድ ዳኛ ነበረ”* ተብሎ በሉቃስ 18፥2 እንደተጻፈው ሰውን የሚጎዳ እግዚአብሔርን የናቀ ነው፤ ምክንያቱም *“የቀድሞውን የድንበር ምልክት አታፍልስ፤ ወደ ድሀ አደጎች እርሻ አትግባ፤ ታዳጊአቸው ጽኑ ነውና፥ እርሱም ፍርዳቸውን ከአንተ ጋር ይፋረዳልና”* ተብሎ በምሳሌ 23፥10-11 ተጽፎአልና።

አጥራችን የሚነቀንቀው እርሱን በናቀ ሰው ነው፤ ሊበድለን የሚነሳ ከእርሱ ፊት የወደቀ ነው፣ የሚያስፈሩ እና የሚያንቀጠቅጡ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔርን የማይፈሩ ናቸው፤ ባይሆንማ ኖሮ የሚያስፈራ እና የሚያንቀጠቅጥ እርሱ ብቻ እንዲሆን ይፈቅዱ ነበር። *“የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርን ቀድሱት፤ የሚያስፈራችሁና የሚያስደነግጣችሁም እርሱ ይሁን”* ይላልና (ኢሳ 8፥13)። ይህን መፈጸም ያቃተው ባገኘው አጋጣሚ በሙሉ ቢያሸብር ቢያስፈራራ ችግሩ እርሱ ለእግዚአብሔር በፍርሃት እና በመንቀጥቀጥ ባለመገዛቱ ብቻ ነው። በእውነት በጌታ ፊት የሚፈራና የሚንቀጠቀጥ ትሁት ሰው ሌሎችን ለማሸበር ጊዜ የለውም የምንልበት ምክንያት  እግዚአብሔርን የጣለ ሁሉን ሊጥል ይነሳልና ነው። ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሱን ያዋረደ ግን ሌሎችን ለማገልገል በጸጋ ይነሳል። ስለዚህም የሰው የጎንዮሽ የትሕትና መንገዱ የላይኛው ነጸብራቅ እንጂ ሌላ አይደለም። ትዕቢተኞች አስቀድመው እግዚአብሔርን የናቁ ናቸው፤ ስለዚህም በሕዝቡ (በልጆቹ ) ላይ ይነሳሉ።

እግዚአብሔር በከበሩ ማዕድናት ሸላልሞ የፈጠረው መልዐክ በውበቱ እና በክብሩ ኮርቶ ሲረክስ (ሕዝ. 28፥13) ራቁቱን በትህትና እንዲመላለስ የተፈጠረው ግን ሃፍረቱ የተሸፈነ ሰው ታየ፤ ይህም በትህትና ከእግዚአብሔር ጋር በመኖር ምክንያት በእግዚአብሔር ክብር እና ጸጋ መሸፈን እንደሚበልጥ አመልካች ነው። ፍጹም ሆኖ አንዳች እንደማያስፈልገው በተቀበለው ነገር የሚመካና ለእግዚአብሔር ክብር በተሰጠው ነገር የሚነግድ፣ ጥበቡን እና መቅደሱን የሚያረክስ ለራሱ ታላቅ ነገርን ሲፈልግ ከሰማዩ ስፍራ የሚጎድል ነው። የሁል ጊዜ የትሕትና መንገዱን የዘነጋና ስለራሱ ከፍታ ሲታገል የእግዚአብሔርን ያጎደለ ወይም የሸፈነ እርሱ ትዕቢተኛ ሊባል ይችላል። ስለዚህም በራስ ውበት መመካት፣ መደነቅ፣ በጥበብ መርከስ በተመደበበት ስራ ግፍን መሞላት እና በከበሩ ማዕድናት መከበብ ወይም የቁሳቁስ ባለቤት የመሆን ትምክህት ነው። እንዲሁም ፍጹም ሆኖ የመፈጠር ወይም የሙላት፣ ያለመጉደል እና የልሕቀት ማለትም ትልቅ የክዋኔ (ችሎታ) ባለቤትነት የመታበይ ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ ከወደቀው መልዐክ ልንማር እንችላለን።

ስለዚህም ከላይ ከተጠቀሱት ልምምዶች ተነስተን ስናይ ትዕቢት ስለ ራስ የተሳሳተ አመለካከት ነው፤ ዋስትና ወደ ሌለው በራስ ወደ መተማመን ይመራል፤ ከዚህም የተነሳ ከሌሎች ጋር በመተባበር የቆመን አንድ ሰው ሌሎች የማያስፈልጉት እስኪመስለው ድረስ ሙሉነት እና ብቃት እንዲሰማው ያደርገዋል። በኢሳያስ 14፥12-15 እንደተጻፈው እኔ፣ እኔ፣ የእኔ በእኔ ለእኔ

የሚያበዛ አስተሳሰብ ይጠናወተዋል። የወደቀው መልዐክ 5 ጊዜ "እኔ" ባለበት 5 ጊዜ በተቃራኒው "እንዲህ ትሆናለህ" ተብሎ ፍርድ ተነግሮበታል።

ትዕቢትን የቃሉ ምንጭ ትርጉም ጥናት እንደሚያመለክተው፣ ትዕቢት የከፍታ ሃሳብ፣ መተለቅ፣ የመላቅ እና የታላቅነት ስሜት ነው። በአንጻሩ የትዕቢት ተቃራኒ የሆነ ትህትና የቃሉ ምንጭ ትርጉም መንበርከክ፣ ራስን ማስመጥ፣ መውረድ፣ ማስቀመጥ እና ማስገዛት ነው። ሌሎች ትዕቢትን እንደመነፋት መኮፈስ አድርገው ይተረጉሙታል። ይህ ግን የሚታየው ውጫዊ ገጽታው ብቻ ነው። የማይታየው እና የተሰወረው ትዕቢት በጉራ (boasting) ራስን በመሸጥ ብቻ አይወከልም። የትዕቢት ኃጢአት እንደ አልኮል እና አደንዛዥ ዕጽ ስለ ራስ ያለን አመለካከት ያበላሸ እና ከእውነታ ውጪ የሆነ እይታ እንዲከሰት ያደርጋል። ለተሳሳተው አመለካከት እና አስተሳሰብ ሌሎቹን ማስደነቅ (ማስገረም) የሚፈልግ አልፎም ይህ በራስ የመተማመን እና ራስን የማግዘፍ ልምምድ አማካሪ እና ደጋፊ እስከማያስፈልግ ድረስ በራስ በበቃ ማንነት በመኩራራት ሉዓላዊ ወሳኝነትን ይጎናጸፋል።

የቃሉን ትርጉም አለማወቅ ስለ ነገሩ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲኖረን ያደርጋል። ብዙዎች ይህን ቃል በራሳቸው ትርጉም ሲረዱት እና ለሰዎችም የተለያየ እንቅስቃሴ የተሳሳተ ግምት እንዲይዙ ምክንያት ሲሆኑ ይታያል። በዚህም የተሳሳተ ምክንያት ለስኬት ሳይሆን ዋጋ ያለው ሰው ሆነው ዘመናቸውን መሰዋት እና የክብርን አክሊል ሽልማት በሰማይ መሸለም የሚፈልጉ ወይ በሕይወታቸው ያለውን የእግዚአብሔርን ዓላማ ትተውት ይቀመጣሉ፤ ወይም በማድረጋቸው ይፈተናሉ ይጎዳሉም።

ከላይ ለተነሳው ሃሳብ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንመልከት "... ታላቅ ወንድሙም ኤልያብ ከሰዎች ጋር ሲነጋገር ሰማ፤ የኤልያብም ቍጣ በዳዊት ላይ ነድዶ፡- ለምን ወደዚህ ወረድህ? እነዚያንስ ጥቂቶች በጎች በምድረ በዳ ለማን ተውሃቸው? እኔ ኵራትህንና (I know thy pride) የልብህን ክፋት አውቃለሁና ሰልፉን ለማየት መጥተሃል አለው።" ይህ ማንም ታላቅ ወንድም ሊናገረው የሚችል አሳብ ነው። ነገር ግን ይህ በኤልያብ ፊት እጅግ ትዕቢተኛ እና ክፉ ልብ እንዳለው የሚቆጠረው ዳዊት "የትዕቢት እግር አይምጣብኝ፥ የኃጢአተኞችም እጅ አያውከኝ" (መዝ 36፥11) ብሎ መጸለይ የዘወትር ኑሮው የነበረ ሰው ነው። ዳዊት ቅን ሰው ነበር፤ እግዚአብሔር "... ሲመሰክርለትም፡- እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ አለ" (ሐዋ 13፥22)።

ዳዊት ሁሉን በማስተዋል የሚያደርግ ታዛዥ፣ በአባቱ ተልኮ የወንድሞቹን ደህንነት ለማወቅ ወደ ሰልፉ የመጣ ነበር፣ በዚህ አጋጣሚ ለሰማው ነገር ምላሽ ሰጠ ተንቀሳቀሰም፣ መረዳቱን ተናገረ ነገር ግን በተሳሳተ ትርጉም ትዕቢትን እና የልብን ክፋትን የተረዳው ሰው ሰልፉን ለማየት ነው የመጣኸው በሚል ዳዊትን ትዕቢተኛ ነህ አለው።

ኤልያብ በቤተሰቡ አሰላለፍ ብቻ ለክቶ ተናገረ። አዎን በእሴይ ልጆች አሰላለፍ ታላላቆቹ ወደ ጦር ሜዳ ታናናሾቹ ወደ መንጋው መሄድ ልክ ነው፤ የእግዚአብሔር ዓላማ አሰላለፍ ደግሞ "አትታበዩ፥ በኵራትም አትናገሩ፤ እግዚአብሔር አዋቂ ነውና፥ እግዚአብሔርም ሥራውን የሚመዝን ነውና፥ ከአፋችሁ የኵራት ነገር አይውጣ። የኃያላንን ቀስት ሰብሮአል፥ ደካሞችም በኃይል ታጥቀዋል" (1ሳሙ 2፥4) ተብሎ እንደተጻፈው የአህዛብን ተግዳሮት ለመስበር ታናሹን የሚያስታጥቅ ነው። የእግዚአብሔርን

ትሄዱበት ዘንድ የሚገባውንም መንገድ እንዲያሳያችሁ ሌሊት በእሳት፥ ቀን በደመና በፊታችሁ በመንገድ ሲሄድ የነበረውን አምላካችሁን እግዚአብሔርን በዚህ ነገር አላመናችሁም።" ይህን መለኮታዊ መልዕክት እና በእግዚአብሔር ሰው የተመሰከረላቸውን መልዕክተኞች እምነት ቃል ማመን አቃታቸው፤ ሁል ጊዜ በተቃራኒው የሚንቀሳቀሱ ትሁታን ለመሆን የሚጥሩ ነበሩ። ታሸንፋላችሁ ሲባሉም ያለቅሳሉ፤ እግዚአብሔር በቃላችሁ ተቆጣ በቃ ተመለሱ ሲባሉም ምላሻቸው ይህ ነበር "...እናንተም እግዚአብሔርን በድለናል አምላካችን እግዚአብሔር እንዳዘዘን ሁሉ እንወጣለን፥ እንዋጋማለን ብላችሁ መለሳችሁልኝ። ከእናንተም ሰው ሁሉ የጦር መሣሪያውን ያዘ፥ ወደ ተራራማውም አገር መውጣትን አቀለላችሁት። እግዚአብሔርም፡- እኔ በእናንተ መካከል አይደለሁምና በጠላቶቻችሁ ፊት እንዳትወድቁ አትውጡ፥ አትዋጉም በላቸው

**ዳዊት የትዕቢት እግር አይምጣብኝ፥ የኃጢአተኞችም እጅ አያውከኝ (መዝ 36፥11) ብሎ መጸለይ የዘወትር ኑሮው የነበረ ሰው ነው።**

አሰራር ለማያውቅ ትዕቢት ቢመስልም ዋጋ ያላቸው የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን ራሳቸውን የሰጡ ሁሉ የሚረዱት ትልቅ ነገር "...ከሕዝቡ መኳንንት ጋር ያስቀምጣቸው ዘንድ፥ የክብርንም ዙፋን ያወርሳቸው ዘንድ፥ ችግረኛውን ከመሬት ያስነሣል፥ ምስኪኑንም ከጉድፍ ያስነሣል" (1ሳሙ 2፥8) ተብሎ የተጻፈው ቃል የሚፈጸም መሆኑን ነው።

በሌላ ስፍራ ደግሞ ትሕትና የሚመስል ነገር ግን ያልሆነውን ዓመጽ እንመልከት። "...በፊታችሁ የሚሄደው አምላካችሁ እግዚአብሔር፥ እናንተ ስታዩ በግብፅና በምድረ በዳ እንዳደረገላችሁ ሁሉ፥ ስለ እናንተ ይዋጋል ወደዚህም ስፍራ እስክትመጡ ድረስ በሄዳችሁበት መንገድ ሁሉ፥ ሰው ልጁን እንዲሸከም አምላክህ እግዚአብሔር እንደተሸከመህ አንተ አይተሃል። ዳሩ ግን ለሰፈራችሁ የሚገባውን ስፍራ እንዲፈልግላችሁ፥

አለኝ። እኔም ተናገርኋችሁ እናንተ ግን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ ዓመፃችሁ እንጂ አልሰማችሁም በትዕቢታችሁም ወደ ተራራማው አገር ወጣችሁ። በዚያም በተራራማው አገር ይኖሩ የነበር አሞራውያን ወጥተው ተጋጠሙአችሁ፥ ንብ እንደምታሳድድም አሳደዱአችሁ፥ እስከ ሔርማም ድረስ በሴይር መቱአችሁ። ተመልሳችሁም በእግዚአብሔር ፊት አለቀሳችሁ እግዚአብሔር ግን ድምፃችሁን አልሰማም፥ ወደ እናንተም አላዳመጠም (ዘዳግም 1፥30-33፣ 43)።

ይህ ዓይነቱ ደግሞ የሚታዘዝ የሚመስል፣ ንስሃ የሚመስል፣ ቅንዓት የሚመስል እንባ እና ለቅሶ የተቀላቀለበት ትዕቢት ነበር። ስለዚህም ነው የትዕቢትንም ሆነ የትሕትናን ትርጉም በትክክለኛው መንገድ ማወቅ አስፈላጊ የሚሆነው። ልክ እንደ አካዝ "... እግዚአብሔርም ደግሞ አካዝን

*እንዲህ ብሎ ተናገረው፦ከጥልቁ ወይም ከከፍታው ቢሆን ከአምላክህ ከእግዚአብሔር ምልክትን ለምን። አካዝም፦ አልለምንም፥ እግዚአብሔርንም አልፈታተንም አለ።"* ኢሳ 7፥10-12 ትሕትና ይመስላል፤ ነገርግን ትዕቢት ነበር። ይህ ሰው በዚህ አፉ ነበር የአሶርን ንጉስ እርዳኝ ብሎ የለመነው፤ ራሱንም ያዋረደው። ስለዚህም በለዘቡ ቃላት የተሰወረ የማይታየው ትዕቢት ግብዝነት ሆኖ ብዙዎችን እንዳይጨርስ ሊታወቅ ይገባል። ከዚህ ቀጥሎ የተወሰኑ የትዕቢት ገጽታዎችን እንመለከታለን።

## 1. የችሎታ እና የክዋኔ ትዕቢት

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ መናገር እና ተደማጭ ስለመሆን ትዕቢት ማስጠንቀቂያ በሰጠበት መልዕክቱ *"እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥ ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ በቃልና በጥበብ ብልጫ ለእግዚአብሔር ምስክርነቴን ለእናንተ እየነገርሁ አልመጣሁም። በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደተሰቀለ ሌላ ነገር እንዳላውቅ ቆርጬ ነበርና። እኔም በድካምና በፍርሃት በብዙ መንቀጥቀጥም በእናንተ ዘንድ ነበርሁ"* (1ቆሮ 2፥1-3) ነበር ያለው ። ሐዋርያው በመናገር ዋና የነበረ ሰው፣ የግሪክ ሰዎች ተመስጠው የሚያደምጡት ነበር። ስለዚህም ሄርሜን የሚል ቅጽል ስም አወጡለት። ሐዋርያው የተናጋሪነት ትዕቢት እንዳይመጣበት ማርከሻውን ያውቅ ነበርና በመካከላቸው እየፈራ እና እየተንቀጠቀጠ ኖረ። ሐዋርያው ጳውሎስ እና በርናባስ ከፈውስ ክዋኔ ቀጥሎ የአበባ ጉንጉን መስዋዕት እና አማልክት ናችሁ እንጂ ሰዎች አይደላችሁም በሚል አምልኮ ቀረበላቸው። *"ሐዋርያት በርናባስና ጳውሎስ ግን ይህን በሰሙ ጊዜ ልብሳቸውን ቀደው ወደ ሕዝቡ መካከል እየጮኹ ሮጡ፥ ይህንም ...ብለው እንዳይሠዉላቸው ሕዝቡን በጭንቅ አስተዉአቸው"* (ሐዋ 14፥14፣ 18)።

በሌላ ስፍራ በሐዋርያው ጴጥሮስ እና ዮሐንስ አገልግሎት ድንቅ ሲሰራ፤ *"እርሱም ጴጥሮስንና ዮሐንስን ይዞ ሳለ፥ ሕዝቡ ሁሉ እየተደነቁ የሰሎሞን ደጅ መመላለሻ በሚባለው አብረው ወደ እነርሱ ሮጡ። ጴጥሮስም አይቶ ለሕዝቡ እንዲህ ሲል መለሰ፦ የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ በዚህ ስለ ምን ትደነቃላችሁ? ወይስ በገዛ ኃይላችን ወይስ እግዚአብሔርን በመፍራታችን ይህ ይመላለስ ዘንድ እንዳደረግነው ስለ ምን ትኵር ብላችሁ ታዩናላችሁ?"* ሐዋርያው ጴጥሮስም ብንመረመር እስኪል እና ለፍተሻ ራሱን እስኪያዘጋጅ ድረስ ሲያስጮኸው የነበረው ይህ ዓይነቱን ትዕቢት መጸየፍ ነው።

ስለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው *"ወንድሞች ሆይ፥ ስለ አንዱ በአንዱ ላይ አንዳችሁም እንዳይታበዩ፦ ከተጻፈው አትለፍ የሚለውን በእኛ ትማሩ ዘንድ፥ ይህን በእናንተ ምክንያት ስለ ራሴና ስለ አጵሎስ እንደ ምሳሌ ተናገርሁ። አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጎሃል? ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? የተቀበልህ ከሆንህ ግን እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድር ነው?"* በማለት ይናገራል። በዳዊትም ሕይወት የሆነው ተመሳሳይ ነበር። እልፍ ገደለ የሚለው የክዋኔ ትዕቢት የሚያመጣ ዘፈን ነበር፤ ብላቴናው ሴቶች በዘፈኑት መከራውን አየ። አንዳንዶች በብዙ ጸሎት የተገኘን ድል ሲያደንቁ የሌሎችን ስራ በማንኳሰስ ስለሆነ በዙሪያ ያሉትን ያስቆጣሉ፤ የእግዚአብሔር ስራ የተከናወነበትን መሳሪያ ያጎሰቁሉና ያስጨንቃሉ።

## 2. የስፍራ  ትዕቢት

እግዚአብሔር በመረጠው በሙሴ ላይ የተነሱት  ሰዎች ማን ነበሩ? ቢባል *"ከጉባኤው የተመረጡ ዝናቸውም የተሰማ የማኅበሩ አለቆች ነበሩ"* (ዘኁልቁ 16፥2)።  ይህ የስፍራ ትዕቢት ነበር እነዚህን አለቆች የጣላቸው። *"ሙሴም ቆሬን አለው፦ እናንተ የሌዊ ልጆች፥ ስሙ፤ የእስራኤል አምላክ ከእስራኤል ማኅበር የለያችሁ፥ የእግዚአብሔርንም ማደሪያ አገልግሎት ትሠሩ ዘንድ፥ እንድታገለግሉአቸውም በማኅበሩ ፊት ትቆሙ ዘንድ ወደ እርሱ ያቀረባችሁ አይበቃችሁምን? አንተን ከአንተም ጋር የሌዊን ልጆች ወንድሞችህን ሁሉ ወደ እርሱ አቅርቦአል፤ ክህነትንም ደግሞ ትፈልጋላችሁን?"* (16፥9) ዋናው ጥያቄያቸው አልበቃንም ነው፤ ድፍረታቸው (ትዕቢታቸው) እስከ ፍርድ ድረስ የሄደ ነበር፤ የመመለስ ነገር አልታየባቸውም።

ፈሪሳዊያን እጅግ ከሚወዱት ነገር አንዱ የከበሬታ ስፍራ እና ማዕረጋቸውን ነው (ማቴ 23፥6)። ስለዚህም በስፍራ የመጣባቸውን አይታገሱም፤ ሃይማኖተኛነታቸው ሁሉ ይጠፋል። በአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን መንጋ  በኃይል የመግዛት መንፈስ  የስፍራ ትዕቢት ነው። የስፍራ ትዕቢት እነዲዮጥራጢስ ይለማመዱት የነበረ ኃጢአት ነው፤ በማንም የማይጠየቁ እና የእረኞችን አለቃ የረሱ ይመስላሉ፤ የክብር አክሊል ሽልማትም ጉዳያቸው አይደለም።

ሌላኛው የስፍራ ትዕቢት ምሳሌ በጌታ የተሾመ ባሪያ ነው *"...ጌታም አለ፦ እንኪያስ ምግባቸውን በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው በቤተ ሰዎቹ ላይ የሚሾመው ታማኝና ልባም መጋቢ ማን ነው? ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው። እውነት እላችኋለሁ፥ ባለው ሁሉ ላይ ይሾመዋል። ያ ባሪያ ግን፦ ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ ሎሌዎችንና ገረዶችንም ይመታ ይበላም ይጠጣም ይሰክርም ዘንድ ቢጀምር፥ የዚያ ባሪያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን ባላወቃትም ሰዓት ይመጣል፥ ከሁለትም ይሰነጥቀዋል እድሉንም ከማይታመኑ ጋር ያደርጋል። የጌታውንም ፈቃድ አውቆ ያልተዘጋጀ እንደ ፈቃዱም ያላደረገ ያ ባሪያ እጅግ ይገረፋል፤ ያላወቀ ግን መገረፍ የሚገባውንም ያደረገ ጥቂት ይገረፋል። ብዙም ከተሰጠው ሰው ሁሉ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል፥ ብዙ አደራም ከተሰጠው ከእርሱ አብዝተው ይሹበታል"* (ሉቃስ 12፥42-48)።

## 3. የብልጽግና ትዕቢት

የዚህ ዓለም ባለጠግነት ትዕቢት በሚያልፈው ነገር የሚያስጥመው ኃጢአት ነው። በስራው  እና በመዝገቡ ብዛት እጅግ የሚመካው ትዕቢተኛ ከራሱ እና ከንብረቱ አሳብ በቀር ሌላ ግድ የማይለው ሕይወትን  በገንዘቡ እንደሚለካ የሚያስብ ሁሉን ወደ ራሱ የሚስብ የሚመስለው  ነው። በታናናሾች ምስኪኖች ጉባዔ ገኖ ለመታየት የሚጥር ወይም አይመጥኑኝም በሚል እኩዮቹን የሚፈልግ እና  ሁሉ

> **በተለይ በብልጽግና ትዕቢት ላለመነካት መፍትሔው ይህ ነው! "...ባለ ጠጋም በውርደቱ ይመካ፤ እንደ ሣር አበባ ያልፋልና" (ያዕቆብ 1፥9-10)**

በእርሱ የሚንቀሳቀስ የሚመስለው ስሙ ካልተጠራ ወይም ካልተደመጠ በጉባዔው የማይባረክ በስጦታው ወይም በአስራቱ የሚያስፈራራ ሌሎችን የሚገዛ የብልጽግና ትዕቢት ሰለባ ነው።

ስለዚህም እግዚአብሔር በጥረታቸው እና በትጋታቸው ያበለጸጋቸው ቅዱሳን ከዘላለም ሕይወት እንዳይቀሩ እንዲህ ተመክረዋል *“... በአሁኑ ዘመን ባለ ጠጎች የሆኑት የትዕቢትን ነገር እንዳያስቡ፥ ደስም እንዲለን ሁሉን አትርፎ በሚሰጠን በሕያው እግዚአብሔር እንጂ በሚያልፍ ባለ ጠግነት ተስፋ እንዳያደርጉ እዘዛቸው። እውነተኛውን ሕይወት ይይዙ ዘንድ፥ ለሚመጣው ዘመን ለራሳቸው መልካም መሠረት የሚሆንላቸውን መዝገብ እየሰበሰቡ፥ መልካምን እንዲያደርጉ በበጎም ሥራ ባለ ጠጎች እንዲሆኑ፥ ሊረዱና ሊያካፍሉም የተዘጋጁ እንዲሆኑ ምከራቸው።”* ተብሎ እንደተጻፈ የትዕቢትን ነገር እንዳያስቡ ሊመከሩ ይገባል። በተለይ በብልጽግና ትዕቢት ላለመነካት መፍትሔው ይህ ነው *“...ባለ ጠጋም በውርደቱ ይመካ፤ እንደ ሣር አበባ ያልፋልና”* (ያዕቆብ 1፥9-10 ፣ 1ኛ ጢሞ. 6፥17-19)።

## 4. የዕውቀት ትዕቢት

ይኼኛው ደግሞ የመጀመሪያዎቹን የሰው ልጆች የጣለ ኃጢአት ነው። *“እውቀት ያስታብያል ፍቅር ግን ያንጻል። ማንም አንዳች የሚያውቅ ቢመስለው ሊያውቅ እንደሚገባው ገና አላወቀም”* (1ቆሮ 8፥1)። *“ማንም ራሱን አያታልል፤ ከእናንተ ማንም በዚች ዓለም ጥበበኛ የሆነ ቢመስለው ጥበበኛ ይሆን ዘንድ ሞኝ ይሁን። የዚህች ዓለም ጥበብ በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት ነውና። እርሱ ጥበበኞችን በተንኰላቸው የሚይዝ፤ ደግሞም፦ ጌታ የጥበበኞችን አሳብ ከንቱ እንደ ሆነ ያውቃል ተብሎ ተጽፎአልና”* (1ቆሮ 3፥18)።

ይህ አሳች የሆነው የትዕቢት ዓይነት በዕውቀት የገባ ዓመጽ ለሰው ውድቀት መነሻ እንደሆነ ሁሉ በመጨረሻም ዘመን ሰውን የሚጥለው ይሄው ነው። *“...በክፋትሽ ታምነሻል፤ የሚያየኝ የለም ብለሻል፤ ጥበብሽና እውቀትሽ አታልለውሻል፥ በልብሽም፦ እኔ ነኝ ከእኔም በቀር ሌላ የለም ብለሻል”* (ኢሳ 47፥10)። ስለዚህም ነው በብሉይም ኪዳን በአዲስም ኪዳን ተመሳሳይ መልዕክት የተነገረን። *“እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ጠቢብ በጥበቡ አይመካ፥ ኃያልም በኃይሉ አይመካ፥ ባለ ጠጋም በብልጥግናው አይመካ፤ ነገር ግን የሚመካው፦ ምሕረትንና ፍርድን ጽድቅንም በምድር ላይ የማደርግ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን በማወቁና በማስተዋሉ በዚህ ይመካ፤ ደስ የሚያሰኙኝ እነዚህ ናቸውና፥ ይላል እግዚአብሔር”* (ኤር 9፥23-24)።

## 5. የስኬት እና አሸናፊነት ትዕቢት

የሙሉነት ወይም ባለመጉደል ከፍታ ላይ መድረስ የተሳካለት በሚባል ደረጃ በብዙዎች ቤተዘመድ እና በወዳጆች መከበብ ሲኖር የሚፈጥረው ስሜት ነው። በዚህ ትዕቢት የሚጠቁ በማህበራዊ ደረጃቸው ከፍ ያሉ የትላልቆች ወገን እንደሆኑ በሚያስቡ፣ የቤተሰባቸው ትልቅነት የሚያኮፍሳቸው ናቸው። በዚህም ምክንያት በአስተሳሰብ፣በንግግራቸው ውስጥ ትምክህት ይታያል። ሁሉን በሰው የሚፈቱ ወይም መፍትሔ የሚያገኙ፣ በሌሎች ምክንያት የሚከበሩ እና የሚሞገሱ ናቸው። በትሕትና እና በልመና ልምምድ ውስጥ እንዳያልፉ ስማቸው ያገዳቸው፣ ሳይጠይቁ የሚሰጣቸው ሁሉ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ልምምድ ትዕቢት እንዳያመጣ እግዚአብሔር በሰጣቸው ነገሮች እያመሰገኑ ብዙ የሚያገለግሉ ብዙ የሚጥሩ በተቀበሉት ከፍታ በተሰጣቸው ነገር ብዙ የሚፈለግባቸው እንደሆኑ እያሰቡ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ *“እኔ ግን በሥጋ ደግሞ የምታመንበት አለኝ። ሌላ ሰው ማንም ቢሆን በሥጋ የሚታመንበት እንዳለው ቢመስለው፥ እኔ እበልጠዋለሁ። በስምንተኛው ቀን የተገረዝሁ፥ ከእስራኤል ትውልድ፥ ከብንያም ወገን፥ ከዕብራውያን ዕብራዊ ነኝ፤ ስለ ሕግ ብትጠይቁ፥ ፈሪሳዊ ነበርሁ፤ ስለ ቅንዓት ብትጠይቁ፥ ቤተ ክርስቲያንን አሳዳጅ ነበርሁ፤ በሕግ ስለሚገኝ ጽድቅ ብትጠይቁ፥ ያለ ነቀፋ ነበርሁ። ነገር ግን ለእኔ ረብ የነበረውን ሁሉ ስለ ክርስቶስ እንደ ጉዳት ቈጥሬዋለሁ። አዎን፥ በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቈጥራለሁ፤ ስለ እርሱ ሁሉን ተጐዳሁ፥ ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ፥ በክርስቶስም በማመን ያለው ጽድቅ ማለት በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ጽድቅ እንጂ ከሕግ ለእኔ ያለው ጽድቅ ሳይሆንልኝ፥ በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ እቈጥራለሁ፤ እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፥ በመከራውም እንድካፈል፥ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፥ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ። አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደ ሆንሁ አይደለም፥ ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ”* (ፊልጵ. 3፥4-12) በሚል ትልቅ ትህትና ትምክህቱን እና የአሸናፊነት ስሜቱን እየጣለ ነገር ግን የተከፈተለትን በር እና ተሰሚነት በአግባቡ እየተጠቀመ ትልቅ መንፈሳዊ አገልግሎት እንደሰጠው የእግዚአብሔር ሰው ልንሆን ይገባናል።

ጌታ ኢየሱስ በነገር ሁሉ ማስተዋልን ይስጠን! ■

# የመከሩ ሰራተኛ

ኢየሱስ የመንግስትን ወንጌል እየሰበከ በነበረበት ወቅት ብዙ ሕዝብ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም በማየቱ ለደቀመዛሙርቱ *“መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት”* ብሎአቸዋል (ማቴ. 9፥37-38)።

እግዚአብሔር በየዘመናቱ ለነጣው እርሻ ሰራተኞችን ሲቀጥርና ሲልክ እናያለን፤ መጨረሻው እስኪመጣም ይህንኑ ተግባሩን ይቀጥላል። በዚህ ዘመን ያለንም አገልጋዮች መከሩ እንደነጣ ተመልክተን እንዲልክ ከመለመን በተጨማሪ ራሳችንንና የምናሰማራቸውን ቅዱሳን በዚህ ራዕይ ውስጥ እንዲገቡ ሳንታክት ልናነቃቃ ይገባል። የመከሩ ሰራተኛ፥-

- ለጠፉት ነፍሳት ፍቅር አለው (ማቴ 9፥36)
- ተከታታይ የሆነ የጾምና የጸሎት ጊዜና ልምምድ አለው
- የተዘጋጀ ነው (2 ጢሞ 4፥2)
- ትጉ ሰራተኛ ነው (2 ጢሞ 4፥5)
- ቃሉ ሲሰበክ ሰዎች ወደ መዳን እንደሚመጡ ያምናል (ያዕ 1፥6-7) በወንጌል ኃይል ያምናል (ሮሜ 1፥16)
- ሸክም አለው (ሐዋ 19፥10)
- ሰዎችን ሁሉ ይወዳል (ሉቃስ 4፥18)
- የሰዎች ነገር ግድ ይለዋል (ሉቃስ 15)
- ራዕይ አለው (ሉቃስ 19፥10)
- ትዕግስተኛ ነው (ሉቃስ 21፥19፣ ገላትያ 6፥9)
- የእግዚአብሔርን ቃል ያጠናል (2 ጢሞ 2፥15)
- የውስጥ ተነሳሽነት አለው (1 ሳሙ. 30፥6)
- በድፍረትና በግልጥ ይናገራል (ሐዋ 4፥29-31፣ 2ጢሞ 1፥7፣ ዕብ 13፥5-6)
- ጥበብን የተሞላ ነው (ምሳሌ 11፥30)
- ሰዎች ይድኑ ዘንድ ሰዎችን ይመስላል (1 ቆሮ 9፥22-23) ■

ምንጭ፥- Sowing and Reaping By James G. Poitras

# ቤተሰብ

# አገልግሎትንና ቤተሰብን በሚዛን

✍ ወንድም ወሰነ ኃይሉ | ጎፋ አጥቢያ

አንድ ደስታን እጅግ የተጠማ ሊጋ ወጣት ደስታ የሚገኝበትን መንገድ ሊነግረኝ ይችላል ወዳለው ሩቅ ቦታ ወደሚገኝ አንድ ጥበበኛ ሰው ጋ ይሄዳል።

ከረጅም የእግር ጉዞ በኋላ ጥበበኛው ሰው ወደ ሚኖርበት በታላቅ ግምብ ወደ ተገነባ ቅጥር ግቢ ይደርሳል። ግቢውም ከተለያዩ ቦታዎች በመጡ የጠቢቡን ምክር በሚፈልጉ ነጋዴዎችና የተለያዩ ሰዎች የተጨናነቀ ሆኖ አገኘው።

ወረፋውን በትዕግስት ከጠበቀ በኋላ ከጠቢቡ ሰው ጋር ተገናኝቶ የመጣበትን ምክንያት አስረዳ። ጠቢቡም ሰው የልጁን ጥያቄ በትዕግስት አድምጦ ሲያበቃ ጥያቄውን ወዲያው መመለስ እንደማይችልና ከጥቂት ሰዓታት በኋላ እንደሚያገኘው አስከዚያ ግን በቤቱ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ስእሎችና ቅርጻ ቅርጾችን እንዲጎበኝ ነገረው። ጉብኝቱን ከመጀመሩ በፊት ጠቢቡ ሰው ለልጁ ማንኪያ ላይ ሁለት ጠብታ ዘይት አድርጎ ሰጠውና "ስዕሎቹንና ቅርጻ ቅርጾቹን ስትጎበኝ ይህንን ማንኪያ ይዘህ ሂድ፤ ነገር ግን ዘይቱ እንዳይደፋ ተጠንቀቅ" ብሎ ሸኘው።

ከሁለት ሰዓታት በኋላ ልጁ ወደ ጠቢቡ ሰው ማንኪያው ላይ ያለው ዘይት ሳይፈስበት ደረሰ። ጠቢቡም ሰው "ደህና፤ ጉብኝቱ እንዴት ነበር? እነዚያን በመመገቢያ ክፍሉ ውስጥ ያሉትን የፋርስ ስዕሎችና ምንጣፎችን አየሃቸው? አትክልተኛው ለማዘጋጀት አስር ዓመታትን የፈጀበት የአትክልቱን ስፍራስ? በቤተመጻሕፍቴ ውስጥ ያሉትን ብራናዎችስ?"

ብላቴናው በጣም አዘነ። እንደ እውነቱ ከሆነ እጁ ላይ ያለውን በማንኪያ ላይ ያለውን ዘይት እንዳይፈስ ሙሉ ትኩረቱን እዚያ ላይ በማድረጉ ምክንያት ጠቢቡ ሰው ያላቸውን ነገሮች አንዱንም እንዳላየ ተናዘዘ።

"አይዞህ እንደገና ሂድና በቤቴ ውስጥ ያሉትን ድንቅ ነገሮች ጎብኝ" ብሎ ጠቢቡ ሰው ብላቴናውን በድጋሚ ላከው። ከጥቂት እረፍት በኋላ ልጁ በማንኪያ ላይ ያለውን ዘይት ይዞ እነዚያን ድንቅ ነገሮቹን "ከእግር አስከራሱ" በሚባል ሁኔታ መጎብኘት ጀመረ።

ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ልጁ ወደ ጠቢቡ ሰው ተመለሰ። "እህስ እንዴት ነበር?" አለው። በሚደንቅ ሁኔታ ስላያቸውና ስለጎበኛቸው ነገሮች በዝርዝር ነገረው። "የሚደንቅ ነው" አለ ጠቢቡ ሰው። "ዘይቱስ የታለ?" ጠየቀ። ልጁ ጎንበስ ብሎ ቢመለከት ከሰዓታት በፊት የነበረው ሁለት ጠብታ ዘይት ማንኪያው ላይ የለም።

ጠቢቡ ሰው ልጁን በማረጋጋት እንዲህ ሲል መከረው "ደስታ ማለት ሚዛንን መጠበቅ ነው። በእጅህ ላይ ያለን ነገር ሳትጥል አስደናቂ ነገሮችንም መመልከትና መጎብኘትም ጭምር ነው።"

ይህ ታሪክ ህይወት ሚዛንን እንደምትሻ ሁነኛ ማሳያ ነው። በዚህች በምንኖርባት አጭር ዕድሜ የተሰጠን ኃላፊነትና እግዚአብሔር በእኛ ተጠቅሞ ሊሰራው ያሰበው ነገር ብዙ ነው። እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ በህይወት የሚገጥሙንን አያሌ ኃላፊነቶችን በጥበብና በሚዛን መያዝ ካልቻልን የሰራነውን ነገር የማበላሸት አቅም አላቸው።

ይህች አነስተኛ ጽሑፍ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የተጠመድን ሁላችን አገልግሎትና ቤተሰብን በሚዛን ማስኬድ እንዳለብን ቅን ልቡናችንን ለማነቃቃት ያለመች ናት።

የዳዊትን ህይወት ስናጠና ዕድሜውን ሙሉ ጊዜውን ከቤተሰቡ ጋር የማሳለፍ ዕድል ብዙም አልገጠመውም። በልጅነቱ በእረኝነት ምድረ በዳ ላይ የት እንዳለ እስኪረሳ ድረስ ቀጥሎም ከሳኦል ፊት ሸሽቶ ለ13 ዓመታት በምድረ በዳ ላይ ሲንከራተት የቆየ ሰው ነው።

እግዚአብሔር በወሰነው ጊዜ በእስራኤል ላይ በይፋ ንጉስ ከሆነ በኋላ ለብዙ አመታት ሳይፈለግ የቆየውን የእግዚአብሔርን ታቦት ለማምጣት ልቡ ተነሳሳ፤ እግዚአብሔርም ረዳው ወደ እስራኤል አመጣው።

አካሄዱን አስተካክሎ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ከተማው ካስገባና ህዝቡን ከባረከ በኋላ ወደ ቤተሰቡ እንደተመለሰ እናነባለን። *"ዳዊትም ቤተ ሰቡን ሊመርቅ ተመለሰ"* (1ኛ ሳሙ. 6፥20) ። ከዳዊት አንድ ነገር እንማራለን ቤተሰብና ሥራን (አገልግሎትን) ማመጣጠንን።

በዘመናቸው ቤተሰባቸውን ሰውተው ለእግዚአብሔር አገልግሎት ዕድሜያቸውን መስዋዕት ላደረጉ ሁሉ እግዚአብሔር በሰማያዊ በረከት ይባርካቸው ያስባቸውም። ዛሬ ይህንን ነገር የማስተካከል ዕድል ያለን አገልጋዮች ግን በነገሩ ላይ እንድናስብበት ጌታ ኢየሱስ ይርዳን!

በጣም ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር አገልጋዮች በተለያየ ሥራ ይጠመዳሉ፤ በዚህም እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሌላ ትልቅ ኃላፊነት እርሱም ቤተሰብን ከአገልግሎት ጋር በሚዛን ማስኬድ ይሳናቸዋል ።

አገልጋዮች ለቤተሰብም ሆነ ለራሳቸው እንዲሁም ለትክክለኛው አገልግሎት ጊዜ የሚያጡበት ምክንያት ብዙ ነው። ከእነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ፦

- በእጃቸው ላይ ያለው አገልግሎት ሲበዛ

*“እናንተ ራሳችሁ ብቻችሁን ወደ ምድረ በዳ ኑና ጥቂት ዕረፉ አላቸው፤ የሚመጡና የሚሄዱ ብዙዎች ነበሩና፥ ለመብላት እንኳ ጊዜ አጡ።”* (ማርቆስ 6፥31)

- አስፈላጊውን ነገር ካለማወቅና ካለማስተዋል

*“ኢየሱስም መልሶ፦ ማርታ፥ ማርታ፥ በብዙ ነገር ትጨነቂአለሽ ትታወኪማለሽ፥የሚያስፈልገው ግን ጥቂት ወይም አንድ ነገር ነው፤ ማርያምም መልካም ዕድልን መርጣለች ከእርስዋም አይወሰድባትም አላት።”* (ሉቃስ 10፥41)

- ሥራን ሊሰሩ ለሚችሉ ሰዎች ካለማከፋፈል የተነሣ

*“አሥራ ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ሁሉን ጠርተው እንዲህ አሉአቸው፦ የእግዚአብሔርን ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም። ወንድሞች ሆይ፥ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፥ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን፤ እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን።”* (ሐዋ 6፥3-5)

በነዚህም ምክንያቶች ለቤተሰብ የሚገባውን ጊዜ ያጣሉ።

በእግዚአብሔር መንግስት ላይ የተጠመደ አንድ አገልጋይ (የእግዚአብሔር ሰው) ቀኑ በጣም መሽቶ ወደ ቤትም ሲገባ ከባለቤቱና ከልጆቹ ጋር ያለው ጊዜ በጣም አጭር ከመሆኑ የተነሳ ቀን በተጠመደበት ነገር አዕምሮ የመያዝ ብሎም ከሸክምና ከጫና የተነሳም ከቤተሰብ ጋር ያለ ግንኙነት መሻከር ሊመጣ ይችላል።

ቀስ በቀስ ባለቤቱ እና ልጆቹ ከእርሱ የሚፈልጉት ጊዜና ትኩረት አደጋ ላይ ይወድቃል። ማስተዋል ከሌለም ከዚህ የተነሣ ባለቤቱና ልጆቹ ለመንፈሳዊ ነገር ጥላቻን ሊያተርፉና መንፈሳዊ ነገር ማለት አባትን ከቤተሰብ የሚነጥል አጉል ነገር እንደሆነ ሊያስቡ ይችላሉ።

የአገልጋዮች በተለይም በእረኝነት አገልግሎት ላይ ያሉ የእግዚአብሔር ሰዎች ቤታቸው በባለጉዳይ የሚጨናነቅ፣ ቅዱሳንም ካላቸው ፍቅርና አክብሮት የተነሳ እግር የሚያበዙበት ብሎም የከፋው፣ የተሰደደ፣ የታመመ ሁሉ የመጠጊያ ከተማ ስለሚያደርገው ከቤተሰብ ጋር ያላቸው ግንኙነትና ጊዜ እንደማንኛውም ባለጉዳይ እንዲያው ከዚያም ያነሰ ጊዜ ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ ብዙ ነው።

እግዚአብሔር ማንኛውም ሰው ስለቤተሰቡ ግድ የሚለው እንዲሆን ይጠብቃል። የሚያስፈልጋቸውን ጊዜ፣ ፍቅር፣ ዕርዳታና እገዛ ሊሰጣቸው ግድ ይላል። ቃሉም ይህንኑ ይደግፋል። *“ነገር ግን ለእርሱ ስለ ሆኑት ይልቁንም ስለ ቤተ ሰዎቹ የማያስብ ማንም ቢሆን፥ ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው።”* (1ኛ ጢሞ. 5፥8)

በመኃልይ መጽሐፍ ላይ የምናገኛት አንዲት የወይን ቦታ የነበራት ሴት አለች። ሌሎች ሰዎች የወይን ቦታዎቻቸውን እንድትጠብቅላቸው ግድ ሳይሏት አልቀረም። የወይን ቦታ ጠባቂ ከሌለው ከጥቃቅን ቀበሮዎች ጥፋት አንስቶ ለተለያየ ጉዳት እንደሚዳረግ የእግዚአብሔር ቃልም ይናገራል (ኢሳ. 27፥3፣ መኃ. 2፥15)። ልጅቷ የሌላውን የወይን ቦታ መጠበቋ ባይከፋም የራሷን የወይን ቦታ ግን ለአደጋ አጋልጣለች።

የእግዚአብሔር ሰዎች ሌሎችን እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ እያገለገሉ ለሌሎች መታነጽ፣ መባረክ፣ መለወጥና መፈወስ ምክንያት ሆነው ሳለ ሚዛን ከማጣት የተነሳ ቤተሰቦቻቸው ከነዚህ ድንቅ ሰዎች የሚገባውን ነገር ሳያገኙ ይቀራሉ። መፍትሔው እንደ ዳዊት ከሥራ በኋላ ከቤተሰብ ጋር ጊዜን ለማሳለፍ መፍቀድ ነው።

መንፈሳዊ አገልግሎት ሰዎችን ማዕከል ያደረገ እንደመሆኑ አገልጋዮች የተለያየ ጥያቄ ካላቸው ቅዱሳን ጋር ቀናቸውን ሙሉ የሚያሳልፉበት ጊዜ ብዙ ነው።

ከነገሮችና ከሚሰማው ጉዳይ የተነሳ በሚመጣ ክብደትና ጫና ሲደክም የዋለ የእግዚአብሔር ሰው ከጉዳዩ ወደ ቤት ከገባ የምግብ ጠረጴዛ ላይ ማስታወሻ ደብተርና ቃለ ጉባዔ ይዞ ላለመቀመጡ ምንም ዋስትና የለም።

ምሳሌው ለአገልጋይ የሚሆን ባይሆንም ሰው የዋለበትን መጥፎ ነገር ቤት ይዞ ሲገባ ቤተሰብን እንደሚረብሽ ከአክአብ መመልከት እንችላለን። *“... ኢይዝራኤላዊውም ናቡቴ፦ የአባቶቼን ርስት አልሰጥህም ብሎ ስለ ተናገረው አክዓብ ተቈጥቶና ተናድዶ ወደ ቤቱ ገባ። በአልጋውም ላይ ተጋድሞ ፊቱን ተሸፋፈነ፥ እንጀራም አልበላም። ሚስቱም ኤልዛቤል ወደ እርሱ መጥታ፦ ልብህ የሚያዝን እንጀራስ የማትበላ ስለምንድር ነው? አለችው”* (1 ነገስት 20፥1-5) ።

አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ዘመን አይሁዳውያን አንድ ልማድ ነበራቸው። በደጅ ላይ ውሃ ያለባቸው የድንጋይ ጋኖች (ዮሐ 2፥6) ያስቀምጡ ነበር። ከገበያ፣ ከጉዳያቸውና ከየትም ቦታ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ወደ ቤት ከመግባታቸው በፊት ታጥበው ነው የሚገቡት (ማርቆስ 7፥1-5)። ለቤተሰብ የማይሆነውን የዋሉበትን ጉዳይ በራፋቸው ላይ ጥለውና ነጽተው የሚገቡ ይመስለኛል።

መፍትሔው የእግዚአብሔር ቃል *“ገርነታችሁ ለሰው ሁሉ ይታወቅ። ጌታ ቅርብ ነው። በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ። አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።”* (ፊልጵ 4፥5-7) እንደሚል በጸሎት ሸክምን ሁሉ አራግፈን ሰላማዊ አዕምሮን ይዞ ቤተሰባችን መሐል መገኘት ነው። ሚስትና ልጆች ቤታቸው ውስጥ እንዲገባ የሚጠብቁት ባል እና አባትን እንጂ ቄስ ወይም ቢሾፕን አይደለም።

አገልጋዮች ሥራን በማከፋፈል በአስፈላጊ ነገር ላይ ጊዜን በማዋል ለቤተሰባቸው ጊዜን ሊያበጁ ይገባል።

ዮቶር ሙሴን እንዴት ሊመክረው ቻለ? ብዬ ሳስብ ሊነሱ የሚችሉ ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም አማች ነውና በእንግድነት መጥቶ የሙሴን ውሎ እና

**”**

**በዘመናቸው ቤተሰባቸውን ሰውተው ለእግዚአብሔር አገልግሎት ዕድሜያቸውን መስዋዕት ላደረጉ ሁሉ እግዚአብሔር በሰማያዊ በረከት ይባርካቸው ያስባቸውም።**

አዳር ከተመለከተ በኋላ ይመስለኛል ይህንን መላ የመከረው (ዘጸ 18፥1-27)። ሙሴ ከውሎው እንደ ገባ ብዙም ሊያጫውተው እንዳልቻለና ከሚስቱና ከልጆቹም ጋር በቂ ጊዜ ማሳለፍ እንዳቃተው ካየ በኋላ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ሐዋርያነቱ በተከራከረበት የቆሮንቶስ መልዕክት ላይ ስለ ጴጥሮስ እንዲህ ብሎ ነበር። *"...እንደ ሌሎቹ ሐዋርያትና እንደ ጌታ ወንድሞች እንደ ኬፋም፥ እኅት ሚስታችንን ይዘን ልንዞር መብት የለንምን?"* (1ኛ ቆሮ.9፥5)።

ጴጥሮስ እንዴት ከሚስቱ ጋር ሊዞር ቻለ? ብለን አሁንም ብንጠይቅ የበዓለ ሃምሳዋ ቤተክርስቲያን በተመሰረተችበት ጥቂት አመታት ውስጥ ሐዋርያትን ከዋና ተግባራቸው አውጥቶ ምግብ አካባቢ የሚያቆይ ችግር ሲፈጠር

ሐዋርያው ጴጥሮስ እኛ ለጸሎትና ለቃሉ እንትጋለን ሌሎቹን ነገሮች ሰዎች ይመረጡና ኃላፊነትን ይሸከሙ አለ። በሚመለከተው ጉዳይ ላይ ማተኮር፤ ጊዜን በአግባቡ መጠቀምና ኃላፊነቶችንና ሥራን ለሌሎች ማካፈል ከቤተሰባችን ጋር መልካም ጊዜ እንዲኖረን ያደርጋል።

ጴጥሮስ ለቤተሰብ ነገር ልዩ ስፍራ እንዳለው የምንመለከተውም ከመልዕክቱ ግማሽ ምዕራፍ ያህሉን ለባልና ለሚስት ግንኙነት መስዋዕት ማድረጉ ነው። የባልና የሚስት ጸሎትም የሚኖረው ጊዜ ሲኖር መሆኑም በዚሁ ክፍል ላይ ተቀምጦ እናገኛለን።

አገልጋይ ከቤተሰቡ ጋር የሚያሳልፈው ጊዜ መኖር አለበት ብለን ስንነጋገር አንድ ነገር ማስተዋል ተገቢ ነው። ያም ነገሩ ለቤተሰቡ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ለአገልጋዩና ለቀጣይ አገልግሎቱም ጭምር ነው። ቤታችን የምንታደስበት ቦታ ነው። በእንቅልፍ አማካይነት የሞቱ ሴሎቻችን እንደሚተኩ ሁሉ ከቀኑ ድካምና ጉዳይ ፋታ የምናገኝበትም ሥፍራ ነው። እንደገና ለመልካም ሥራ የምንነቃቃበት ሥፍራ ነው። ሌላው መዘንጋት የሌለብን ለሌሎች ምዕመናኖቻችን ነፍስ እንደምንጨነቀውና ተጠያቂ እንሆናለን ብለን እንደምናስበው ሁሉ

ስለ ቤተሰቦቻችንም ያው ስሜት ሊኖረን ይገባል። ቤተሰቦቻችን ቤተሰቦቻችን ብቻ ሳይሆኑ ምእመናኖቻችንም ናቸውና። በተጨማሪም የቤተሰቦቻችን ብልሹ አካሄድ ለሌላው መሠናክል የሚሆንና የእኛንም አገልግሎት የሚያስነቅፍ ይሆናል።

ስንጀምር እንደተመለከትነው ዳዊት አብዛኛው ዘመኑን ቤት ውስጥ (የተደራጀ ቤተሰብ ውስጥ) አላሳለፈም። እንዲያውም በምድረ በዳ እያለ እንቅልፍ እንኳ በአግባቡ አይተኛም ነበር (1ኛ ሳሙ. 26፥7)። ምንም እንኳ በነዚህ የስደትና የመንከራተት ዓመቶች ለእግዚአብሔር ሥራን የሰራ ቢሆንም በ2ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 7 ላይ የሚከተለው ሰፍሮ እናገኛለን።

*"እንዲህም ሆነ፤ ንጉሡ በቤቱ በተቀመጠ ጊዜ እግዚአብሔርም በዙሪያው ካሉት ጠላቶቹ ሁሉ ባሳረፈው ጊዜ፥ ንጉሡ ነቢዩን ናታንን፦ እኔ ከዝግባ በተሠራ ቤት ተቀምጬአለሁ፥ የእግዚአብሔር ታቦት ግን በመጋረጆች ውስጥ እንደ ተቀመጠ እይ አለው"* (2ኛ ሳሙ. 7፥1-2)።

ይህንን ታላቅ ራዕይ ያገኘው ቤቱ ጊዜ ማሳለፍ በመጀመሩ እና በቂ እንቅልፍ በማግኘቱም ጭምር እንደሆነ ይህ ክፍል ጨምሮ ያስረዳናል። ዳዊት ቤቱ ሲቀመጥና ሲያርፍ ወደ አዲስ ራዕይ ተሸጋገረ (ቤቱ ላይ ሥራውን ትቶ አላግባብ ሲቀመጥ ያመጣበት ችግር እንዳለ ሆኖ)። በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ለሩቅ ዘመን የሆነን ቃል ኪዳን ለቤተሰቡ ተናገረ። *"እግዚአብሔርም ደግሞ፦ ቤት እሠራልሃለሁ ብሎ ይነግርሃል"* (2ኛ ሳሙ. 7፥10-11)።

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ባዘዛቸው በዓላት ላይ ሰው ከቤተሰቡ ጋር እንዲታይ በአጭር ቃል ሰው ከቤተሰቡ ጋር አብሮ ሲደሰት ማየት ይፈልግ ነበር። *"በዚያም በገንዘቡ ሰውነትህ የፈለገውን፥ በሬ ወይም በግ ወይም የወይን ጠጅ ወይም ብርቱ መጠጥ ሰውነትህም የሚሻውን ሁሉ ትገዛለህ በዚያም በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት ትበላዋለህ፥ አንተና ቤተ ሰብህም ደስ ይላችኋል።"* (ዘዳ. 14፥26) ፤ *"አምላክህ እግዚአብሔር በመረጠው ስፍራ አንተና ቤተ ሰብህ በየዓመቱ በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት ብሉአቸው።"* (ዘዳ. 15፥20)።

ቤት ሰላማዊና እረፍት ያለበት እንዲሆን እግዚአብሔርም ይፈልጋል። ኑኃሚን አንድ ሰው ቤተሰብ ሲኖረው ዕረፍት እንደሚኖረው በማወቅ ሁለቱንም የልጆቿን ሚስቶች በዚህ ቃል መረቃለች። *"እግዚአብሔር በየባላችሁ ቤት ዕረፍት ይስጣችሁ አለቻቸው።"* (ሩት 1፥9)። በተጨማሪም ለሩት ትዳርን ስታስብ ያለቻት ነገር *"ልጄ ሆይ፥ መልካም እንዲሆንልሽ ዕረፍት አልፈልግልሽምን?"* (ሩት 3፥1) ነው።

ወደ ነገሩ ፍጻሜ ስንመጣ በቀረልን ዘመን አገልግሎታችንና ቤተሰባችን የሚባረክበትና በሚዛን የምናስኬድበት ዘመን ይሁንልን።

ምን አልባት ከላይ ያለውን ነገር ተመልክተን ተስፋ የምንቆርጥ ካሁን ወዲያ ማስተካከል የምችል አይመስለኝም የምንል ካለን ዕዝራ ነገሮች የጨለሙ ሲመስሉ የተናገረውን ነገር አስታውሼ ላብቃ።

*"ከኤላም ልጆች ወገን የነበረም የይሒኤል ልጅ ሴኬንያ ዕዝራን እንዲህ ብሎ ተናገረው፦ አምላካችንን በድለናል፤ የምድርን አሕዛብ እንግዶች ሴቶችን አግብተናል፤ አሁን ግን ስለዚህ ነገር ገና ለእስራኤል ተስፋ አለ።"* (ዕዝራ 10፥2)

ስለዚህ ነገር ተስፋ አለ! እንበልና እንነሳ!

እግዚአብሔር አገልግሎታችንንም ቤታችንንም ይባርክልን! ■

## ”

## አገልጋዮች ሥራን በማከፋፈል በአስፈላጊ ነገር ላይ ጊዜን በማዋል ለቤተሰባቸው ጊዜን ሊያበጁ ይገባል።

# ልጆቻችን

እግዚአብሔር ስጦታ አድርጎ የሰጠን ልጆች ፍላጎት ብዙ ነው፥፥ ነገር ግን ሁሉም ልጆች በጋራ ቢያንስ ሰባት ፍላጎት አላቸው፥፥ እነርሱም፥-

1. ተደማጭነት
2. ዋስትና
3. ተቀባይነትን ማግኘት
4. መወደድ
5. መመስገን
6. በሥነ ሥርዓት ወይም በሥነ ምግባር መታነጽ
7. እግዚአብሔርን ማወቅ

ጌታ ኢየሱስ ፍላጎታቸውን እንድናሟላ ጥበብን፣ ማስተዋልንና ኃይልን ይስጠን! ■